## የጠበቆችና ፡ የሕግ ፡ አማካሪዎች ፡
## የሕግ ፡ ሥነ ፡ ምግባር ።

የሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ በተለይ ፡ ተሠማርተው ፡ የሚሠሩት ፡ በተለያዩ ፡ የሥራ ፡ መስኰች ፡ ሲሆን ፡ ከነዚሁም ፡ ጥቂቶቹ ፡ በመንግሥት ፡ ድርጅቶች ፡ ውስጥ ፤ በኩባንያዎች ፤ በዳኝነት ፤ በሕግ ፡ አስከባሪነት ፤ በፓርላማ ፤ በጥብቅና ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ለመተንተን ፡ የምንፈልገው ፡ የጥብቅናን ፡ ሥራ ፡ ሞያ ፡ አድርገው ፡ ለሚኖሩት ፡ ብቻ ፡ ነው ። በመሠረቱ ፡ የጠበቆች ፡ አስፈላጊነት ፡ ለሁለት ፡ ዓብይ ፡ ምክንያቶች ፡ ሲሆን ፡ ይኸውም ፡ ለምክርና ፡ ለጥብቅና ፡ ነው ። የሕግ ፡ ምክር ፡ ወይም ፡ ሐሳብ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በግል ፡ ሊደረግ ፡ ይችላል ፤ ይኸውም ፡ መሬት ፡ ሲሸጥ ፡ የሺያጩን ፡ ስምምነት ፡ መጻፍ ፤ የንግድ ፡ ማኅበር ፡ ሲቋቋም ፡ የማኅበሩን ፡ የመመሥረቻ ፡ ጽሑፍና ፤ የመተዳደሪያ ፡ ደንቡን ፡ ማዘጋጀት ፤ እንዲሁም ፡ ማንኛውንም ፡ የሕግ ፡ ሐሳብ ፡ እንዳስፈላጊነቱ ፡ ለደንበኞቹ ፡ መስጠትን ፡ ጭምር ፡ ያጠቃልላል ። ጥብቅና ፡ ግን ፡ በግልጽ ፡ ወይም ፡ በገሃድ ፡ የሚደረግ ፡ ሥራ ፡ ነው ። ጠበቃ ፡ ደንበኛው ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ ወይም ፡ ተወክሎ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፤ በፖሊስ ፡ ጣቢያ ፤ በአስተዳደር ፡ ቦርድ ፤ በግብር ፡ ሰሚ ፡ ጉባዔ ፤ በአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ቦርድ ፡ እንዲሁም ፡ የዳኝነትን ፡ መልክ ፡ በያዙ ፡ ገላጋይ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ዘንድ ፡ ቀርቦ ፡ ይከራከራል፡ ይሟገታል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ጠበቃ ፡ ለደንበኛው ፡ ቆሞ ፡ ይከራከራል ፡ ሲባል ፡ እርታታን ፡ አግኝቶ ፡ ደንበኛውን ፡ ለማስደሰት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የፍርድ ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ በሚገባና ፡ በትክክል ፡ እንዲመራ ፡ ማድረግ ፡ ተጨማሪውና ፡ ዓብይ ፡ ግዴታው፡ መሆኑ ፡ መታወቅ ፡ አለበት ። ጥብቅና ፡ ሞያ ፡ እንጂ ፡ ንግድ ፡ አይደለም ። ስለሆነም ፡ ጥብቅና ፡ እጅግ ፡ ከፍተኛ ፡ ግዴታና ፡ ኃላፊነት ፡ ያለበት ፡ ሞያ ፡ ነው ።

አንድ ፡ ጠበቃ ፡ ያለበት ፡ ግዴታ ፡ ብዙ ፡ ቢሆንም ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ በአራት ፡ የተከፈሉ ፡ ሲሆኑ ፡ እነርሱም ፡ ጠበቃው ፡ ለመንግሥት ፤ ለፍርድ ፡ ቤት ፤ ለደንበኛውና ፡ ለመሰሎቹ ፡ ጠበቆች ፡ ያሉት ፡ ግዴታዎች ፡ ናቸው ። እነዚህ ፡ ግዴታዎች ፡ በሚገባ ፡ ሊከበሩ ፡ የሚችሉት ፡ ጥብቅና ፡ እንደ ፡ ንግድ ፡ ሥራ ፡ ሳይቆጠር ፡ እንደ ፡ ሞያ ፡ የተያዘ ፡ እንደሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ወደ ፡ ጽሑፉ ፡ ትንተና ፡ ከመግባታችን ፡ አስቀድሞ ፡ ሞያ ፡ ማለት ፡ ምን ፡ ማለት ፡ መሆኑን ፡ የሞያ ፡ ምንጮች ፡ ምን ፡ መሆናቸውንና ፡ የሞያስ ፡ መንፈስ ፡ ከሌሎች ፡ ሥራዎች ፡ ማለትም ፡ ለምሳሌ ፡ ከንግድ ፡ የሚለየው ፡ በምን ፡ በምን ፡ እንደሆነ ፡ እንመራመራለን ። ሮቬ ፡ ፓውንድ ፡ የተባለው ፡ አሜሪካዊ ፡ የሕግ ፡ ሊቅ ፡ ስለሞያ ፡ ሲተነትን ፡ እንዲህ ፡ ይላል ። «ሞያ ፡ በጥንት ፡ ጊዜ ፡ ለሶስት ፡ ሥራዎች ፡ ብቻ ፡ ማለትም ፡ ለቅስና ፤ ለሕክምና ፤ ለጥብቅና ፡ የተሰጠ ፡ መለያ ፡ ነበር ። ምንም ፡ እንኳ ፡ እነዚህ ፡ ሶስቱ ፡ ሙያዎች ፡ በቀድሞ ፡ ጊዜ ፡ ዋና ፡ ዓላማቸው ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ አገልግሎትን ፡ መስጠት ፡ ቢሆንም ፡ ዛሬ ፡ ይህንን ፡ ዓላማቸውን ፡ እየለቀቁ ፡ ሄደዋል ። በመሠረቱ ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ዋና ፡ ዓላማው፡ ትርፍ ፡ ማስገኘት ፡ ነው ። በሌላው ፡ አንጻር ፡ የሙያ ፡ ዓላማ ፡ ግን ፡ ሕዝብን ፡ ማገልገል ፡ ሲሆን ፡ ትርፉ ፡ በሙያ ፡ አማካይነት ፡ የሚያገኘው ፡ እንደ ፡ ጭፍጫፊ ፡ የሚቆጠር ፡ መጠቀሚያ ፡ ነው ። ...»

የንግድ ፡ ዋና ፡ ዓላማው ፡ ባለንብረቱ ፡ የሚያገኘውን ፡ ትርፍ ፡ ማዳበር ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ የነጋዴ ፡ መሠረታዊ ፡ ጉጉቱ ፡ ገንዘብ ፡ ሊያገኝ ፡ የሚችልበትንና ፡ ደንበኛው ፡ የማይሸሽበትን ፡ ዘዴ ፡ ማጠናቀር ፡ ነው ። ምንም ፡ እንኳ ፡ በሙያ ፡ አማካይነት ፡ ብዙ ፡ ትርፍ ፡ የሚያስገኝ ፡ መንገድ ፡ ቢኖርም ፡ ባለሙያው ፡ ጥቅሙን ፡ ብቻ ፡ በመመልከት ፡ የተወሰነውን ፡ ሥነ ፡ ምግባር ፡ ወደጎን ፡ መተው ፡ ፈጽሞ ፡ የተከለከለ ፡ አድራጎት ፡ ነው ። ጥብቅና ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ስላልሆነ ፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ የሕግ ፡ ጠበቃ ፡ አዲስ ፡ ቢሮ ፡ እዚህ ፡ ሥፍራ ፡ ከፍቻለሁና ፡ የጥብቅና ፡ አገልግሎት ፡ የምትፈልጉ ፡ ሁሉ ፡ ማንኛውም ፡ እርዳታ ፡ ለመስጠት ፡ ዝግጁ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ በሬዲዮና ፡ በጋዜጣ ፡ ራሱን ፡ ማስተዋወቅ ፡ በፍጹም ፡ የለበትም ። በጥብቅና ፡ የተሠማራ ፡ ባለሙያ ፡ ደንበኞች ፡ የሚያመጣለት ፡ ደላላ ፡ አይቀጥርም ። በንግድ ፡ ሥራ ፡ ግን ፡ በማስታወቂያ ፡ አማካይነት ፡ ደንበኛን ፡ ማግባባትና ፡ መሳብ ፡ ደግሞም ፡ ለሽያጭ ፡ ክፍል ፡ ኰሚሲዮን ፡ ማሰብ ፡ የትርፍ ፡ ማግኛ ፡ ዘዴ ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ የጥብቅና ፡ ዋናው ፡ መሠረት ፡ ሙያ ፡ ወይም ፡ አገልግሎት ፡ እንጂ ፡ ንግድ ፡ አይደለም ። እዚህ ፡ ላይ ፡ ስለሙያ ፡ ትርጉም ፡ ኮኸን ፡ የተባለው ፡ በ፲፱፻፷፬ ፡ (እ.ኤ.አ.) በጻፈው ፡ ዘ ፡ ሎ ፡ ቢዝነስ ፡ ኦር ፡ ፕሮፌሽን ፡ በተሰኘው ፡ መጽሐፍ ፡ በገጽ ፡ ፫፻፴፮ ፡ ቶኒስ ፡ ከተባለው ፡ ደራሴ ፡ የቀዳውን ፡ (የጠቀሰውን) ማብራሪያ ፡ እንመልከት ።

«ሞያ ..... የተለዩ ፡ ሰዎች ፡ አባሎቻቸው ፡ በተሻለ ፡ መንገድ ፡ እንዲጠበቁና ፡ ሕዝቡም ፡ የተሻለ ፡ አገልግሎት ፡ እንዲያገኝ ፡ በማሰብ ፡ ሥራቸውን ፡ ደንቡ ፡ በሚፈቅደው ፡ መሠረት ፡ ለማከናወን ፡ እንዲያስችል ፡ የተሟላ ፡ ደረጃ ፡ የሚያስጠብቁበት ፡ አቋም ፡ ነው ። ..... ሞያ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ለሙያተኛው ፡ ጥቅም ፡ ወይም ፡ ትርፍ ፡ የሚያመጣለት ፡ ቢሆንም ፡ ሙያተኛው ፡ አባል ፡ ለሆነበት ፡ አቋም ፡ ውርደት ፡ እንዳያመጣ ፡ ሙያተኛው ፡ የተወሰኑ ፡ ተግባሮችን ፡ እንዳይፈጽም ፡ በግልጽ ፡ ይከለክላል ። ... ስለዚህም ፡ በኢንዱስትሪና ፡ በሞያ ፡ መካከል ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ በጣም ፡ ግልጽና ፡ የማያሳስት ፡ ነው ። የኢንዱስትሪ ፡ ዋናው ፡ ዓላማ ፡ የባለአክሲዮኑን ፡ የገንዘብ ፡ ትርፍ ፡ ማዳበር ፡ ነው ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ሞያ ፡ ለሰዎች ፡ የዕለት ፡ ጉርስ ፡ ቢያስገኝላቸውም ፡ የሙያቸው ፡ ውጤት ፡ የሚለካው ፡ በሚሠጡት ፡ አገልግሎት ፡ እንጂ ፡ በሚሰበስቡት ፡ ገንዘብ ፡ ብዛት ፡ አይደለም ።»

ሕግ ፡ በጣም ፡ የላቀና ፡ የተከበረ ፡ ሙያ ፡ ነው ። ሙያ ፡ ከንግድ ፡ የሚለይበት ፡ ሁኔታ ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ ከላይ ፡ የገለጽነው ፡ ሲሆን ፡ ሞያ ፡ ራሱ ፡ የተወሰኑ ፡ ጠባዮች ፡ አሉት ። አሜሪካዊ ፡ የሕግ ፡ ሊቅ ፡ ፓውንድ ፡ ሞያ ፡ ሶስት ፡ መሠረታዊ ፡ ሐሳቦችን ፡ እንደያዘ ፡ ሲያስረዳ ፡ አንደኛ ፡ ሞያ ፡ አቋም ፡ ያለው ፡ መሆን ፡ እንዳለበት ፤ ሁለተኛ ፡ የተለየ ፡ ትምህርትን ፡ እንደሚጠይቅና ፡ ሦስተኛም ፡ ሞያ ፡ ሕዝብን ፡ በማገልገል ፡ መንፈስ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ መሆን ፡ እንዳለበት ፡ ይገልጻል ። የአቋም ፡ (የድርጅት) አስፈላጊነት ፡ ሞያን ፡ ከሌሎች ፡ ሥራዎች ፡ እጅግም ፡ አይለየውም ፤ ምክንያቱም ፡ የቀን ፡ ሠራተኞቹ ፡ እንኳን ፡ በአንድነት ፡ ተሰብስበው ፡ አንድ ፡ አቋም ፡ ፈጥረው ፡ የአባሎቻቸውን ፡ ጥቅምና ፡ መብት ፡ የሚጠበቅበትን ፡ መንገድ ፡ መፈለግ ፡ ይችላሉና ፡ ነው ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ የፍርድ ፡ ሥራ ፡ በሚገባ ፡ ሊካሄድ ፡ የሚችለው ፡ ጠበቆች ፡ አንድ ፡ አቋም ፡ ኖሯቸው ፡ አባሎቻቸው ፡ የተወሰኑ ፡ ሥነ ፡ ተግባሮችን ፡ አክብረው ፡ ሲገኙና ፡ ሞያው ፡ ክብር ፡ አግኝቶ ፡ በሚገባ ፡ ሲደራጅ ፡ መሆኑ ፡ መዘንጋት ፡ የለበትም ።

ሞያ ፡ የተለየ ፡ ትምህርትን ፡ እንደሚጠይቅ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። የሞያ ፡ አባል ፡ የሆኑ ፡ ሁሉ ፡ ከልዩ ፡ ትምህርቱ ፡ በስተቀር ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ ችግር ፡ ለማቃለልና ፤ በየዕለቱ ፡ በሌላው ፡ የሚያጋጥመውን ፡ ችግር ፡ ለማቃለል ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ጠቅላላ ፡ ዕውቀት ፡ ያስፈልገዋል ። ሶስተኛው ፡ የሞያ ፡ ጠባይ ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ማበርከት ፡

ነው ። አንድ ፡ ሆቴል ፡ ወይም ፡ መደብር ፡ ከሌላው ፡ ሆቴል ፡ ወይም ፡ መደብር ፡ ጋር ፡ በንግድ ፡ ሥራው ፡ እንደሚወዳደር ፡ አይጠረጠርም ፤ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ ግን ፡ ከሌላው ፡ ጠበቃ ፡ ጋር ፡ በሥራው ፡ አይወዳደርም ። ምክንያቱም ፡ ዓላማው ፡ ገንዘብ ፡ መሰብሰብ ፡ አይደለምና ። እንዲያውም ፡ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ ለችግረኞቹ ፡ በነፃ ፡ ቆሞ ፡ የሕግ ፡ እርዳታ ፡ እንዲሰጥ ፡ ሲጠየቅ ፡ ጥያቄውን ፡ መቀበል ፡ ይገባዋል ። ባለሆቴሎች ፡ ወይም ባለ ፡ መደብሮች ፡ ግን ፡ ዋናው ፡ ግባቸው ፡ ገንዘብና ፡ ትርፍ ፡ በመሆኑ ፡ ለችግረኞች ፡ የነፃ ፡ አገልግሎት ፡ እንዲሰጡ ፡ አይጠበቁም ፡ አይሰጡምም ።

ፓውንድ ፡ እንደገለጸው ፡ ሁሉ ፡ ጥብቅና ፡ ሞያ ፡ በመሆኑ ፡ አቋም ፡ ያለው ፡ ሥራ፡ መሆን ፡ ስለሚገባው ፡ በብዙዎቹ ፡ አገሮች ፡ በሕግ ፡ የተቋቋመ ፡ የጠበቆች ፡ ማሕበር፡ አለ ። ማኅበሩም ፡ የጥብቅና ፡ ፈቃድ ፡ አሰጣጥን ፤ በአጥፊ ፡ ጠበቃ ፡ ላይ ፡ አስፈላጊውን ፡ ቅጣት ፡ በመውሰድ ፡ ረገድና ፡ የፍርድ ፡ ሥራ ፡ በሚገባ ፡ መመራቱን ፡ ይቆጣጠራል ። ይሁንና ፡ የየሀገሩ ፡ የጥብቅና ፡ አቋም ፡ እንደ ፡ አገሩ ፡ ታሪክና ፡ ባሕል ፡ የተለያየ ፡ ነው ። ዋናው ፡ ዓላማው ፡ ግን ፡ የሞያው ፡ ክብር ፡ እንዲጠበቅ ፡ የፍርድ ፡ ሥራ ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ እንዲካሄድና ፡ እንዲደራጅ ፡ ማድረግ ፡ ነው ። የኢትዮጵያን ፡ የጥብቅና ፡ አቋምና ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ምግባር ፡ ከመመልከታችን ፡ አስቀድሞ ፡ የዓለም ፡ አቀፍ ፡ የሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ ጉባዔ ፡ «ኢንተርናሽናል ፡ ኮሚሽን ፡ ኦፍ ፡ ጁሪስትስ» በልዩ ፡ ልዩ ፡ አገሮች ፡ የአደረጋቸውን ፡ የሕግ ፡ ሞያ ፡ አቋም ፡ ጥናቶች ፡ መመልከቱ ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ ይሆናል ። የጥናቶቹ ፡ ትንታኔ ፡ ዓላማ ፡ የአንዱን ፡ አገር ፡ ጥናት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ በቀጥታ ፡ ይጠቅማታል ፡ ለማለት ፡ ሳይሆን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላሉት ፡ ተመሳሳይ ፡ ችግሮች ፡ በሌላው ፡ ሀገር ፡ የተገኘው ፡ መፍትሔ ፡ ይጠቅማል ፡ ብለን ፡ ስለ ምናምን ፡ ነው ። ሌሎቹ ፡ አገሮች ፡ አሁን ፡ ካሉበት ፡ ሥልጣኔ ፡ ላይ ፡ ለመድረስ ፡ አያሌ ፡ ዓመታት ፡ ፈጅቶባቸዋል ። ኢትዮጵያ ፡ ግን ፡ ሌሎቹ ፡ አገሮች ፡ የደረሱበት ፡ ላይ ፡ ለመድረስ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ዘመን ፡ ለመጓዝ ፡ አትችልም ። ሌሎቹ ፡ አገሮች ፡ በረጅም ፡ ዘመናት ፡ ያገኙትን ፡ ውጤት ፡ በመከተልና ፡ በመቅዳት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሌሎች ፡ ከደረሱበት ፡ በአጭር ፡ ጊዜ ፡ ለመድረስ ፡ ትችላለች ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከሌሎች ፡ ያዩትንና ፡ ያገኙትን ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ መከተልና ፡ መቅዳት ፡ ከጥቅሙ ፡ ይልቅ ፡ ጉዳቱ ፡ የሚያመዝን ፡ ቢሆንም ፡ በየሐገሩ ፡ የተደረገውን ፡ ምርምር ፡ ማወቁ ፡ በቀላሉ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋል ፡ የሚችሉትንና ፡ የሚጠቅሙትን ፡ ለመለየት ፡ ስለሚያስችል ፡ ምንጊዜም ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ።

ከላይ ፡ በተገለጸው ፡ ኮሚሽን ፡ የተደረገው ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ሀገሮች ፡ የሕግ ፡ ሞያ ፡ አቋም ፡ ጥናት ፡ የሚከተለው ፡ ነው ።

<u>የሕግ ፡ ሞያ ፡ አቋም ፡-</u>

ሀ/ <u>የእንግሊዝ ፡ ሀገር ፡</u>

የሕግ ፡ ሞያ ፡ አቋም ፡ በሁለት ፡ የተከፈለ ፡ ነው ። አንደኛው ፡ ክፍል ፡ በየፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በጥብቅና ፡ ቆመው ፡ የሚነጋገሩ ፡ «ባሪስተርስ» ተብለው ፡ የሚጠሩትን ፡ የያዘ ፡ ሲሆን ፤ ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ደግሞ ፡ ከየባለጉዳዩ ፡ ጋር ፡ በቀጥታ ፡ በመገናኘት ፡ ጉዳዩን ፡ አውቀው ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ምርምርና ፡ ጥናት ፡ አድርገው ፡ በጥብቅና ፡ ለሚነጋገሩ ፡ የሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ ጉዳዩን ፡ የሚያቀርቡትን ፡ «ሶሊስተርስ» የያዘ ፡ ነው ። በዚህም ፡ በሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ በኢንግላንድና ፡ በዌልስ ፡ ብቻ ፡ አሥራ ፡ ስባት ፡ ሺህ ፡ ያህል ፡ ባለሞያዎች ፡ እንዳሉ ፡ ሲታወቅ ፡ እነሱም ፡ በከፍተኛው ፡ ፍ/ቤት በይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤትና ፡ በሐውስ ፡ ኦፍ ፡ ሎርድስ ፡ ቀርበው ፡ ሊነጋገሩ ፡ አይችሉም ።

የሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ አቋም ፡ የሚካሄደው ፡ በሕግ ፡ ማሕበር ፡ ሲሆን ፡ ይህም ፡ ማሕበር ፡ በሕግ ፡ የተወሰኑ ፡ ሥልጣኖች ፡ አሉት ። አንድ ፡ ሰው ፡ የዚሁ ፡ ክፍል ፡

አባል ፡ ለመሆን ፡ በሚፈልግበት ፡ ጊዜ ፡ በማሕበሩ ፡ በኩል ፡ ማስተር ፡ ኦፍ ፡ ዘ ፡ ሮልስ ፡ (በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ዘንድ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቦታ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው) ፡ ለተባለው ፡ ሰው ፡ ማመልከቻውን ፡ ያቀርባል ። ማሕበሩም ፡ የመገልገያ ፡ ሰርቲፊኬት ፡ በየዓመቱ ፡ ይሰጣል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በአንዳንድ ፡ ምክንያቶች ፡ ሰርቲፊኬቱን ፡ ሊነፍግ ፡ ይችላል ። ለመንፈጉም ፡ ምክንያት ፡ ሊሆን ፡ ከሚችሉት ፡ ምክንያቶች ፡ አንዱ ፡ አመልካቹ ፡ የከሠረና ፡ ዕዳውን ፡ ለመክፈል ፡ ሳይችል ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ። በተጨማሪም ፡ ይኸው ፡ ማኅበር ፡ የአባሎቹ ፡ ማረሚያ ፡ ሥርዓቶችን ፡ ያዘጋጃል ። የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አስከባሪ ፡ ኮሚቴውም ፡ በሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ በተጠቀሱት ፡ ሰዎች ፡ (ሶሊስተርስ) ላይ ፡ የሚቀርበውን ፡ የቅሬታ ፡ ክስ ፡ ተቀብሎ ፡ በመስማት ፡ ጥፋቱን ፡ በሚያረጋግጥበት ፡ ጊዜ ፡ ክሱ ፡ የቀረበበት ፡ ሰው ፡ ለጊዜው ፡ ከሥራው ፡ እንዲታገድ ፡ ወይም ፡ ከአገልግሎቱ ፡ ውጭ ፡ እንዲሆን ፡ ሊወሰን ፡ ይችላል ። «ሶሊስተሩ» ፡ የጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ባልደረባ ፡ በመሆኑ ፡ ቁጥጥር ፡ የሚደረግበትም ፡ በዚሁ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ።

በጥብቅና ፡ ቋመው ፡ የሚነጋገሩት ፡ (ባሪስተርስ) ባለሞያዎች ፡ በጉዳዩ ፡ አጥኚና አዘጋጅ ፡ (ሶሊስተር) ምክር ፡ ካልሆነ ፡ ከየተራው ፡ ባለጉዳይ ፡ ጋር ፡ በቀጥታ ፡ ግንኙነት ፡ የላቸውም ። ለእነኚህም ፡ ባለሞያዎች ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ የመነጋገሩ ፡ ሥልጣን ፡ በተለይ ፡ ተሰጥቶአቸዋል ። በዚህም ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ተሰማርተው የሚገኙት ፡ ሰዎች ፡ ብዛት ፡ ፪ሺ ፡ ያህል ፡ ሲሆን ፡ ጠቅላይ ፡ ድርጅቶቻቸውም ፡ «ኢንስ ኦፍ ፡ ኮርትስ» ፡ ተብለው ፡ ይጠራሉ ። እያንዳንዱ ፡ ጠበቃ ፡ ከነኚህ ፡ ድርጅቶች ፡ ያንዱ ፡ አባል ፡ መሆን ፡ አለበት ። በዚህም ፡ የጥብቅና ፡ ሥራ ፡ ተሠማርቶ ፡ ለመሥራት ፡ የሚፈልግ ፡ ሰው ፤ በተማሪነት ፡ መልክ ፡ የድርጅቱ ፡ አባል ፡ ይሆናል ። ድርጅቱም ፡ ተማሪው ፡ ለጥብቅና ፡ ሥራ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ችሎታ ፡ አግኝቷል ፡ ብሎ ፡ በሚያምንበት ፡ ጊዜ ፡ ጥብቅናውን ፡ እንዲጀምር ፡ ይፈቀድለታል ። ከሥራውም ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ባላቸው ፡ ነገሮች ፡ ጠበቃው ፡ ለሚያደርገውና ፡ ለሚያሳየው ፡ መጥፎ ፡ ጠባይ ፡ ሁሉ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ የቅጣት ፡ እርምጃ ፡ የሚወስዱት ፡ እነኚሁ ፡ ድርጅቶች ፡ ናቸው ። የድርጅቶችም ፡ አስተዳደር ፡ የሚካሄደው ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ሥራቸው ፡ ዳኝነት ፡ በሆነው ፡ በድርጅቶቹ ፡ ነባር ፡ አባሎች ፡ ሲሆን ፡ ድርጅቶቹም ፡ በሚያደርጉት ፡ ውሣኔ ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ ለዳኛ ፡ ይግባኝ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

በሹማምንቱ ፡ ምርጫ ፡ ጠበቆች ፡ (ባሪስተርስ) ሁሉ ፡ ተካፋይ ፡ የሚሆኑበት ፡ ድርጅቱን ፡ የሚወክል ፡ ጠቅላይ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አለ ። ይህም ፡ ጠቅላይ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በቀጥታ ፡ ቅጣት ፡ የመወሰን ፡ መብት ፡ የለውም ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ የሞያተኛን ፡ ጠባይ ፡ አራሚ ፡ ኮሚቴው ፡ አንዳንድ ፡ ከሞያው ፡ ጋር ፡ የተያያዙ ፡ ቅሬታዎችን ፡ በመቀበልና ፡ በመመርመር ፡ ለተገቢው ፡ ድርጅት ፡ (ኢን) ጉዳዩን ፡ ያስተላልፈዋል ። በተጨማሪም ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ በጠበቆቹ ፡ ግብረ ፡ ገብ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ አስተያየትና ፡ ውሳኔ ፡ እየሰጠ ፡ በዓመታዊ ፡ ሪፖርት ፡ ላይ ፡ እንዲወጣ ፡ ያደርጋል ። ከጥፋት ፡ እንዲወገዱ ፡ የሚያደርጋቸው ፡ ከቅጣት ፡ ይልቅ ፡ በሞያተኞቹ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ያንድነትና ፡ የመከባበር ፡ መንፈስ ፡ ሲሆን ፤ ይህም ፡ የአንድነት ፡ መንፈስ ፡ በእንግሊዝ ፡ ሀገር ፡ የሕግ ፡ ሞያተኞች ፡ (ባሪስተርስ) ዘንድ ፡ ዕድሜአቸውን ፡ ሙሉ ፡ የሚጠቀሙበት ፡ በመሆኑ ፤ ይህ ፡ ዓይነቱ ፡ ስሜት ፡ በሌሎች ፡ «ኰመን ፡ ሎ» ሀገሮች ፡ ተወዳዳሪ ፡ የለውም ፡ ተብሎ ፡ ይገመታል ።

ለ/ <u>በአሜሪካ ፡ ውስጥ ፤</u>

የጥብቅና ፡ ሥራ ፡ የሕዝቡን ፡ ሕይወት ፡ የሚነካ ፡ ሞያ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ስለሚታመንበት ፤ የሕግ ፡ ሰዎች ፡ በጥብቅና ፡ ሥራ ፡ ከመሠማራታቸው ፡ አስቀድሞ ፡ ለሞ

ያው ፡ የሚያበቁትን ፡ የችሎታ ፡ ደረጃዎችና ፡ መለኪያዎች ፡ እንዲሁም ፡ የቅጣት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቶችን ፡ የሚወስኑ ፡ የመንግሥቱ ፡ ሕግ ፡ አውጭዎች ፡ ናቸው ። ሕግ ፡ አውጭዎቹም ፡ ይህን ፡ ተግባር ፡ በሚፈጽሙበት ፡ ጊዜ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ዕርዳታ ፡ ማቅረባቸው ፡ እንጂ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የተሰጣቸውን ፡ ሥልጣን ፡ መጋፋታቸው ፡ ያለመሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ያምኑበታል ። አንድ ፡ ጠበቃ ፡ ከጥብቅና ፡ ሥራው ፡ የሚወገድባቸው ፡ ምክንያቶች ፡ በሕግ ፡ ተዘርዝረው ፡ ባልተደነገጉበት ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ የጠባይ ፡ ማረሚያ ፡ እርምጃዎች ፡ በመውሰድ ፡ ጠበቃውን ፡ ለጊዜው ፡ ለማገድም ፡ ሆነ ፡ ከሥራው ፡ እንዲሰናበትም ፡ ለማድረግ ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ። ለአንድ ፡ ሰው ፡ የጥብቅና ፡ ሥራ ፡ እንዲሠራ ፡ የሚፈቅድለት ፡ በሀገሩ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለሆነ ፡ ሕግ ፡ አውጪው ፡ ፈቃድ ፡ ለመስጠት ፡ አይችልም ።

የጠበቆች ፡ ማኅበሮች ፡ (እነሱም ፡ ጠበቆች ፡ በግል ፡ ፈቃዳቸው ፡ በሀገሪቷ ፡ ጅኦግራፊ ፡ ወይም ፡ ፖለቲካ ፡ አከፋፈል ፡ መሠረት ፡ የተቋቋሙ ፡ ናቸው) ፡ እየተባሉ፡ የሚጠሩት ፡ ድርጅቶች ፡ ከፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በሚሰጣቸው ፡ ሥልጣንና ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት፡ መሠረት ፡ የጥብቅናውን ፡ ሞያ ፡ ይመሩታል ። የነኝህም ፡ ማህበራዊ ፡ ድርጅቶች ፡ ኮሚቴዎች ፡ በያንዳንዱ ፡ ጠበቃ ፡ ላይ ፡ የሚቀርበውን ፡ ቅሬታና ፡ አቤቱታ ፡ በመቀበል ፡ የሚያስፈልገውን ፡ እርምጃ ፡ በአጥፊው ፡ ጠበቃ ፡ ላይ ፡ ለማስወሰድ ፡ ጉዳዩን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ከማቅረባቸውም ፡ ሌላ ፡ ጠበቃው ፡ ለሥራቸውና ፡ ከሞያው ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ባላቸው ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ ለፈጸማቸው ፡ ወንጀሎች ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጋውያን ፡ በመሆን ፡ ክሱን ፡ ተከታትለው ፡ ከፍጻሜ ፡ ያደርሳሉ ።

በካናዳና ፡ በአውስትራሊያ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ የሕግ ፡ ሞያተኞች ፡ (ጠበቆች) ተግባር ፡ ከአንዳንድ ፡ ጥቃቅን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቶች ፡ በስተቀር ፡ ልምዱ ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ እንደሚሠራው ፡ ስለሆነ ፡ የዚሁኑ ፡ አገር ፡ የጠበቆች ፡ አቋም ፡ መመልከት ፡ በቂ ፡ ነው ።

ሐ/ <u>በሕንድ ፡ አገር ፤</u>

የጥብቅና ፡ ሥራው ፡ ፈቃድ ፡ አሰጣጥ ፡ በየፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይለያያል ። የከፍተኛው ፡ ፍ/ቤት ፡ ጠበቃ ፡ ለመሆን ፡ ፈቃዱ ፡ የሚገኘው ፡ ከዚሁ ፡ ከከፍተኛው ፡ ፍርድ፡ ቤት ፡ ሲሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ፈቃዱን ፡ የሚሰጠው ፡ ከጠበቆቹ ፡ ጠቅላይ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ጋር ፡ ከተመካከረ ፡ በኋላ ፡ ነው ። (ጠቅላይ ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ የተቋቋመው ፡ በሕግ፡ ሲሆን ፡ እያንዳንዱም ፡ ከፍተኛ ፡ ፍ/ቤት ፡ አንዳንድ ፡ የጠበቆች ፡ ጠቅላይ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አለው) ። በጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለሚቆሙት ፡ ጠበቆችም ፡ ፈቃዱ ፡ የሚሰጠው ፡ በዚሁ ፡ በጠቅላይ ፡ ቤቱ ፡ ሲሆን ፤ ይህም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፈቃዱን ፡ የሚሰጠው ፡ ከጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የጠበቆች ፡ ጠቅላይ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ጋር ፡ ከተመካከረ ፡ በኋላ ፡ ነው ። በቀሩት ፡ ዝቅተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ብቻ ፡ በጥብቅና ፡ ለመቆም ፡ ፈቃድ ፡ የሚሰጠው ፡ ያውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኛ ፡ ነው ።

ከጥብቅና ፡ ሥራ ፡ የማገዱም ፡ ተግባር ፡ እንደ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተለያየ ፡ ነው ። በዝቅተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ብቻ ፡ በጥብቅና ፡ የሚቆሙት ፡ ሰዎች ፡ ከሥራቸው ፡ የሚወገዱት ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ ሲሆን ፡ ውሳኔውም ፡ የሚሰጠው ፡ ጉዳዩ ፡ በደንብ ፡ ከተጠናና ፡ የማመሳከሩም ፡ ሁኔታ ፡ ከተከናወነ ፡ በኋላ ፡ ነው ። በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በጥብቅና ፡ የሚቆሙት ፡ ሰዎች ፡ ከሥራቸው ፡ የሚወገዱት፡ በዚሁ ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሲሆን ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጉዳዩን ፡ ከመስማቱ ፡ በፊት ፡ ለጠበቆች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ይልከውና ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ የሚቀርብለትን ፡ የክስ

ማመልከቻ ፡ ተቀብሎ ፣ ምስክሮችን ፡ አስመስክሮና ፡ ሌሎችም ፡ መረጃዎችን ፡ መዝግቦ ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍ/ቤት ያስተላልፈዋል ። ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ከሁለት ፡ ወይም ፡ ከሁለት ፡ ከበለጡ ፡ ዳኞች ፡ የቀረበለትን ፡ መዝገብ ፡ መርምሮና ፡ ከምክር ፡ ቤቱም ፡ የቀረበለትን ፡ ሃሳብ ፡ ተመልክቶ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጥበታል ። ውሳኔውም ፡ በጠቅላይ ፡ ፍ/ቤት ፡ ሊሻር ፣ ሊሻሻል ፡ ወይም ፡ ሊጸድቅ ፡ ይችላል ። በጠቅላይ ፡ ፍ/ቤት ፡ በሚያገለግሉ ፡ ጠበቆችም ፡ ላይ ፡ የሚወሰደው ፡ የቅጣት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ጠበቆች ፡ ላይ ፡ እንደሚወሰድ ፡ ያለ ፡ ነው ።

አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ አንዱ ፡ ጠበቃ ፡ ጠቅላይ ፡ ፍ/ቤትና ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የመነጋገር ፡ ፈቃድ ፡ ይሰጠው ፡ ይሆናል ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚወሰደው ፡ የቅጣት ፡ እርምጃ ፡ በአንደኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ ዋጋ ፡ ሊኖረው ፡ አይችልም ። ቢሆንም ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዘንድ ፡ በልማድ ፡ የሚሠራበት ፤ በተከሰሰው ፡ ጠበቃ ፡ ላይ ፡ ውሳኔውን ፡ ከሰጠ ፡ በኋላ ፡ ይህን ፡ ውሳኔ ፡ ለጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በማስታወቅ ፡ ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ስለሰውየው ፡ በጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ቆሞ ፡ የመነጋገር ፡ መብት ፡ ላይ ፡ የሚወስደው ፡ እርምጃ ፡ እንዳለ ፡ ያስታውሳል ። ጠቅላይ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ ሲታየው ፡ የከፍተኛውን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሪኮርድ (ማስረጃ) ፡ ይወስድና ፡ በተከሰሰው ፡ ጠበቃ ፡ ላይ ፡ የሚቀርብ ፡ ተጨማሪና ፡ ልዩ ፡ መረጃ ፡ ወይም ፡ አቤቱታ ፡ እንዳለ ፡ በመቀበል ፡ ጉዳዩን ፡ ተመልክቶ ፡ አስፈላጊውን ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጣል ።

እስካሁን ፡ ድረስ ፡ በተወሰዱት ፡ እርምጃዎች ፡ በሁለቱ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ መካከል ፡ የውሳኔ ፡ መጋጨት ፡ ደርሶ ፡ አያውቅም ፤ ይህም ፡ ሊሆን ፡ የቻለው ፡ ምናልባት ፡ በጠበቃው ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ የሚነሳው ፡ በከባድ ፡ ጥፋት ፡ ብቻ ፡ ስለሚሆን ፡ ይሆናል ። በመሠረቱ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሚሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ የይግባኝ ፡ መብት ፡ ስለሌለና ፡ የጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፴፮ ፡ በተሠጠው ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ ጉዳዩን ፡ ለማየት ፡ ወይም ፡ ላለማየት ፡ ዳኞች ፡ በሕሊና ፡ ግምታቸው ፡ ስለሚመሩ ፤ ጠበቃው ፡ በአንዱ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተከልክሎ ፡ በሌላው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲሠራ ፡ ሲደረግ ፡ በሰዎች ፡ ላይ ፡ መጥፎ ፡ ግምትን ፡ ይፈጥራል ፡ ተብሎ ፡ ይታመንበታል ። ስለዚህ ፡ ይህን ፡ ዓይነቱን ፡ ችግር ፡ ለማቃለል ፡ «የሕንድ ፡ ጠቅላላ ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር» የሚባል ፡ ድርጅት ፡ መቋቋም ፡ እንደሚያስፈልግና ፡ ጉዳዩም ፡ የታሰበበት ፡ መሆኑ ፡ ታውቋል ።

መ/ <u>በፈረንሳይ ፡ አገር ፤</u>

ያሉት ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበሮች ፡ በየግዛቱ ፡ የተለያዩና ፡ ራሳቸውን ፡ የቻሉ ፡ ሲሆኑ ፡ እያንዳንዳቸውም ፡ ከይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ያላቸው ፡ ናቸው ። እያንዳንዱም ፡ ማህበር ፡ በማኅበርተኝነት ፡ በተመዘገቡት ፡ አባሎች ፡ ላይ ፡ የአስተዳደርና ፡ የቅጣት ፡ ሥልጣን ፡ አለው ። ይህም ፡ ስልጣኑ ፡ በይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተቆጣጣሪነት ፡ የሚካሄድ ፡ ነው ። በልዩ ፡ ልዩ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ማለት ፡ በኩርደ ፡ ካስሲዮን ፤ በኮንሲል ፡ ዴታ ፡ እና ፡ በትሪቡናል ፡ ዴ ፡ ኩንፍሊ ፡ የሚቆሙ ፡ ጠበቆች ፡ ግን ፡ የተወሰኑ ፡ አባሎችን ፡ የያዘ ፡ ልዩ ፡ ማኅበር ፡ አላቸው ። በነኚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችም ፡ የሚያገለግሉ ፡ ጠበቆች ፡ ምትኬቻቸውን ፡ በእጩነት ፡ ለማቅረብ ፡ መብት ፡ ሲኖራቸው ፡ እጩዎቹም ፡ ሥራቸውን ፡ የሚጀምሩት ፡ የሀገሪቷ ፕሬዚዳንት ፡ ሲፈቅዱላቸው ፡ ነው ። ከነዚህ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ማኅበሮች ፡ ሌላ ፡ ብሔራዊ የጠበቆች ፡ ማኅበሮች ፡ አሉ ። እነኚህም ፡ ማህበሮች ፡ ምንም ፡ ሕጋዊ ፡ ሥልጣን ፡ ባይ

ኖራቸውም ፡ እንኳን ፡ ከሞያው ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ባላቸው ፡ አንዳንድ ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ፡
ተካፋይ ፡ ይሆናሉ ።

ሠ/ <u>በጀርመን ፡ አገር ፤</u>

እንደ ፡ ፈረንሣይ ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ በየግዛቱ ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበሮች ፡ አሉ ። እነዚ
ህም ፡ ማኅበሮች ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ በሕግ ፡ የተወሰኑ ፡ ባይሆኑም ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ሥል
ጣን ፡ አላቸው ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ለጠበቆች ፡ የጥብቅና ፡ ፈቃድ ፡ የመሠጠቱና ፡ የመከል
ከሉ ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ <u>ለየቦታው ፡</u> ፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ቅርንጫፍ ፡ ነው ።
የማኅበርተኞቹ ፡ የውስጥ ፡ አስተዳደርና ፡ የሥራ ፡ እርምጃ ፡ የሚካሄደው ፡ ግን ፡ በጠበቆ
ች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ እና ፡ ይኸው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ባቋቋመው ፡ በጠባይ ፡ አራሚ ፡ ዳኞች፡
ነው ። በልዩ ፡ ልዩ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ቆሞ ፡ የመነጋገሩ ፡ ፈቃድ ፡ ከማኅበሩ ፡ አባልነት፡
የተለየ ፡ ነገር ፡ በመሆኑ ፤ ለፈቃዱ ፡ ማመልከቻዎችን ፡ አግብቶ ፡ መጠየቅ ፡ ግድ ፡
ይሆናል ። የፈቃዱም ፡ አሰጣጥ ፡ መለኪያ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ደረጃዎችና ፡ መመዘኛዎች ፡
ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ።

ረ/ <u>በስዊድን ፡ አገር ፤</u>

በስዊድን ፡ አገር ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በዕድሜው ፡ ጠና ፡ ብሎ ፤ በጠባዩም ፡
ጥሩ ፡ ሆኖ ፡ እነዚህንና ፡ እነዚህን ፡ የመሰሉትን ፡ ሌሎች ፡ መሠረታዊ ፡ ነገሮች ፡
ፈጽሞ ፡ የተገኘ ፡ እንደሆነ ፡ በጥብቅና ፡ ቆሞ ፡ ሊሠራ ፡ ይችላል ። ስለዚህ ፡ በተለይ ፡
የሕግ ፡ ሰዎች ፡ በመባል ፡ የሕግን ፡ ተግባር ፡ የሚያከናውኑ ፡ ሰዎች ፡ በስዊድን ፡ ው
ስጥ ፡ የሉም ። የሆነው ፡ ሆኖ ፡ በጥብቅና ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩት ፡ አብዛኞቹ ፡ የሕግ ፡
ትምህርት ፡ ያላቸው ፡ ናቸው ። ደንበኛውን ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ የተከታተሉትን ፡
ባለሞያዎች ፡ የያዘ ፡ ማኅበር ፡ አለ ። ይህ ፡ ማኅበር ፡ ምንም ፡ እንኳን የግል ፡ ማኅበር
ቢሆንም ፡ መንግሥቱ ፡ በመጠኑ ፡ ይቆጣጠረዋል ። ለምሳሌ ፡ የማኅበሩ ፡ ያስተዳደር ፡
ደንብ ፡ በመንግሥቱ ፡ መፈቀድ ፡ አለበት ። የማኅበሩንም ፡ አባሎች ፡ የሚመለከቱ ፡
አንቀጾች ፡ በዳኝነት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ይገኛሉ ። በዚህም ፡ የጠበቆች ፡
ማኅበር ፡ ስም ፡ ሌሎቹ ፡ የሕግ ፡ ሊቃውንትና ፡ የማኅበሩ ፡ አባል ፡ ሳይሆኑ ፡ በጥብቅና ፡
ለመቆም ፡ የሚችሉ ፡ ሰዎች ፡ ሊጠቀሙበት ፡ አይችሉም ። በሥነ ፡ ሥርዓቱም ፡ ሕግ
መሠረት ፡ የማኅበሩ ፡ አባል ፡ ሊሆኑ ፡ የሚችሉት ፡ ዕድሜያቸው ፡ ከ፳፫ ፡ ዓመት ፡
በላይ ፡ ሆኖ ፡ ተገቢው ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ያላቸውና ፡ በማህበሩም ፡ የውስጥ ፡ ደንብ ፡
መሠረት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ልምምድ ፡ ያደረጉ ፤ ታማኝነት ፡ ያላቸውና ፡ የስዊድን ፡
አገር ፡ ዜጋ ፡ የሆኑ ፡ ስዊድናውያን ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። የአባልነት ፡ ማመልከቻቸው ፡
የሚመረመረው ፡ በማኅበሩ ፡ የአስተዳደር ፡ ቦርድ ፡ ነው ። የማኅበሩም ፡ አባል ፡ በጠ
ባዩ ፡ የሚፈለግበትን ፡ ግዴታ ፡ ሳይፈጽም ፡ የተገኘ ፡ እንደሆነ ፡ ቦርዱ ፡ ከአባልነት ፡
ሊያስወጣው ፡ ይችላል ። በተጨማሪም ፡ ጠበቃው ፡ አገልግሎቱን ፡ በየፍርድ ፡ ቤቶች
በሚያበረክትበትም ፡ ጊዜ ፡ ሆነ ፡ በሌሎች ፡ ተግባሮች ፡ ሁሉ ፡ የተሰጠውን ፡ አደራ ፡
የሚጠብቅ ፡ መሆኑን ፡ ቦርድ ፡ ይከታተለዋል ። ሥራውን ፡ በትክክል ፡ ሳይፈጽም ፡ የቀ
ረው ፡ የማኅበሩ ፡ አባል ፡ ጠበቃ ፡ ተገቢው ፡ እርምጃ ፡ እንዲወሰድበት ፡ የጠቅላይ
አቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ሹም ፡ ለቦርድ ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችላል ። ቦርዱ ፡ ከማኅበሩ ፡ ላለማስገባ
ትም ፡ ሆነ ፡ ከማኅበሩ ፡ ለማስወጣት ፡ በሚወስደው ፡ እርምጃ ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ ለጠቅላይ
ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ ሊባል ፡ ይቻላል ።

ሰ/ በአንዳንድ አገሮች ፤

ለምሳሌ ፡ በኢራን ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ የሚተዳደረው ፡ በመጠኑ ፡ በፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ነው ። በጃፓን ፡ አገር ፡ ይህ ፡ ዓይነቱ ፡ ድርጊት ፡ በፍርድ ሚኒስቴሩ ፡ ቁጥጥር ፡ ሲሠራበት ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ዓይነቱ ፡ ድርጊት ፡ ቀርቶ ፡ ድርጅቱ ፡ የሚካሄደው ፡ በጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ በሚካሄደው ፡ በጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ ብቻ ፡ ነው ። በተጨማሪም ፡ በዚሁ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ጠበቆች ፡ በሕብረተ ፡ ሰቡ ፡ ዘንድ ፡ ያላቸው ፡ ቦታ ፡ እንደሌሎቹ ፡ አገሮች ፡ ጠበቆች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ እንዲሆን ፡ ጥረት ፡ በመደረግ ፡ ላይ ፡ ነው ።

ሸ/ በሶቪየት ፡ ሩሲያ ፡ ውስጥ ፤

የጥብቅና ፡ ሥራ ፡ በአንድነት ፡ የተጠቃለለ ፡ ሆኖ ፡ የሞያውም ፡ ቁጥጥር ፡ የሚካሄደው ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሳይሆን ፡ በፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ነው ። የጥብቅና ፡ ሥራ ፡ ያለ ፡ ምንም ፡ መለኪያ ፡ ወይም ፡ ፈተና ፡ ለማንም ፡ ሰው ፡ በፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ የሚፈቀድ ፡ ቢሆንም ፡ ቅሉ ፡ በተለይ ፡ የሕግ ፡ ሰዎች ፡ የጠበቆች ፡ ማህበር ፡ አባሎች ፡ መሆን ፡ አለባቸው ። በዚሁ ፡ በአንድነት ፡ አቋም ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ ጠበቆች ፡ የሚከራከሩባቸውን ፡ ጉዳዮች ፡ የሚወስዱት ፡ በአቋሙ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ደልዳይነት ፡ ነው። የሁንጋሪ ፡ የጠበቆች ፡ ድርጅት ፡ በቅርቡ ፡ በሩስያ ፡ የጠበቆች ፡ አቋም ፡ መሠረት ፡ እንዲመራ ፡ ተደርጓል ። በዩጐዝላቪያ ፡ ግን ፡ ጠበቆች ፡ በአንድነት ፡ አቋም ፡ እንዲሠሩ ፡ አይገደዱም ። በፖላንድ ፡ በየጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ የተመሠረቱ ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበሮችና ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ የጠበቆች ፡ ጠቅላይ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አለ ።

በኢትዮጵያ ፡-

በኢትዮጵያ ፡ የጥብቅና ፡ ፈቃድ ፡ መስጠቱን ፡ እንዲሁም ፡ በጠበቃው ፡ ላይ ፡ የሚቀርብበትን ፡ የቅሬታ ፡ ክስ ፡ ተቀብሎ ፡ የመመርመርና ፡ የማገዱ ፡ ሥልጣን ፡ በ፲፱፻፴፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በወጣው ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፳ ፡ መሠረት ፡ የተሰጠው ፡ ለፍርድ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ነው ። በዚህም ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ስለ ፡ ፈቃዱ ፡ አሰጣጥና ፡ ጠበቃውም ፡ ሊታገድ ፡ የሚችልበትን ፡ ሁኔታ በሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፳፮/፲፱፻፵፬ ፡ አውጥቷል ።

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ የጥብቅና ፡ ፈቃድ ፡ እንዲሰጠው ፡ በጠየቀ ፡ ጊዜ ፡ አመልካቹ ፡ አድራሻውንና ፡ የሕይወት ፡ ታሪኩን ፡ የሚገልጽ ፡ ማመልከቻ ፡ ፎርም ፡ እንዲሞላና ፡ ፫ ፡ ጉርድ ፡ ፎቶግራፍ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ ጠባዩ ፡ በምሥጢር ፡ ተጣርቶ ፡ እንዲላክ ፡ ከአራት ፡ ፎቶግራፎች ፡ ጋር ፡ ለክፍሉ ፡ አውራጃ ፡ ግዛት ፡ ይጻፋል ። የክፍሉም ፡ አውራጃ ፡ ግዛት ፡ ለወረዳው ፡ ግዛትና ፡ ለወንጀል ፡ ምርመራ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ አጣርተው ፡ እንዲልኩ ፡ ትዕዛዝ ፡ ያስተላልፋል ።

ስለአመልካቹ ፡ ሁኔታ ፡ ከአውራጃው ፡ ግዛት ፡ የሚተላለፈው ፡ ደብዳቤ ፡ አመልካቹ ፡ በሚኖርበት ፡ ሠፈር ፡ ጠባዩ ፡ መልካም ፡ ስለመሆኑ ፡ የተመሰከረለት ፡ እንደሆነና ፡ በወንጀል ፡ ምርመራ ፡ በኩል ፡ በወንጀል ፡ ነገር ፡ የተመዘገበበት ፡ ጥፋት ፡ የሌለ መሆኑ ፡ ከተረጋገጠ ፡ በኋላ ፡ ለፈተና ፡ ይመዘገባል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አመልካቹ ፡ በሕግ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ችሎታ ፡ ለመመርመር ፡ ፈተና ፡ እንዲወስድ ፡ ይደረግና ፡ ፈተናውን ፡ ያለፈ ፡ እንደሆነ ፡ በፈተና ፡ ውጤቱ ፡ መሠረት ፡ የመመዝገቢያና ፡ የዓመት ፡ ግብሩን ፡ ከፍሎ ፡ ፈቃዱ ፡ ይሰጠዋል ። ከዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ዲግሪ ፡ በማቅረብ ፡ የጥብቅና ፡ ፈቃድ ፡ እንዲሰጠው ፡ ለሚጠይቅ ፡ አመልካች ፡ ግን ፡ ያለፈተና ፡ ፈቃዱን ፡ ሊወስድ ፡

ይችላል ። ይህ ፡ የሚደረግበት ፡ ምክንያት ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፳፯/፩፲፱፻፵፬ ፡ የጥብቅና ፡ ፈቃድ ፡ የሚጠይቅ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሁለት ፡ ነገሮች ፡ አሟልቶ ፡ መያዝ ፡ ስለአለበት ፡ ነው ። እነርሱም ፡ አንደኛ ፡ አመልካቹ ፡ የጥብቅና ፡ ሥራውን ፡ በሚገባ ፡ ለመሥራት ፡ የሚያስችለው ፡ ትምህርትና ፡ ዕውቀት ፡ ያለው ፡ መሆን ፡ አለበት ። ሁለተኛ ፡ ደንበኛውን ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ለመርዳት ፡ የተስማማ ፡ ጠባይ ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ሲያረጋግጥ ፡ ፈቃድ ፡ የሚሰጠው ፡ መሆኑን ፡ ስለሚደነግግ ፡ ነው ።

በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ የጥብቅና ፡ ፈቃድ ፡ ሊሰጠው ፡ ይገባል ፡ ተብሎ ፡ የተፈቀደለት ፡ ሰው ፡ የጥብቅና ፡ ፈቃድን ፡ ያገኘና ፡ ቢሮም ፡ ይከፍታል ፤ ደንበኛም ፡ ይመጣለታል ፤ ፋይሎችንም ፡ በቦርሳ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በመሄድ ፡ ካባ ፡ ለብሶ ፡ ችሎት ፡ መቆም ፡ ይጀምራል ። ካባም ፡ የትልቅ ፡ ክብር ፡ ምልክት ፡ በመሆኑ ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ አይለብስም ፤ ለምሳሌ ፡ የዳኝነት ፡ መልክ ፡ ወይም ፡ ጠባይ ፡ ባለው ፡ ቦርድ ፤ ፖሊስ ፡ ጣቢያ ፡ ገላጋይ ፡ ሽማግሌዎች ፤ በሚገኙበት ፡ ሽንጐ ፡ ፊት ፡ ሲቀርብ ፡ ካባ ፡ አይለብስም ፤ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተለየ ፡ ክብር ፡ ያለው ፡ በመሆኑ ፡ ግን ፡ ዳኞች ፤ ጠበቆችም ፡ በችሎት ፡ ጊዜ ፡ ካባ ፡ ይለብሳሉ ። ካባ ፡ መልበስም ፡ ሆነ ፡ ከአንዱ ፡ ችሎታ ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ መራወጡ ፡ ብቻ ፡ አይበቃም ። ጠበቃ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ኃላፊነትና ፡ ግዴታዎችን ፡ ማክበር ፡ እንደሚገባው ፡ ማወቅ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ሕጉ ፡ የጥብቅና ፡ ፈቃድ ፡ የሚሰጠው ፡ ሰው ፡ ደንበኛውን ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ለመርዳት ፡ የተስማማ ፡ ጠባይ ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ሚኒስትሩ ፡ ወይም ፡ ሚኒስቴሩ ፡ ሥልጣን ፡ የሰጠው ፡ ሰው የተረዳው ፡ እንደሆነ ፡ ስሙ ፡ በመዝገቡ ፡ እንዲመዘገብ ፡ ይፈቅድለታል ፡ ስለሚል ፡ በጠበቃው ፡ ላይ ፡ ከፍተኛ ፡ ኃላፊነት ፡ የተጣለበት ፡ ለመሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ እንደማናቸውም ፡ ተራ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የደንበኛው ፡ ወኪልና ነገረፈጅ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ ጭምር ፡ ነው ። ጠበቆች ፡ የሚጣልባቸውን ፡ እምነት ፡ ለመረዳት ፡ ያህል ፡ በአሥመራ ፡ የሚደረገውን ፡ ሁኔታ ፡ ምሳሌ ፡ ማድረግ ፡ ይቻላል ። ለምሳሌ ፡ በአሥመራ ፡ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ ሬጅስትራሩ ፡ ቢሮ ፡ ወይም ፡ መዝገብ ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ የፈለገውን ፡ ፋይል ፡ አገላብጦና ፡ ከአንዱ ፡ ችሎት ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ተላላኪ ፡ ሳያስፈልግ ፡ መዝገቡን ፡ ራሱ ፡ ይዞ ፡ ለመሄድ ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ ደንበኛውን ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ሶስተኛ ፡ ወገን ፡ የሚጐዳውን ፡ ማስረጃ ፡ ከውስጡ ፡ ያወጣል ፡ ተብሎ ፡ ስለሚገመት ፡ በራሱ ፡ ኃላፊነት ፡ ብቻ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ፈጽሞ ፡ አይሰጠውም ።

በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የሞያ ፡ ሥነ ፡ ምግባር ፡ ደንብ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ባለመውጣቱ ፡ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ አድራጐቱ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ የሞያውን ፡ ሥነ ፡ ምግባር ፡ ደንብ ፡ እንደሚጻረር ፡ አያውቅ ፡ ይሆናል ። ይሁንና ፡ ጠበቆች ፡ ሁሉ ፡ ለጥብቅና ፡ የተለየ ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ምግባር ፡ እንዳለው ፡ ያውቃሉ ። ለሕግ ፡ ሥነ ፡ ምግባር ፡ አጥጋቢ ፡ ትርጉም ፡ ለመስጠት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ። ጠበቃ ፡ በሕግ ፡ ሞያው ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ እንዳለበትና ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ እንደማይገባው ፡ በመተንተንና ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ለማድረግ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ፤ ጠበቆች ፡ ከሕግ ፡ ሥነ ፡ ምግባር ፡ ውጪ ፡ የሆኑ ፡ አድራጐት ፡ በየጊዜው ፡ እንደሚፈጽሙ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። የሕግ ፡ ሥነ ፡ ምግባር ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ በአገራችን ፡ አይከበርም ፡ ቢባል ፡ ስሕተት ፡ አይሆንም ። አብዛኛዎቹ ፡ ጠበቆች ፡ የሚመለከቱት ፡ የዕለት ፡ ጥቅማቸውን ፡ በመሆኑ ፡ ጥብቅናን ፡ ሞያ ፡ አድርገው ፡ ከመቁጠር ፡ ይልቅ ፡ እንደ ፡ ንግድ ፡ ይቆጥሩታል ። ይህ ፡ አስተሳሰብ ፡ ፈጽሞ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። አንድ ፡ ጠበቃ ፡ ለዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ይረዳል ፡ ተብሎ ፡ ፈቃድ ፡ ሲሰጠው ፡ መንግሥት ፡ ከተራው ፡ ሕዝብ ፡ የተለየ ፡ ኃላፊነት ፡ የተጣለበት ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣን ፡ አድርጐታል ፡ ማለት ፡ ነው ። ጠበቃ ፡ ለመንግሥት ፤ ለፍርድ ፡ ቤት ፤

ለደንበኛውና ፡ ለሌላው ፡ መሰል ፡ ጠበቃው ፡ ያለበት ፡ ግዴታና ፡ ኃላፊነት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደሚከበር ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ እንመልከት ።

## ጠበቃው ፡ ለመንግሥቱና ፡ ለሕዝቡ ፡ ያለው ፡ ግዴታ ።

አርኪን ፡ «ሊጋል ፡ ኤቲክስ» ፡ በተባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ አስተያየቱን ፡ ሲሰጥ ፡ ጠበቃው ፡ የሕግ ፡ ባለሥልጣን ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ የመንግሥቱን ፡ አቋምና ፡ የሀገሩን ፡ ሕግ ፡ ለማክበር ፡ ከተራው ፡ ሕዝብ ፡ የተለየ ፡ ኃላፊነት ፡ አለበት ። ይህንንም ፡ ኃላፊነቱን ፡ ለመፈጸም ፡ በመሃላ ፡ ቃል ፡ ግዴታ ፡ መግባት ፡ ይኖርበታል ። ይህን ፡ ኃላፊነቱን ፡ ይፈጽማል ፡ ተብሎ ፡ እምነት ፡ ያልተጣለበት ፡ ማንኛውም ፡ የሕግ ፡ አዋቂ ፡ የጥብቅና ፡ ሥራ ፡ እንዲሠራ ፡ የሚከለከልበት ፡ ጊዜ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ይኖራል ።

የሕግ ፡ ጠበቃ ፡ ተግባር ፡ እራሱ ፡ የመንግሥቱን ፡ አቋምና ፡ የሀገሪቱን ፡ ሕግ ፡ መጠበቅ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ደንበኞቹም ፡ ሕግ ፡ እንዲጥሱ ፡ መምከር ፡ ወይም ፡ ሕግ ፡ ሲጥሱ ፡ ዝም፡ ብሎ ፡ ማየት ፡ የለበትም ። ደንበኞቹ ፡ ሕግ፡ እንዲጥሱ ፡ ከመከረ ፡ ወይም ፡ ሕግ ፡ ሲጥሱ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ካየ ፡ ሕጉን ፡ እራሱ ፡ እንደጣሰ ፡ ይቆጠርበታል ። ስለዚህ ፡ በቀጥታም ፡ ሆነ ፡ በተዘዋዋሪ ፡ መንገድ ፡ ሕጉ ፡ እንዳይጣስ ፡ ወይም ፡ እንዳይዛባ ፡ ማድረግ ፡ የጠበቃው ፡ የመጀመሪያ ፡ ተግባሩ ፡ ነው ።

በኢትዮጵያም ፡ ውስጥ ፡ የሕግ ፡ ጠበቆች ፡ ሕጉን ፡ ማክበርና ፡ ማስከበር ፡ ተግባራቸው ፡ መሆኑን ፡ እንደሚያውቁት ፡ አያጠራጥርም ። ከአንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ እንደሚሰማው ፡ ግን ፡ አንዳንድ ፡ ጠበቆች ፡ በተለይም ፡ በቂ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ሳይኖራቸው ፡ በዝቅተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በጥብቅና ፡ የሚቆሙት ፤ ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ ብቻ ፡ በመሆኑ ፡ ያላመኑበትን ፡ ወይም ፡ ሕጋዊ ፡ ሆኖ ፡ ያልተገኘውን ፡ ነገር ፡ ሕጋዊ ፡ ነው ፡ በማለትና ፡ በማስመሰል ፡ ደንበኞቻቸውን ፡ ሕግ ፡ እንዲጥሱ ፡ ወይም ፡ ሌላውን ፡ እንዲጎዱ ፡ ያደርጋሉ ። ስለዚህ ፡ ለእንደዚህ ፡ ያሉት ፡ ጠበቆች ፡ የሚያስፈልገው ፡ ትምህርት ፡ የሚሰጥበት ፡ ዘዴ ፡ ቢፈለግና ፡ እንዲሁም ፡ አንዳንድ ፡ ቋሚ ፡ ሕጎች ፡ (የሕግ ፡ ሥነ ፡ ምግባር) ፡ ወጥተው ፡ ጥፋት ፡ ሲያደርግ ፡ በሚገኘው ፡ ጠበቃ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ እርምጃ ፡ ቢወሰድበት ፡ መልካም ፡ ይሆናል ።

እናንድ ፡ የተባለውም ፡ ደራሲ ፡ «ጀኔራል ፡ ፕሪንስፕልስ ፡ ኦፍ ፡ ሌጋል ፡ ኤቲክስ» በተባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ጠበቃው ፡ ለሕዝቡና ፡ ለመንግሥቱ ፡ ያለውን ፡ ግዴታ ሲገልጽ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ።

እያንዳንዱ ፡ ጠበቃ ፡ ወይም ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ ሕዝቡን ፡ ለማገልገል ፡ ከተወሰኑት ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ ድርጅቶች ፡ አንዱ ፡ ነው ። ጠበቃው ፡ ወይም ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ ለሕዝቡ ፡ ካሉበት ፡ ግዴታዎች ፡ ጥቂቶቹን ፡ ለመጥቀስ ፤

፩/ የሕግ ፡ ልዕልናና ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ እንዲጠበቅ ፡ ወይም ፡ <u>እንዲከበር ፡ ማድረግ</u> ። በማናቸውም ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ሕግ ፡ መውጣቱ ፡ ብቻ ፡ በቂ ፡ አይደለም ። ሕጉ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውልና ፡ የታቀደውንም ፡ ዓላማ ፡ ከግቡ ፡ እንዲደርስ ፡ መደረግ ፡ አለበት ። ይህንንም ፡ ዓላማ ፡ ከግቡ ፡ ለማድረስ ፡ የተወሰኑ ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ ድርጅቶች ፡ እንዲኖሩ ፡ ያስፈልጋል ። ሊኖሩም ፡ ከሚገቡት ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ ድርጅቶች ፡ አንዱ ፤ ጠበቆች ፡ ወይም ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ ነው ።

ሕግ ፡ በሕግነቱ ፡ ብቻ ፡ ፍትሕነት ፡ ሊኖረው ፡ አይችልም ፤ በገዛ ፡ ራሱም ፡ ሊከበር ፡ አይችልም ። ፍትሕነት ፡ እንዲኖረው ፤ እንዲከበርና ፡ እንዲሠራበት ፡ መደረግ ፡

አለበት ። ሕግ ፡ ከተከበረና ፡ በትክክለኛው ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ከዋለ ፡ ለአንድ ፡ ሀገር ፡ ሕዝብ ፡ የኑሮ ፡ ደረጃ ፡ ማደግና ፡ የሥልጣኔ ፡ መገሥገሥ ፡ መፍትሔው ፡ ይሆናል ። ሕግ ፡ ይህን ፡ ጠቃሚ ፡ ተግባሩን ፡ እንዲፈጽም ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ መጣጣር ፡ የያንዳንዱ ፡ ጠበቃ ፡ ወይም ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ ድርጅት ፡ የመጀመሪያው ፡ ተግባር ፡ ነው ። ጠበቃው ፡ ይህን ፡ ተግባሩን ፡ ሲፈጽም ፡ ለሕዝቡ ፡ ያለውን ፡ የመጀመሪያውን፡ ተግባሩን ፡ ፈጸመ ፡ ማለት ፡ ነው ።

፪/ በሀሰትና ፡ በማጭበርበር ፡ ላይ ፡ የተመሠረቱ ፡ ክሶች ፡ <u>እንዳይኖሩ ፡ ማድረግ ።</u>

ጠበቃው ፡ ሊፈጽማቸው ፡ ከሚገቡት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ነገሮች ፡ አንዱ ፡ በሕብረተሰቡ ፡ ዘንድ ፡ ሰላምና ፡ ስምምነት ፡ እንዲኖር ፡ ማድረግ ፡ ነው ። ይህም ፡ ማለት ፡ ጠበቆች ፡ ገንዘብ ፡ ፈላጊዎች ፡ በመሆናቸው ፡ ሁልጊዜ ፡ ጭቅጭቅ ፡ እንዲኖር ፡ ይጣጣራሉ ፡ ተብሎ ፡ የሚነገረው ፡ ሀሰት ፡ ወሬ ፡ ሆኖ ፡ እንዲቀርና ፡ በእርግጥ ፡ ስምምነት ፡ እንዲኖር ፡ ጠበቆች ፡ ሁልጊዜ ፡ የሚታገሉ ፡ መሆናቸውን ፡ ማሳየት ፡ አለባቸው ማለት ፡ ነው ።

ይህ ፡ ተግባር ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ጠበቆች ፡ ሊፈጸም ፡ የሚገባው ፡ ነው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የማዋሉ ፡ ተግባር ፡ ትንሽ ፡ አስቸጋሪ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። ምክንያቱም ፡ አንዱ ፡ ባለጉዳይ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ጠበቃ ፡ ሄዶ ፡ ለጉዳዩ ፡ ጥብቅና ፡ እንዲቆምለት ፡ ሲጠይቀውና ፡ ጠበቃው ፡ ጉዳዩ ፡ የማያዋጣ ፡ መሆኑን ፡ በመረዳት ፡ ወይም ፡ በቀላሉ ፡ በሽምግልና ፡ ሊያልቅ ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ በመገንዘብ ፡ ለባለጉዳዩ ፡ ይህን ፡ አስተያየት ፡ የገለጸለት ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ እራሱ ፡ በሽምግልና ፡ ሊጨርስለት ፡ የፈለገ ፡ እንደሆነ ፡ ባለጉዳዩ ፡ ጠበቃው ፡ ምንም ፡ አገልግሎት ፡ እንደፈጸመለት ፡ ሳይቆጥር ፡ በነፃ ፡ ምክሩን ፡ ወይም ፡ ሽምግልናውን ፡ ተቀብሎ ፡ ስለሚሄድ ፡ ነው ። በሀገሩም ፡ ባህል ፡ መሠረት ፡ ለሽምግልና ፡ የተቀመጠ ፡ ሰው ፡ ምንም ፡ ዋጋ ፡ የማይጠይቅ ፡ በመሆኑ ፡ ጠበቃው ፡ ለሽምግልናው ፡ ዋጋ ፡ ለመጠየቅ ፡ ሕፍረት ፡ ይይዘውና ፡ በነፃ ፡ አገልግሎቱን ፡ ይሰጣል ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ የነፃው ፡ ውለታ ፡ ሲበዛበት ፡ የማያዋጣውን ፡ ነገር ፡ ያዋጣል ፡ በማለት ፤ በሽምግልና ፡ ሊያልቅ ፡ የሚገባውንም ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይሂድ ፡ በማለት ፡ ጭቅጭቅ ፡ እንዲፈጠር ፡ ሊያደርግ ፡ ይችል ፡ ይሆናል ።

ስለዚህ ፡ በሌሎች ፡ የውጭ ፡ አገሮች ፡ እንደሚደረገው ፡ ሁሉ ፡ ጠበቃው ፡ በሀሰትና ፡ በጭቅጭቅ ፡ ላይ ፡ የሚመሠረቱ ፡ ክሶች ፡ ቀርተው ፡ በሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡ ሰላምና ፡ ስምምነት ፡ እንዲኖር ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ለባለጉዳዮቹ ፡ ለሚሰጠው ፡ ምክርና ፡ አስተያየት ፡ ሁሉ ፡ በሰዓት ፡ እየታሰበ ፡ እንዲከፈለው ፡ የሚደረግበት ፡ ዘዴ ፡ ቢፈለግ ፡ ይህን ፡ የተጠቀሰውን፡ መልካም ፡ ተግባር፡ በሥራ ፡ ላይ፡ ለማዋል ፡ የሚቻል፡ ይመስላል ።

፫/ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በድህነት ፡ ምክንያት ፡ ሕጋዊ ፡ መብቱ ፡ <u>እንዳይነፈገው ማድረግ ።</u>

ጠበቃው ፡ የሕግ ፡ ባለሥልጣን ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፤ በሀብታምና ፡ በደሀ ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ ሳይፈጠር ፡ ትክክለኛው ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ማድረግ ፡ አለበት ። ጠበቃው ፡ በገንዘብ ፡ ብቻ ፡ የሚገኝ ፡ ከሆነ ፡ ግን ፤ ገንዘብ ፡ የሌለው ፡ ለመግዛት ፡ በማይችልበት ፡ ጊዜ ፡ ለመብቱ ፡ የሚከራከርለት ፡ ጠበቃ ፡ በማጣት ፡ መብቱን ፡ ሊነፈግ ፡ ይችላል ።

ስለዚህ ፡ ደሀው ፡ ገንዘብ ፡ በማጣት ፡ መብቱን ፡ እንዳይነፈግ ፡ ጠበቃው ፡ በነፃ ፡ መቆምና ፡ መነጋገር ፡ ከተግባሮቹ ፡ አንዱ ፡ ነው ። ይህም ፡ ነፃ ፡ አገልግሎት ፡ ለወንጀል ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለፍትሐብሔርም ፡ ጉዳይ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።

እርግጥ ፡ የደሀው ፡ መብት ፡ እንዲጠበቅ ፡ ማድረግ ፡ የመንግሥቱ ፡ ቀዳሚ ፡ ተግባር ፡ ነው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ መንግሥቱ ፡ ነፃ ፡ አገልግሎቱን ፡ ለሁሉም ፡ ለማዳረስ ፡ በማይሳነው ፡ ጊዜ ፡ ጠበቆች ፡ ወይም ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ ይህን ፡ የተጠቀሰውን ፡ የነፃ ፡ አገልግሎት ፡ ለደሀው ፡ ማበርከት ፡ ለሕዝቡና ፡ ለመንግሥቱ ፡ ካላቸው ፡ ግዴታ ፡ አንዱ ፡ መሆን ፡ አለበት ።

በኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፶፪ ፡ መሠረት ፡ «በወንጀል ፡ ክሶች ፡ ሁሉ ...ተከሳሹ ፡ በራሱ ፡ ችሎታ ፡ ወይም ፡ በገንዘቡ ፡ ጠበቃ ፡ ለመግዛት ፡ ያልቻለ እንደሆነ ፡ በሚወሰነው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጠበቃ ፡ ያቆምለታል» ። ለማሳሰብ ፡ ያሀል ፡ በሚወሰነው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የተባለው ፡ ሐረግ ፡ በእንግሊዝኛው ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የለም ። እንግሊዝኛው ፡ በቀጥታ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጠበቃ ፡ ያቆምለታል፡ ይላል ። የአማርኛው፡ እላይ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ሐረግ፡ ይዟል ። ያማርኛውን ፡ የተከተልን ፡ እንደሆነ ፡ ስለጠበቆች ፡ አቋቋምም ፡ ሆነ ፡ ስለአከፋፈላቸው ፡ ለጊዜው ፡ የተወሰነ ፡ ሕግ ፡ የለም ።

እስከ ፡ ፶፱ ፡ ዓ.ም. ድረስ ፡ በልማድ ፡ ሲሠራበት ፡ የቆየው ፡ ፍርድ፡ ቤቶች ፡ በመሰላቸው ፡ አንዱን ፡ ጠበቃ ፡ እንዲነጋገር ፡ በማዘዝ ፡ ነበር ። አሠራሩ ፡ በመሰለ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ በአንድ ፡ ችሎት ፡ ውስጥ ፡ በነፃ ፡ እንዲቆም ፡ ተደጋግሞ ፡ ለመታዘዝ ፡ ከመቻሉም ፡ ሌላ ፡ ይኸው ፡ አንዱ ፡ ጠበቃ ፡ በሌሎች ፡ ችሎቶች ፡ እንደዚሁ ፡ ሊታዘዝ ፡ ይችላል ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ አንዳንድ ፡ ጠበቆች ፡ በነፃ ፡ እንዲቆሙ ፡ በሚታዘዙበት ፡ ጊዜ ፡ ሌላው ፡ ችሎት ፡ ታዘናል ፡ በማለት ፡ የሚያጭበረብሩም ፡ አይጠፉም። በጠቅላላው ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጠበቃ ፡ የማቆሙ ፡ ተግባር ፡ በደንብ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ያልያዘ ፡ በመሆኑ ፡ ጥቂቶች ፡ ጠበቆች ፡ ብቻ ፡ በመደጋገም ፡ በነፃ ፡ እንዲቆሙ ፡ ሲታዘዙ ፡ አብዛኛዎቹ ፡ ግን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሳያዛቸውና ፡ በነፃ ፡ ለደሀ ፡ ተከሳሾቹ ፡ ሳይቆሙ ፡ የሚኖሩ ፡ ናቸው ።

ከ፷ ፡ ዓ.ም. ወዲህ ፡ ግን ፡ ለያንዳንዱ ፡ የወንጀል ፡ ችሎት ፡ ሠላሳ ፡ የሚሆኑ ፡ ጠበቆች ፡ የተደለደሉ ፡ በመሆናቸው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቱ ፡ ለወጥ ፡ ያለ ፡ መልክ ፡ የያዘ ፡ ይመስላል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በድልድሉ ፡ ላይ ፡ ካሁኑ ፡ ቅሬታ ፡ የተፈጠረ ፡ በመሆኑ ፡ ሁኔታውን ፡ ለማጥናት ፡ ጠበቆች ፤ አቃቤ ፡ ሕጐችና ፡ ዳኞች ፡ ተሰብስበው ፡ እንዲመካከሩበት ፡ ታስቧል ።

በመሠረቱ ፡ ጠበቆች ፡ ነፃ ፡ አገልግሎታቸውን ፡ ለደሀው ፡ በመስጠት ፡ መብቱ ፡ እንዲጠበቅለት ፡ ማድረግ ፡ ተገቢ ፡ ተግባራቸው ፡ መሆኑ ፡ የማያጠራጥር ፡ ነው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ያሉት ፡ ጠበቆች ፡ አሁን ፡ ባላቸው ፡ የኤኮኖሚ ፡ ይዞታና ፡ የወንጀል ፡ አፈጻጸም ፡ ተግባር ፡ እየበረከተ ፡ በሄደበት ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ጠበቆች ፡ ለድሆች ፡ ተከሳሾች ፡ ነፃ ፡ አገልግሎታቸውን ፡ ማበርከት ፡ አለባቸው ፡ ማለት ፡ በመጠኑ ፡ አስቸጋሪ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። አገልግሎታቸውን ፡ በነፃ ፡ ለመስጠት ፡ ፈቃደኞች ፡ ቢሆኑ ፡ ወይም ፡ ቢገደዱ ፤ አብዛኞቹ ፡ የገንዘብ ፡ እጥረት ፡ ስለሚያጋጥማቸው ፡ ምናልባት ፡ የሚሰጣቸውን ፡ ጉዳይ ፡ በግድ ፡ የለሽነት ፡ መልክ ፡ እየወሰዱ ፡ ሊያበላሹት ፡ ይችላሉ ። ስለዚህ ፡ ይህን ፡ ችግር ፡ ለማቃለልና ፡ ጠበቃውም ፡ የገንዘብ ፡ አምሮት ፡ ይዞት ፡ ጉዳዩን ፡ እንዳያበላሽ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ የገንዘብም ፡ ሆነ ፡ የሞራል ፡ ድጋፍ ሊሰጥ ፡ የሚችል ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ ቢቋቋም ፡ ሳያገለግል ፡ አይቀርም ።

፬/ ትክክለኛ ፡ ወይም ፡ ለጊዜው ፡ ተስማሚ ፡ ያልሆኑ ፡ ሕጎች ፡ እንዲሻሻሉ ፡ ማድረግ ። የሀገራችን ፡ ሕግ ፡ በጥበብና ፡ በትክክለኛ ፡ መንገድ ፡ ተደራጅቶ ፡ የወጣ ፡

እንዲሆንና ፡ ከወጣም ፡ በኋላ ፡ አስተዳደሩ ፡ ከጊዜው ፡ ጋር ፡ የሚራመድ ፡ ያልተዛባ ፡ እንዲሆን ፡ መጣጣር ፡ የጠበቆች ፡ ተግባር ፡ ነው ።

ሕግ ፡ በሕግ ፡ ሊቃውንት ፡ ተጠንቶ ፡ ካልወጣ ፡ ለሕዝቡ ፡ ከሚያስገኘው መድ ኅንነት ፡ የሚያስከትለው ፡ ጉጂነት ፡ የበለጠ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። አስቀድሞ ፡ ሳይታሰብ በትና ፡ በሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ ሳይመከርበት ፡ የሚወጣ ፡ ሕግ ፡ በሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡ መታ ወክንና ፡ ጭቀናን ፡ ያስከትላል ። ማንኛውም ፡ ሕግ ፡ ግልጽና ፡ የሕዝቡን ፡ ፍላጐት ፡ የሚያረካ ፡ ሆኖ ፡ ካልተገኘ ፡ ጥቅም ፡ የለውም ። ስለዚህ ፡ ሕጉ ፡ ለሕዝቡ ፡ ጥቅም ፡ እንዲውል ፡ ለማድረግ ፡ ጠበቆች ፡ በሚከተሉት ፡ ሁለት ፡ መንገዶች ፡ ሊረዱ ፡ ይች ላሉ ።

ሀ/ ዳኞች ፡ ፍርዳቸውን ፡ በሚሰጡበት ፡ ጊዜ ፡ ለሕጉ ፡ ትክክለኛውን ፡ ትርጉም ፡ እንዲሰጡትና ፡ ተመሳሳይ ፡ ሆነው ፡ በሚነሱት ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ ይህ ፡ ትክክ ለኛው ፡ የሕጉ ፡ ትርጉም ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ በማድረግ ።

ለ/ ሕጉ ፡ በሚወጣበት ፡ ጊዜ ፡ አስቀድሞ ፡ እንዲታሰብበት ፤ ግልጽና ፡ የሕዝቡን ፡ ፍላጐት ፡ የሚያረካ ፡ እንዲሆን ፤ ከወጣም ፡ በኋላ ፡ ለጊዜው ፡ ሁኔታ ፡ ተስማሚ ፡ ሆኖ ፡ ያልተገኘ ፡ እንደሆነ ፡ እንዲለወጥ ፡ በማድረግ ፡ ነው ።

እርግጥ ፡ ሕጉ ፡ እንዲሻሻልና ፡ ከጊዜው ፡ ጋር ፡ እንዲራመድ ፡ ማድረግ ፡ የጠበ ቆች ፡ ተግባር ፡ መሆን ፡ አለበት ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ከላይ ፡ በ(ሀ) የተጠቀሰውን ፡ ተግባር ፡ የተማሩ ፡ ጠበቆች ፡ ሊጠቀሙበት ፡ ሲችሉ ፤ በ(ለ) የተጠቀሰውን ፡ ተግባር ፡ ግን በሥራ ፡ ላይ ፡ ማዋል ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ ሕጉ ፡ የሚወጣው ፡ በፓርላማው ፡ ሲሆን ፡ በጠበቆችና፡ በፓርላማው ፡ አባሎች፡ መካከል፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ በጣም ፡ የመነመነ ፡ ነው ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ ቢቋቋምና ፡ ከአላማ ዎቹ ፡ አንዱ ፡ ይህን ፡ ተግባር ፡ አድርጐ ፡ ቢሠራ ፡ በጣም ፡ የተሻለ ፡ ነው ። ማኅበሩም እስኪቋቋም ፡ ድረስ ፡ አሁን ፡ ጠበቆች ፡ ተሰብስበው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥር ዓት ፡ አንቀጽ ፡ ፶፰ ፡ ላይ ፡ ቅሬታቸውን ፡ ሊያሰሙ ፡ እንደሚችሉ ፡ ሁሉ ፡ በሌሎቹም ሕዝብ ፡ ነክ ፡ ሕጐች ፡ ላይ ፡ እንደዚሁ ፡ ቢያደርጉም ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ይሆናል ። ባጭሩ ፡ ጠበቆች ፡ የራሳቸውን ፡ ጥቅም ፡ በሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በውል ፡ ጉዳይም ፡ ላይ ፡ ድምፃቸውን ፡ ማሰማት ፡ አለባቸው ።

ፎ/ <u>ለፍርድ ፡ የሚቀርቡ ፡ ጉዳዮች ፡ በቶሎ ፡ ፍጻሜ ፡ እንዲያገኙ ፡ ማድረግ ።</u>

ለፍትሕ ፡ መዘግየት ፡ ዋና ፡ ምክንያቶች ፡ ሆነው ፡ የሚገኙት ፡ የዳኞችና ፡ የጠ በቆች ፡ ደንበኛውን ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ አለማግኘት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ባለጉዳዩ ፡ በወቅቱ ፡ መብቱ ፡ እንዲጠበቅለት ፡ ምስክሮች ፡ በከንቱ ፡ እንዳይጉላሉና ፤ ሕዝቡ ፡ በቀጠሮ ፡ ብዛት ፡ ሥራ-ፈት ፡ እንዳይሆን ፡ ጉዳዩን ፡ በተጣራ ፡ አኳኋን ፡ ለማቅረብና ፡ ለመቀበል ፡ የሚችሉ ፡ ጠበቆችና ፡ ዳኞች ፡ በአንድ ፡ ሀገር ፡ ውስጥ ፡ እንዲኖሩ ፡ ማድረግ የያንዳንዱ ፡ ጠበቃና፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ ተግባር ፡ ነው ። እያንዳንዱ ፡ ጠበቃ፡ ወይም ፡ የጠበቆች፡ ማህበር፡ ይህን፡ ተግባር፡ የሚፈጽመው ፡ አንድ፡ ሰው ፡ ጠበቃ ፡ ወይም ፡ ዳኛ ፡ ከመሆኑ ፡ በፊት ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ የትምህርት ፡ ችሎታ ፡ ሊኖረው ፡ እንደሚገባ ፡ የሕግ ትምህርት ፡ ከሚሰጡት ፡ ድርጅቶች ፡ ጋር ፡ በመመካከር ፡ ወይም ፡ እራሱ ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ የተወሰነ ፡ የችሎታ ፡ መለኪያ ፡ ፈተና ፡ በማሰናዳት ፡ ነው ።

በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ካለው ፡ የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ወቀሳ ፡ ዋናውን ፡ ቦታ ፡ ይዞ ፡ የሚገኘው ፡ የነገር ፡ ወደኋላ ፡ መጐተት ፡ ነው ። ከላይ ፡ በጸሐፊው ፡ እንደተገለጸው ፡ በኢትዮጵያም ፡ ውስጥ ፡ ለነገር ፡ መጐተት ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ጠበቆች ፡ የሕግ ፡

ዕውቀታቸው ፡ የተወሰነ ፡ በመሆኑ ፡ ክርክራቸውን ፡ በደንበኛው ፡ አሳክተው ፡ ለመ ቅረብ ፡ ስለሚያዳግታቸውና ፡ ዳኞችም ፡ እንደዚሁ ፡ ዕውቀታቸው ፡ ያነሰ ፡ በመሆኑ ፡ ደንበኛውን ፡ መምሪያም ፡ ሆነ ፡ ፍርድ ፡ ለመስጠት ፡ ባለመቻላቸው ፡ ነው ። ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ የሚገርመው ፡ የዳኞቹ ፡ የሕግ ፡ እውቀት ፡ ማጣት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በብዙ ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ የሕጎቹ ፡ መጻሕፍት ፡ እንኳ ፡ የማይገኙ ፡ በመሆ ናቸው ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ዳኞች ፡ ከጠበቆች ፡ ጠበቆችም ፡ ከዳኞች ፡ የሕጎቹን ፡ መጻ ሕፍት ፡ እየተዋዋሱ ፡ ሲሠሩ ፡ ይታያሉ ።

ስለዚህ ፡ ክርክሮች ፡ በአስቸኳይ ፡ ፍጻሜ ፡ እንዲያገኙ ፡ ለማድረግ ፡ ዳኞችና ፡ ጠበቆች ፡ ሥራቸውን ፡ ከመጀመራቸው ፡ አስቀድሞ ፡ የተወሰነ ፡ ችሎታ ፡ እንዲኖራ ቸው ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ጥብቅ ፡ እርምጃ ፡ ቢወስድ ፡ ወይም ፡ የሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ ማኅበር ፡ ተቋቁሞ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ እርምጃ ፡ እንዲወስድ ፡ ሥልጣን ፡ ቢሰጠው ፡ የተሻለ ፡ ይሆናል ።

## የሕግ ፡ ጠበቃ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ያለበት ፡ ግዴታ ።

ማንኛውም ፡ የሕግ ፡ ጠበቃ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ብዙ ፡ ግዴታዎች ፡ አለበት ። ከእነዚሁም ፡ ግዴታዎች ፡ ውስጥ ፡ በሕግ ፡ ሥነ ፡ ምግባር ፡ ቀደምትነት ፡ አለው ፡ ተብሎ ፡ የሚገመተው ፡ ጠበቃው ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ማሳየት ፡ ያለበት ፡ አክብሮትና ፡ ትህትና ፡ ነው ። በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ጠበቆች ፡ ለዳኞች ፡ አክብሮትና ፡ ትኅትና ፡ ያሳያሉ ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ይህንን ፡ ዓይነት ፡ ጠባይ ፡ የሚ ያሳዩት ፡ ዳኞችን ፡ ከመፍራት ፡ የተነሳ ፡ እንጂ ፡ በእርግጥ ፡ ከልብ ፡ የመነጨ ፡ አይደ ለም ። ይሁንና ፡ ዳኛው ፡ ራሱ ፡ በጠባዩ ፡ የተወደደ ፤ ሰው ፡ አክባሪ ፤ ትሁትና ፡ ታጋሽ ፡ በተለይም ፡ ለጠበቆች ፡ የሚገባቸውን ፡ ክብር ፡ የማይነፍጋቸው ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ጠበቆች ፡ የሚያሳዩት ፡ ትኅትናና ፡ አክብሮት ፡ ከልብ ፡ የመነጨ ፡ ነው ፡ ልንል ፡ እን ችላለን ።

በሌላው ፡ በኩል ፡ የተመለከትን ፡ እንደሆነ ፡ ጠበቆች ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፤ ማለት ፡ የዳኞች ፡ ረዳቶች ፡ እንደመሆናቸው ፡ መጠን ፡ አንድ ፡ ክርክር ፡ በሚገባ ፡ ተከናውኖ፡ በመጨረሻው ፡ እውነት ፡ እንድትወጣ ፡ መሞከርና ፡ ለዚሁም ፡ ሥራ ፡ ለዳኞች ፡ ተባባሪ ፡ በመሆን ፡ የቀደምትነት ፡ ደረጃ ፡ መያዝ ፡ እንዳለባቸው ፡ መታወቅ ፡ አለበት ። ስለዚህም ፡ ጠበቆች ፡ ፍርድ ፡ ቤትን ፡ ለማሳሳት ፡ ከመሞከር ፡ ፈጽመው ፡ መራቅ ፡ ይኖርባቸዋል ። ይኸውም ፡ እውነት ፡ ያልሆነውን ፡ ነገር ፡ እውነት ፡ አስመስለው ፡ ከመ ከራከር ፡ መቆጠብ ፡ ምስክሮች ፡ በሐሰት ፡ የተደገፈ ፡ ማስረጃ ፡ እንዲሰጡ ፡ አለማ ግባባት ፤ ለትክክለኛ ፡ ፍትሕ ፡ ምቹ ፡ የሆነውን ፡ መንገድ ፡ ለማዛባት ፡ አለመከጀል ፤ በአወጣ ፡ ያውጣው ፡ ወይም ፡ አምነው ፡ ይቀበሉኛል ፡ በማለት ፡ በክርክር ፡ ጊዜ ፡ ፈጽሞ፡ ግንኙነት ፡ የሌለውን ፡ አንቀጽ ፡ አለመጥቀስ ፡ ጠበቆች ፡ ሊያደርጓቸው ፡ ከሚገቡት ፡ ተግባሮች ፡ ጥቂቶቹ ፡ ናቸው ። ይህ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ አብዛኛዎቹ ፡ የአገራችን ፡ ጠበቆች ፡ እንደዚህ ፡ ዓይነቶቹን ፡ ግዴታዎቻቸውን ፡ የዘነጉ ፡ ይመስላሉ ፤ ምናልባትም ፡ ግዴ ታቸውን ፡ ባለማወቅ ፡ ይሆናል ፡ ፍርድ ፡ ቤትን ፡ ለማሳሳት ፡ እውነት ፡ ያልሆነውን ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ እውነት ፡ አድርገው ፡ ያቀርባሉ ። ሁለተኛ ፡ ምስክሮችን ፡ ይመክራሉ ፤ ከደንበኞቻቸው ፡ የምስክር ፡ ዝርዝር ፡ በመቀበል ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰጡትን ፡ ጭብጥ ፡ እነርሱ ፡ ራሳቸው ፡ በሚፈልጉት ፡ መልክ ፡ ብቻ ፡ እንዲመሰክሩላቸው ፡ ምስክሮችን ፡ በመምከር ፡ የሚመሰክሩትን ፡ ያስጠናቸዋል ። ይህ ፡ ዓይነቱ ፡ አሠራር ፡ እውነት ፡ እን ዳትገለጽ ፡ ፍትሕ ፡ እንዳይሠምር ፡ ስለሚያደርግ ፡ ከትክክለኛው ፡ የጠበቆች ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ምግባር ፡ ፈጽሞ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

የደንበኛውና ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጥቅም ፡ በሚጋጭበት ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ጠበቃ ፡
እውነት ፡ እንዲገለጥ ፡ በማለት ፡ ደንበኛውን ፡ የሚጐዳ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ተገቢውን፡
ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማመልከት ፡ አለበት ፡ ወይስ ፡ የደንበኛውን ፡ ጥቅም ፡ ብቻ ፡ ለመጠ
በቅ ፡ በመጣር ፡ የፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ጥቅም ፡ ወደጐን ፡ መተው ፡ አለበት ፡ የሚለው ፡ አ
ማራጭ ፡ ብዙ ፡ አከራካሪ ፡ ሆኗል ። ለምሳሌ ፡ ሚስተር ፡ ቡልቶን ፡ የተባሉ ፡ አንድ ፡
እንግሊዛዊ ፡ ደራሲ ፡ ይህን ፡ አከራካሪ ፡ ጥያቄ ፡ እንደዚህ ፡ ብለው ፡ መልሰውታል ።

«ጠበቃው ፡ ደንበኛውን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱንም ፡ ጭምር ፡ ማገ
ልገል ፡ እንዳለበት ፡ መዘንጋት ፡ የለበትም ። ይህም ፡ ማለት ፡ ደንበኛዬን ፡
ከክስ ፡ አድነዋለሁ ፡ በማለት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ማታለል ፡ ወይም ፡ ያልሆነ፡
መስመር ፡ ማስያዝ ፡ አይገባም ። እንዲያውም ፡ ጉዳትም ፡ እንኳን ፡ የሚያ
መጣበት ፡ ቢሆን ፡ በጉዳዩ ፡ አግባብ ፡ ያለውን ፡ ሕግ ፡ በተገቢው ፡ ቦታ ፡
መጥቀስና ፡ ለዳኛው ፡ ማስታወስ ፡ የጠበቃ ፡ ዓይነተኛ ፡ ተግባሩ ፡ ነው ። በዐ
ቃቤ ፡ ሕጉም ፡ ሆነ ፡ በምስክሮች ፡ የቀረቡት ፡ ፍሬ ፡ ነገሮች ፡ ስህተት ፡ ካለ
ባቸው ፡ ስህተቱም ፡ ሲታረም ፡ ተከሳሹን ፡ እንደሚጐዳው ፡ ጠበቃው ፡ ካመ
ነበት ፡ ይህን ፡ የተሳሳተ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ እንዳለ ፡ መተው ፡ እንጂ ፡ ለፍርድ ፡
ቤቱ ፡ ያለኝ ፡ ግዴታ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ለማስተካከል ፡ መሞከር ፡ የለበትም» ።

ይሁንና ፡ የሚስተር ፡ ቡልቶንን ፡ ሃሳብ ፡ የሚቃወሙ ፡ ሰዎች ፡ አይታጡም ፤
ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ ይረዳኛል ፡ ብሎ ፡ ያቆመውን ፡ ደንበኛውን ፡ አሳ
ልፎ ፡ ይስጥ ፡ ማለት ፡ አስቸጋሪ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። አንድ ፡ ተከሳሽ ፡ ጠበቃ ፡ መያዙ ፡
የሚጐዳው ፡ ከሆነ ፡ ለወደፊቱ ፡ ጠበቃ ፡ መግዛት ፡ ይፈራል ። ስለዚህም ፡ ተራው ፡
ሰው ፡ እራሱ ፡ ጉዳዩን ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይዞ ፡ እንዲመጣና ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡
በሌለው ፡ አታካራ ፡ ጊዜ ፡ እንዲያጠፋ ፡ ማደፋፈር ፡ ይሆናል ። ይህ ፡ ጉዳይ ፡ በአሁኑ ፡
ጊዜ ፡ ብዙ ፡ የሚያከራክረን ፡ አይመስለንም ፤ ምክንያቱም ፡ ጠበቆቻችን ፡ ዋና ፡ ዓላ
ማችን ፡ ብለው ፡ የያዙት ፡ ደንበኞቻቸውን ፡ ማስደሰትና ፡ ክርክሩን ፡ በምንም ፡ መን
ገድ ፡ መርታትና ፡ ጥቅም ፡ መፈለግ ፡ በመሆኑ ፡ እንኳን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለደንበኞቻ
ቸው ፡ የሚጠቅም ፡ ነገር ፡ በስህተት ፡ ሊመዘግብላቸው ፡ ቀርቶ ፡ ራሳቸው ፡ ሆነ ፡
ብለው ፡ ለማሳሳት ፡ የሚሞክሩ ፡ አያሌ ፡ ናቸው ።

ዳኞችን ፡ ከችሎት ፡ ውጪ ፡ አንድ ፡ አጋጣሚ ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በማን
ኛውም ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ በማግኘት ፡ ሌላው ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ በሌለበት ፡ በዚያው ፡
ችሎት ፡ ያላቸውን ፡ ክርክር ፡ በማንሳት ፡ ለማግባባት ፡ አስተያየታቸውን ፡ መግለጽ ፡
የለባቸውም ። ይህ ፡ በሌሎች ፡ አገሮች ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ምግባር ፡ የተከለከለ ፡ ድርጊት ፡
ሲሆን ፡ የሀገራችን ፡ ጠበቆች ፡ ግን ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ እንደዚህ ፡ ዓይነቱን ፡ ድርጊት ፡
ሲፈጽሙ ፡ መታየታቸው ፡ አልቀረም ። ዳኞችም ፡ በማወቅም ፡ ሆነ ፡ ባለማወቅ ፡ በእ
ነርሱ ፡ ችሎት ፡ ያለውን ፡ ክርክር ፡ ሌላው ፡ ወገን ፡ በሌለበት ፡ ከአንደኛው ፡ ጠበቃ ፡
ጋር ፡ ሐሳብ ፡ ለሐሳብ ፡ ይለዋወጡበታል ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ አንዳንድ ፡ ጠበ
ቆች ፡ ሥራዬ ፡ ብለው ፡ ዳኛ ፡ እየወሰዱ ፡ የሚጋብዙና ፡ አማላጅ ፡ እየሆኑ ፡ የሚያስ
ጠኑ ፡ አሉ ፡ የሚባል ፡ ሐሜት ፡ አለ ። በቀጠሮው ፡ ቀን ፡ ዳኛው ፡ ገና ፡ መዝገቡን ፡
ሳያይ ፡ «አቶ ፡ እገሌ ፡ እኮ ፡ የሚለው ፡ እንዲህ ፡ ነው ። የአንተ ፡ ጥያቄ ፡ ሕግን ፡ የተመ
ረኮዘ ፡ አይመስልም» ፡ እያሉ ፡ ትችት ፡ በመስጠት ፤ እንዲሁም ፡ ገላጋይ ፡ ሽማግሌ ፡
በመምሰል ፡ «ነገሩ ፡ በሽማግሌ ፡ ቢታይላችሁ ፡ በስምምነት ፡ ብትጨርሱትስ?» በማ
ለት ፡ የሚያማቱ ፡ ዳኞች ፡ ሞልተዋል ። በሌላው ፡ ወገን ፡ ያለውን ፡ ጠበቃ ፡ ክርክር ፡
ፈር ፡ ለማስለቀቅ ፡ በሰፊው ፡ የሚሞክሩ ፡ ዳኞችም ፡ አሉ ።

በዝቅተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚገኙት ፡ ዳኞች ፡ በችሎታ ፡ ማነስ ፡ ምክንያትና ፡
ከሕጉ ፡ ጋር ፡ በሰፊው ፡ የማይተዋወቁ ፡ በመሆናቸው ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ስህተት ፡ ያደር

ጋሉ ። በእነዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ጠበቆች ፡ ሕግ ፡ ጠቅሰው ፡ የተከራከሩ ፡ እንደሆነ ፡ የሚታዩት ፡ እንደጠላት ፡ ነው ። ምንም ፡ እንኳን ፡ እያደረ ፡ እየተሻሻለ ፡ የሄደ ፡ ቢሆንም ፡ በጠቅላላው ፡ ጠበቆች ፡ ከማይግባቧቸው ፡ ዳኞች ፡ ብዙ ፡ ግልምጫና ፡ ትችት ፡ እንደሚደርስባቸው ፡ ግልጽ ፡ ነው ። በአንዳንድ ፡ ዳኞች ፡ አስተያየት ፡ የጠበቆች ፡ ሥራ ፡ ክብር ፡ ሊሰጠው ፡ የማይገባ ፡ ነው ፤ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ የሚናገረው ፡ ሕጋዊ ፡ ቢሆንም ፡ ባይሆንም ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ካልመሰለው ፡ እንዲናገር ፡ እንኳን ፡ አይፈቅድለትም ። ዳኞች ፡ ጠበቆችን ፡ የማስፈራሪያ ፡ መሣሪያ ፡ አድርገው ፡ የያዙት ፡ ፍርድ ፡ ቤትን ፡ «ስለተጋፋህ» ፡ እንቀጣሃለን ፡ የሚለው ፡ አነጋገር ፡ ነው ። «ረጋ ፡ ብትል ፡ እኮ፡ ይሻላል ፡ አለበለዚያ ፡ ...» በማለት ፡ ያስፈራሩታል ። እንግዲህ ፡ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ አንድን ፡ ነገር፡ ወደ፡ ፍርድ፡ ቤት ፡ ለማቅረብ ፡ ሲፈልግ ፡ ማየት፡ ያለበት ፡ የነገሩን፡ ትክክለኛነት ፤ ማዋጣት ፡ አለማዋጣቱን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ አስቀድሞ ፡ ጉዳዩ ፡ ወደማይፈልገው ፡ ዳኛ ፡ እንዳይመራበት ፡ ሊያደርግ ፡ የሚችለውን ፡ አጥብቆ ፡ መመርመር ፡ ጭምር ፡ ይሆናል ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የአንድ ፡ ፋይል ፡ አመራር ፡ በቂ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አልያዘም ፡ ነበር ። አንድ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ ፋይል ፡ ሲከፍት ፡ እነ ፡ እገሌ ፡ ችሎት ፡ ምራልኝ ፡ በማለት ፡ ከተራ ፡ ፋይል ፡ ከፋች ፡ ጋር ፡ በመስማማት ፡ ነገሩን ፡ ወደ ፡ ሚፈልገው ፡ ችሎት ፡ ያስመራል ። ይህ ፡ ዓይነቱ ፡ አደራረግ ፡ የአንደኛውን ፡ ወገን ፡ ጠበቃ ፡ ሲረዳ ፡ የሌላውን ፡ ወገን ፡ ሊጐዳው ፡ ይችላል ።

በጠቅላላው ፡ ጠበቆች ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ጋር ፡ ያላቸው ፡ ግንኙነት ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ እየተሻሻለ ፡ በመሄድ ፡ ላይ ፡ ቢገኝም ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ ብለን ፡ እምናምንበት ፡ ደረጃ ፡ ለመድረስ ፡ ገና ፡ የብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጉዞ ፡ እንደሚቀረው ፡ አይጠረጠርም ።

የመናናቅ ፣ የመቀናናት ፣ የመፈራራት ፤ የጥርጣሬ ፡ እና ፡ የሌላም ፡ ዓይነት ፡ የተመሳሳይ ፡ መንፈስ ፡ በሁለቱም ፡ ወገን ፡ አለ ። ይህን ፡ ለማስወገድ ፡ በዕውቀት ፡ የበሰሉ ፤ በልምምድ ፡ የቆዩ ፤ በቅን ፡ ልቦና ፡ የሚሠሩ ፡ ዳኞችን ፡ በወንበሩ ፡ ላይ ፡ በማስቀመጥና ፡ እንደዚሁም ፡ በሌላው ፡ በኩል ፡ የጥብቅና ፡ ፈቃድ ፡ በመስጠት ፡ ረገድ ፡ ከፍተኛ ፡ ምርጫ ፡ ቢደረግ ፡ የፍርድ ፡ ቤትና ፡ የጠበቆች ፡ ግንኙነት ፡ እየተሻሻለ ፡ እንደሚሄድ ፡ ጥርጥር ፡ የለውም ።

## ጠበቃ ፡ ለደንበኛው ፡ ያለበት ፡ ግዴታ ።

አንድ ፡ ጠበቃ ፡ ለአንድ ፡ ሰው ፡ ወኪል ፡ ሆኖ ፡ ሊከራከር ፡ ተገቢ ፡ አበሉን ፡ ተቀብሎ ፡ ወይም ፡ የሚቀበለውን ፡ ተገቢ ፡ አበል ፡ ወስኖ ፡ ከጉዳዩ ፡ ከገባ ፡ በኋላ ፡ በማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ በክርክሩ ፡ መጠን ፡ እንደ ፡ ባለጉዳዩ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ ለመከራከር ፡ ግዴታ ፡ አለበት ። ጠበቃ ፡ የደንበኛው ፡ እንደራሴ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ የጀመረውን ፡ ነገር ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ መግፋት ፡ ይኖርበታል ።

ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ አንድን ፡ ነገር ፡ ከመጀመሩ ፡ ወይም ፡ ከመቀጠሉ ፡ በፊት ፡ የደንበኛው ፡ ባላጋራ ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ ማወቅና ፤ ክርክሩን ፡ ያምንበት ፡ ወይም አያምንበት ፡ እንደሆነ ፡ ማለት ፡ አከራካሪ ፡ መንገድ ፡ እንዳለው ፡ መመርመር ፡ ተገቢው ፡ ነው ። አንዳንድ ፡ ጠበቆች ፡ ክርክር ፡ ሲመጣላቸው ፡ በተቀዳሚ ፡ ባለጉዳዩን ፡ የሚጠይቁት ፡ ባላጋራው ፡ ማን ፡ እንደሆነና ፡ ፍሬ ፡ ነገሩ ፡ በምን ፡ ላይ ፡ እንደተመሠረተ ፡ ነው ። ይህንን ፡ ካጣሩ ፡ በኋላ ፡ ጉዳዩን ፡ ለመቀበል ፡ ያላቸውን ፡ ፈቃደኛነት፡ ይገልጹለታል ። ብዙዎቹ ፡ ጠበቆች ፡ ግን ፡ ይህን ፡ አይነቱን ፡ ጥያቄ ፡ ሳያጣሩ ፡ በሀሰት ፡ የተመሠረተ ፡ ነገር ፡ እንኳን ፡ ሲመጣላቸው ፡ የሚያገኙትን ፡ ጥቅም ፡ ብቻ ፡ በመመልከት ፡ ጉዳዩን ፡ ለመጀመር ፡ ይቀበላሉ ። ነገሩ ፡ ከተጀመረና ፡ ገንዘብ ፡ ከተቀበሉ ፡ በኋላ ፡ ምክንያት ፡ እየፈጠሩ ፡ ከደንበኛቸው ፡ ጋር ፡ በመጣላት ፡ ወይም ፡ ነገ

ሩን ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ በመሸሽ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እያፈገፈጉ ፡ ሌላ ፡ አዲስ ፡ ጠበቃ ፡ ሊገዛ ፤ ችሎታ ፡ የሌለውን ፡ ሰው ፡ ራሱ ፡ እንዲከራከር ፡ ያደርጉታል ። በሕግ ፡ ሥነ ፡ ምግባር መሠረት ፡ ጠበቃው ፡ ለመማከር ፡ የመጣለትን ፡ ሰው ፡ ባላጋራ ፡ ማንነት ፡ ካረጋገጠ ፡ በኋላ ፡ «ከባላጋራህ ፡ ጋር ፡ ዝምድና ፡ ወይም ፡ ግንኙነት ፡ አለኝና ፡ ጉዳዩን ፡ ከመዘክ ዘክህ ፡ በፊት ፡ ነገሩን ፡ ተቀብዬ ፡ ልከራከርልህ ፡ ስለማልችል ፡ ሌላ ፡ ጠበቃ ፡ ብትፈ ልግ ፡ ይሻላል» ፡ ብሎ ፡ ሊያሰናብተው ፡ ይገባል ።

ይሁንና ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ሳይሆን ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ጠበቆችን ፡ የሚያጋጥማ ቸው ፡ ችግር ፡ አንድ ፡ ክርክር ፡ ያዋጣል ፡ ወይስ ፡ አያዋጣም ፡ የሚለው ፡ ጥያቄ ፡ አስቀድሞ ፡ መመለሱ ፡ ነው ። ጠበቆች ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ በጣም ፡ ይወቀሳሉ ። የማያ ዋጣ ፡ ጉዳይ ፡ ሲመጣላቸው ፡ ለምን ፡ አያሰናብቱም ፡ ለምንስ ፡ ለማስታረቅ ፡ አይሞ ክሩም ፡ የሚል ፡ ትችት ፡ አለ ። እርግጥ ፡ ብዙዎቹ ፡ ጠበቆች ፡ በጥቅም ፡ ብቻ ፡ የሚ መሩ ፡ ስለሆኑ ፡ ማንኛውንም ፡ የማያዋጣውን ፡ ጉዳይ ፡ ሁሉ ፡ ተቀብለው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሲያቀርቡ ፡ ይታያሉ ፤ ይህ ፡ አሠራር ፡ የገቢ ፡ ምንጫቸው ፡ እንዳይደርቅ ፡ ለማ ድረግ ፡ የሚወስዱት ፡ እርምጃ ፡ ነው ። ይሁንና ፡ በሌላ ፡ አንፃር ፡ ልንመለከተው ፡ የሚገባ ፡ ታላቅ ፡ ችግር ፡ አለ ። ይኸውም ፡ «የሕግ ፡ እርግጠኛነት» ፡ ሳይሆን ፡ «የዳኝ ነት ፡ እርግጠኛነት» ፡ ማለትም ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በአንድ ፡ ዓይነት ፡ መልክ ፡ አለመመ ራት ፡ ነው ። ፍርድ ፡ ቤት ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ በሆኑ ፡ ነገሮች ፡ ላይ ፡ ተመሳሳይ ፡ ፍርድ ስለማይሰጥና ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የበላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችን ፡ ውሳኔዎች ፡ እንደምሳሌ ፡ አድርገው ፡ ስለማይሠሩባቸው ፡ ነው ። እንዲያውም ፡ አንዱ ፡ ችሎት ፡ ራሱ ፡ በአንድ ፡ ዓይነት ፡ ጉዳይ ፡ በአንድ ፡ ዓይነት ፡ ጭብጥ ፡ የተለያየ ፡ ፍርድ፡ ስለሚ ሰጥ ፡ ጠበቆች ፡ የሚያዋጣውን ፡ ጉዳይ ፡ አስቀድመው ፡ ለመተንበይ ፡ አይችሉም ። እዚህ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ምሳሌ ፡ ልጠቅሰው ፡ የምፈልገው ፡ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ ያጫወተኝን ፡ ነው ። ጠበቃው ፡ ከአምስት ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ የጥብቅና ፡ ሥራ ፡ እንደጀመሩ ፡ በስድ ስት ፡ ወሮች ፡ ውስጥ ፡ ሃምሳ ፡ ጉዳዮች ፡ እንደመጡላቸውና ፡ ከዚህ ፡ ውስጥ ፡ ስምንት ብቻ ፡ ያዋጣኛል ፡ ብለው ፡ እንደተቀበሉ ፡ ከነገሩኝ ፡ በኋላ ፡ «ከእነዚህ ፡ ከስምንቱ ፡ ውስጥ ፡ ሁለቱን፡ ብቻ ፡ ስረታባቸው ፡ ስድስቱን፡ ግን፡ ተረታሁባቸው፤ ከተረታሁባቸው ፡ ጉዳዮች ፡ አንዱ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ተመልክቼ ፡ የተሸጠው ፡ መሬት ፡ በከተማ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ ስለሆነ ፡ የሥጋ ፡ ዘመዶች ፡ ወይም ፡ ተወላጆች ፡ በቀዳሚነት ፡ ግዥ፡ ይገባናል ፡ የማለት ፡ መብት ፡ የላቸውም ፡ የሚለውን ፡ አንቀጽ ፡ በማየት ፡ በዚህ ፡ ሕግ፡ የተደገፈ ፡ ክርክር ፡ ባቀርብ ፡ ሕጉ ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሌሎቹን ፡ ወገኖች ፡ ተወላጅነታቸውን ፡ ብቻ ፡ እንዲያስመሰክሩ ፡ አድርጐ ፡ ካስመሰከሩ ፡ በኋላ ፡ ፈረደ ብኝ ። እዚያው ፡ ችሎት ፡ ተመሳሳይ ፡ ክርክር ፡ ቀርቦ ፡ በከተማ ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ ተወላጆች ፡ የግዢ ፡ ቀደምትነት ፡ መብት ፡ እንደሌላቸው ፡ ሕጉ ፡ ደንግጓል ፡ ብለው ፡ ሲፈርዱ ፡ ሰማሁ ። እንዲሁም ፡ አያዋጣም ፡ እያልኩ ፡ የመለስኳቸውን ፡ ጉዳዩች ፡ ሌሎች ፡ ጠበቆች ፡ ተቀብለው ፡ ሲረቱበት ፡ አየሁ ፤ ስለዚህ ፡ ስለአንድ ፡ ክርክር ፡ አዋ ጭነት ፡ መተንበይ ፡ የሚያዘልቅ ፡ መስሎ ፡ ስላልታየኝ ፡ ትቼዋለሁ» ። ብለው ፡ አጫወ ቱኝ ። ይሁንና ፡ ብዙዎች ፡ ጠበቆች ፡ ፈጽሞ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊቀበለው ፡ የማይገ ባውን ፡ ክስ ፡ ያቀርባሉ ። ይህ ፡ ከሕግ ፡ ሥነ ፡ ምግባር ፡ ውጪ ፡ ነው ። ደንበኞቻቸው፡ የዳኝነት ፤ ኪሣራ ፤ የጠበቃ ፡ አበል ፡ ከፍለው ፡ ቀልጠው ፡ ይቀራሉ ። ምንም ፡ እን ኳን ፡ ከላይ ፡ እንደገለጽነው ፡ ሙሉ ፡ መተማመን ፡ ሊኖር ፡ ባይችልም ፡ መታየት ፡ እንደሌለበት ፡ በግልጽ ፡ የሚታወቅ ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ማቅረብ ፡ ፍጹም ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ አድራጐት ፡ ነው ። ጥብቅና ፡ እንደ ፡ ንግድ ፡ ሥራ ፡ ገንዘብ ፡ መሰብ ሰቢያ ፡ ማድረግ ፡ የሙያውን ፡ ክብር ፡ መቀነስ ፡ ይሆናል ።

ሌላው ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ደግሞ ፡ ደንበኛው ፡ ለጠበቃው ፡ በምስጢር ፡ የነገረውን ፡ ጉዳይ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ማውራት ፡ ተገቢ ፡ አለመሆኑ ፡ ነው ። አንድ ፡ ጠበቃ ፡ በሥራው፡

ምክንያት ፡ ደንበኛው ፡ የነገረውን ፡ ምስጢር ፡ አሳልፎ ፡ ማውራት ፡ እንደሌለበት ፡ መታወቅ ፡ አለበት ። አንዳንዶች ፡ ግን ፡ ለደምበኞቻቸው ፡ ያለባቸውን ፡ ግዴታ ፡ አጥብቀው ፡ ስለማያውቁ ፡ እንዲሁም ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ በተንኰል ፡ ከሌላው ፡ በኩል ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ ለመወዳጀት ፡ ሲሉ ፡ ሚስጥሩን ፡ ያባክኑበታል ። በዚህም ፡ ጉዳይ ፡ በዲሲፕሌን ፡ የተቀጡ ፡ ይገኛሉ ። ጠበቃው ፡ በበቂ ፡ ምክንያት ፡ ከክርክሩ፡ ቢወጣና ፡ ሌላ ፡ ጠበቃ ፡ ቢተካ ፡ ደንበኛው ፡ ሳይፈቅድለት ፡ ለአዲሱ ፡ ጠበቃ ፡ የደንበኛውን ፡ ምሥጢር ፡ መናገር ፡ እንኳ ፡ ክልክል ፡ ነው ። ጉዳዩ ፡ ካለቀም ፡ በኋላ ፡ አለ ፡ ደንበኛው ፡ ፈቃድ ፡ በሥራው ፡ ምክንያት ፡ ያገኘውን ፡ ምሥጢር ፡ ማውጣት ፡ የለበትም ። ስለሆነ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቁ. ፬፻፯ ፡ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ የተነገረውን ፡ ምሥጢር ፡ ቢያወጣ ፡ እንደሚያስቀጣው ፡ ተደንግጓል ።

ይህን ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ደምድመን ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ጥያቄ ፡ ብናመራ ፡ ጠበቃ ፡ ደንበኛው ፡ ያመጣለትን ፡ ጉዳይ ፡ ያለበቂ ፡ ምክንያት ፡ አልቀበልም ፡ ለማለት ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ወይም ፡ የሌለው ፡ መሆኑንና ፡ እንዲሁም ፡ የተቀበለውን ፡ ጉዳይ ፡ ሊከራከር ፡ ከደንበኛው ፡ ጋር ፡ የሚዋዋለው ፡ ውል ፡ እንደ ፡ ተራ ፡ የውል ፡ ስምምነት ፡ ይቆጠር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንመረምራለን ።

ስለመጀመሪያው ፡ ጥያቄ ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ያለውን ፡ ሕግ ፡ ብንመረምር ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንደገለጽነው ፡ ሁሉ ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ የሚደረገው ፡ የጥብቅና ፡ ሙያ፡ ተግባር ፡ ሁለት ፡ አቋሞችን ፡ የያዘ ፡ ነው ። አንደኛው ፡ «ባሪስተር» ፡ እየተባለ ፡ የሚጠራው ፡ ክፍል ፡ ከሕዝብ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ባለው ፡ «ሶሊሲተር» ፡ የሚቀርብለትን ፡ ማንኛውንም ፡ ጉዳይ ፡ ተቀብሎ ፡ መከራከር ፡ አለበት ፡ የሚል ፡ ሲሆን ፤ ሁለተኛው ፡ ጉዳዩን ፡ ከያዘው ፡ በኋላ ፡ የመጨረሻ ፡ ዕውቀቱ ፡ እፈቀደለት ፡ ድረስ ፡ መከራከር ፡ አለበት ፡ የሚል ፡ ነው ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የጠቀስናቸው ፡ ሚስተር ፡ ቡልቶን ፡ የእንግሊዝን ፡ ሀገር ፡ የጥብቅና ፡ ሙያ ፡ ተግባር ፡ ሲገልጹ ፡ እንዲህ ፡ ብለዋል ።

> «ማንኛውም ፡ የሕግ ፡ ጠበቃ ፡ ቆሞ ፡ በሚከራከርበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ የሚቀርብለትን ፡ ማንኛውንም ፡ ጉዳይ ፡ ተቀብሎ ፡ መከራከር ፡ አለበት ፡ እንጂ ፡ የሚፈልገውን ፡ ወስዶ ፡ የማይፈልገውን ፡ ሊተው ፡ አይችልም ። እዚህ ፡ ላይ ፡ ማስታወስ ፡ የሚገባን ፡ አንድን ፡ ጉዳይ ፡ ለመውሰድ ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ጠበቃ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ግዳጅና ፡ በሌሎች ፡ አገሮች ፡ ጉዳዩን ፡ ካላመነበት ፡ ጠበቃው ፡ በጥብቅና ፡ ለአንድ ፡ ጉዳይ ፡ እንዲቆም ፡ የሚያስገድደው ፡ ነገር ፡ ያለመኖሩን ፡ ነው ። በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ያለው ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ ሕግ ፡ የጠነከረበት ፡ ሁለት ፡ ምክንያቶች ፡ አሉት ፤ አንደኛው ፡ እያንዳንዱ ፡ ጠበቃ ፡ የማይፈልገውን ፡ ጉዳይ ፡ ይተው ፡ ብሎ ፡ መፍቀድ ፡ ከሥራ ፡ የማምለጫ ፡ ዘዴን ፡ ስለሚያስፋፋ ፡ እና ፡ ሁለተኛም ፡ አንዱ ፡ ጠበቃ ፡ ይህ ፡ ጉዳይ ፡ ትክክል ፡ ነው ፡ ወይም ፡ ትክክል ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ የመፍረዱ ፡ ተግባር ፡ ለእርሱ ፡ ከተሰጠው ፡ የጠበቆችን ፡ ሳይሆን ፡ የዳኞችን ፡ ሥራ ፡ እንደያዘ ፡ ስለሚያስቆጥረው ፡ ነው ። ... ሲሆንም ፡ ጠበቃው ፡ የተሰጠውን ፡ ጉዳይ ፡ ሁሉ ፡ ተቀብሎ ፡ መከራከር ፡ አለበት ፡ የሚለው ፡ መምሪያ ፡ የሚፈርስበት ፡ ሁለት ፡ ሁኔታዎች ፡ አሉ ። አንደኛ ፡ ጉዳዩን ፡ መቀበል ፡ ከትክክለኛ ፡ ፍትሕ ፡ የሚቃረን ፡ ወይም ፡ የጥብቅና ፡ ሙያን ፡ ነፃነት ፡ የሚፃረር ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደሆነ ፤ ሁለተኛ ፡ ጠበቃው ፤ ጉዳዩን ፡ በመቀበሉ ፡ ችግር ፡ ላይ ፡ የሚወድቅ ፡ ሆኖ ፡ የተገኘ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ። ይህም ፡ የተባለው ፡ ችግር ፡ በሚከተሉት ፡ ሁለት ፡ ምክንያቶች ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። አንደኛው ፡ ጠበቃው ፡ በጉዳዩ ፡ ላይ ፡ ማየት ፡

ወይም ፡ ማወቅ ፡ የማይገባውን ፡ ምሥጢር ፡ አይቶ ፡ ወይም ፡ ሰምቶ ፡ እንደ ሆነ ፡ ሁለተኛ ፡ በባለጉዳዩና ፡ በጠበቃው ፡ መካከል ፡ ጉዳዩን ፡ ያለ ፡ አድ ልዎ ፡ ለመከራከር ፡ የማይቻል ፡ ከሆነ ፡ ነው ።»

በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ ደንበኛው ፡ ያመጣለትን ፡ ጉዳይ ፡ እን ዲቀበል ፡ የሚያስገድደው ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ የመቀበል ፡ ያለመቀበሉ ፡ መብት ፡ የራሱ፡ መሆኑን ፡ የሚገልጽ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ጽሑፍ ፡ ለጊዜው ፡ የለም ። በልማድ ፡ እንደ ምናየው ፡ ከሆነ ፡ ማንኛውም ፡ ጠበቃ ፡ ደንበኛው ፡ የሚያመጣለትን ፡ ነገር ፡ ካልፈ ለገ ፡ አይቀበልም ። ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ አልቀበልም ፡ የሚለው ፡ ለክርክሩ ፡ ከደንበኛው፡ የሚሰጠው ፡ አበል ፡ ዝቅተኛ ፡ ሲሆን ፡ ስለሆነ ፡ ጉዳዩን ፡ ተቀብሎ ፡ በአነስተኛ ፡ አበል ፡ ከሚከራከር ፡ ይልቅ ፡ አለመከራከሩን ፡ ስለሚመርጥ ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ ሊቀ በላቸው ፡ ከማይፈልጋቸው ፡ ውስጥ ፡ «መጥፎ» ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ሊያጋጩ ፡ የሚችሉትንና ፡ ሳይታሰቡ ፡ የሚያመልጡ ፡ ቃላት ፡ መነሻ ፡ ሊሆኑ ፡ የሚችሉ ፡ ነገሮች ፡ ይገኛሉ ። ከደንበኛው ፡ ባላጋራ ፡ ጋር ፡ ዝምድና ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ትውውቅ ፡ ካለው ፡ ጉዳዩን ፡ ላለመቀበል ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ይኖረዋል ። ይህንኑም ፡ ለደንበኛቸው ፡ አስረድተው ፡ ጉዳዩን ፡ የማይቀበሉ ፡ ሞልተዋል ።

ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ በአሜሪካን ፡ አገር ፡ ያለው ፡ ልምድ ፡ እኛ ፡ ከምንከተለው ፡ ልምድ ፡ የተለየ ፡ አይደለም ። በአንድ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ በጥብቅና ፡ መቆም ፡ ወይም ፡ አለመቆሙ ፡ የጠበቃውን ፡ ፍላጐት ፡ የሚጠይቅ ፡ እንጂ ፡ የሚያስገድደው ፡ ሕግ ፡ የለም ። ቢሆንም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ተከሶ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከቀረበና ፡ ጉዳዩ ፡ ከተጀመረ ፡ በኋላ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጠበቃውን ፡ እንዲቆም ፡ ካዘዘው ፡ እንዳይቆም ፡ የሚከለክለው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ምክንያት ፡ ከሌለ ፡ በስተቀር ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ቆሞ ፡ ሊከራከር ፡ ይገደዳል ። እንዲሁም ፡ ገንዘብ ፡ ለሌለው ፡ ደኃ ፡ ሰው ፡ ቆሞ ፡ እንዲከራከር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የጠየቀው ፡ እንደሆነ ፡ ትእዛዙን ፡ ተቀብሎ ፡ መከራከር ፡ ይኖርበታል ።

በእኛ ፡ አገር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ጠበቃን ፡ ለአንድ ፡ ነገር ፡ እንዲቆም ፡ የሚያዘው ፡ ነገሩ ፡ የወንጀል ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ነገር ፡ የተሻሻለው ፡ የኢ ትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፶፪ ፡ ሲደነግግ ፡—

«...ስለራሱም ፡ ለመከላከል ፡ የጠበቃ ፡ ረዳትነት ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ። ነገር ፡ ግን ፡ ተከሳሹ ፡ በራሱ ፡ ችሎታ ፡ ወይም ፡ በገንዘቡ ፡ ጠበቃ ፡ ለመግዛት ፡ ያልቻለ ፡ እንደሆነ ፡ በሚወሰነው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጠበቃ ፡ ያቆምለታል» ፡ ይላል ።

ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ ለአንድ ፡ በወንጀል ፡ ለተከሰሰ ፡ ሰው ፡ ቆሞ ፡ እንዲከ ራከር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ባዘዘው ፡ ጊዜ ፡ ትእዛዙን ፡ ተቀብሎ ፡ በነፃ ፡ ይከራከርለታል ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ እንደገለጽነው ፡ ዳኞች ፡ ጠበቆችና ፡ ሕግ ፡ አስከባሪዎች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚያዝበትን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ እንዲመካከሩበት ፡ የተሰነዘረ ፡ ሐሳብ ፡ አለ ። ይሁንና ፡ ጉዳዩ ፡ አከራካሪ ፡ ሆኗል ። እስከአሁንም ፡ ጠበቆች ፡ ከፍርድ ፡ ሚኒስቴርና ፡ ከከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ጋር ፡ በመጻጻፍ ፡ ላይ ፡ ናቸው ።

ጠበቆች ፡ በትእዛዝ ፡ እንዲቆሙ ፡ የሚያደርገው ፡ አንቀጽ ፡ ፶፪ ።

«...በሚወሰነው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጠበቃ ፡ ያቆምለታል» ይላል። ስለዚህ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ የወጣ ፡ ሕግ ፡ ስለ ሌለ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በቀጥታ ፡ ተከራከሩ ፡ ብሎ ፡ ሊያዝ ፡ የሚያስችለው ፡ ሥልጣን ፡ አከራካሪ ፡ ነው ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አንድን ፡ ጠበቃ ፡ በወንጀል ፡ ተከሶ ፡ በራሱም ፡

ችሎታ ፡ ሆነ ፡ በገንዘቡ ፡ ጠበቃ ፡ ሊያቆም ፡ ላልቻለው ፡ ሰው ፡ ቆሞ ፡ እንዲከራከር ፡ የሚያዝዘው ፡ በየትኛው ፡ ሥልጣኑ ፡ እንደሆነ ፡ መጠይቅ ፡ ቢቀርብ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ መሠረት ፡ ነው ፡ የሚል ፡ መልስ ፡ ይሰጣል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱ፡ አንቀጽ ፡ ፶፪ ፡ የሌላ ፡ ዝርዝር ፡ ሕግ ፡ ምንጭ ፡ እንጂ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በምን ፡ ዓይነት ፡ ሁኔታ ፡ ጠበቆችን ፡ ማዘዝ ፡ እንደሚችል ፡ አይናገርም ። ይሁንና ፡ እስካሁን ፡ ጠበቆች ፡ ከፍርድ ፡ ሚኒስቴርም ፡ ሆነ ፡ ከከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚጻጻፉት ፡ ደብዳቤዎች ፡ ተስፋ ፡ የሚሰጧቸው ፡ ስላልሆኑ ፡ የታዘዙትን ፡ እየተቀበሉ ፡ መከራከር ፡ ላይ ፡ ይገኛሉ ።

በጠበቆች ፡ በኩል ፡ የተዘነጋ ፡ የሚመስለው ፡ የፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ትእዛዝ ፡ ተቀብለው ፡ ወደ ፡ ክርክሩ ፡ ከገቡ ፡ በኋላ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ በነፃ ፡ የቆሙ ፡ ቢሆንም ፡ ጉዳዩን ፡ በጥሞና ፡ ተከታትለው ፡ የጥብቅና ፡ ሥራቸውን ፡ በሚገባ ፡ አለማከናወናቸው ፡ ነው ። መጀመሪያውኑ ፡ ጉዳዩን ፡ ሲቀበሉ ፡ ሙሉ ፡ ፈቃደኛነታቸውን ፡ አያሳዩም ፤ አንዳንዶች ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጋር ፡ ብዙ ፡ ይጨቃጨቃሉ ። አንዳንዶቹ ፡ ጠበቆች ፡ ተከሳሾቹንም ፡ ወኅኒ ፡ ቤት ፡ ሄደው ፡ አያነጋግሩም ። በቀጠሮው ፡ ቀን ፡ ተከሳሹ ፡እምነት ፡ ክህደት ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላልን ፡ ተብለው ፡ ሲጠየቁ ፡ በጊዜ ፡ እጥረት ፡ ምክንያት ፡ ተከሳሹን ፡ አላነጋገርኩትም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ምን ፡ አለ ፡ ይስጥ ፡ ይላሉ ። ዳኞቹም ፡ በዚህ ነገር ፡ እየተናደዱ ፤ የነገሩ ፡ መነሻ ፡ እምነት ፡ ክህደቱ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ እንዴት ፡ ነገሩን ፡ ሳያጠኑት ፡ እምነት ፡ ክህደቱን ፡ እንዲሰጥ ፡ ይመክሩታል ፡ በማለት ፡ ጠበቆችን ፡ ሲወቅሱ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይሰማል ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በአጭሩ ፡ የገለጽነው ፡ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ አንድን ፡ ጉዳይ ፡ ከመቀበሉ ፡ በፊት ፡ መፈጸም ፡ ስለሚገባውና ፡ በእርግጥም ፡ ስለሚፈጽመው ፡ እንዲሁም ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ግዴታ ፡ እንዳለበት ፡ ነው ። አንድ ፡ ጠበቃ ፡ ከደንበኛው ፡ ተዋውሎ ፡ አንድን ፡ ክርክር ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከወሰደ ፡ በኋላ ፡ በፈለገ ፡ ጊዜ ፡ ከነገሩ ፡ መውጣት ፡ ይችላልን ? ይህም ፡ የሚመራን ፡ በጠበቃውና ፡ በደንበኛው ፡ መካከል ፡ የሚፈጸመው ፡ ስምምነት ፡ ተራ ፡ የውል ፡ ስምምነት ፡ ነው ፡ ወይንስ የተለየ ፡ ግዴታን ፡ የሚፈጥር ፡ የውል ፡ ስምምነት ፡ ነው ፡ የሚለው ፡ ነው ። ይህ ፡ ጥያቄ ፡ አከራካሪ ፡ በመሆኑ ፡ በሌሎች ፡ አገሮች ፡ ብዙ ፡ ጽሑፍ ፡ ተጽፈውበታል ። ስለ ፡ ወንጀል ፡ ነገር ፡ አስቀድመን ፡ ባለፉት ፡ ገጾች ፡ ስለዘረዘርን ፡ ወደዚያው ፡ አንመለስም ። ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ ግን ፡ የምንጠቅሳቸው ፡ አንዳንድ ፡ ነገሮች ፡ ይኖራሉ ። በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ጉዳዮች ፡ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ ከደንበኛው ፡ ጋር ፡ ተዋውሎ ፡ ነገሩን ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ በፈለገ ፡ ጊዜ ፡ ከነገሩ ፡ ሊወጣ ፡ ይችላልን ፡ የሚለውን ፡ ጥያቄ ፡ ለመመለስ ፡ በጠበቃና ፡ በደንበኛው ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ በሰፊው ፡ መመርመር ፡ ያስፈልጋል ።

የጠበቃና ፡ የደንበኛው ፡ ግንኙነት ፡ (በአጠቃላይ) ፡ (በሰፊው) ፡ ሲታሰብ ፡ የውክልና ፡ ግንኙነት ፡ ነው ። አንድ ፡ ወኪል ፡ በተወከለበት ፡ ነገር ፡ አንድ ፡ ሶስተኛ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ባይተዋር ፡ ሳይሆን ፡ ልክ ፡ ባለቤቱ ፡ ሊሠራው ፡ ቢችል ፡ ይሠራው ፡ እንደነበር ፡ አድርጐ ፡ መሥራት ፡ አለበት ። የውክልና ፡ ዋና ፡ ዓላማው ፡ ባለቤቱ ፡ በችሎታ ፡ ማጣት ፤ ወይም ፡ በሥራ ፡ ብዛት ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ በማንኛውም ፡ ምክንያት ፡ ሊሠራ ፡ የማይችለውን ፡ ወይም ፡ ሊሠራ ፡ የማይፈቅደውን ፡ ሥራ ፡ እንደራሴ ፡ ሆኖ ፡ እንዲሠራለት ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ በእኔ ፡ ስም ፡ ስለእኔ ፡ ሆኖ ፡ ይሥራልኝ ፡ ብሎ ፡ ሥልጣን ፡ ሰጥቶ ፡ መተካት ፡ ስለሆነ ፡ ወኪሉ ፡ የሚሠራው ፡ ሁሉ ፡ ባለቤቱ ፡ እንደሠራው ፡ ይቆጠራል ። የኢትዮጵያ ፡ የፍትሐብሔር ፡ ሕግም ፡ ይህን ፡ ክፍል ፡ «እንደራሴነት» የሚለው ፡ ለዚሁ ፡ ነው ። ጠበቃ ፡ በሕግ ፡ ረገድ ፡ የተለየ ፡ የሙያ ፡ ችሎታ ፡ ስላለው ፡

ወኪል ፡ የሚሆነው እንዳንድ ፡ ነፃ ፡ ተቋራጭ ፡ መሆኑን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ይደነግጋል ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ፫ኛው ፡ ቮሊዩም ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ ይግባኝ ፡ ባይ ፡ ታደሰ ፡ ድልነሳሁ ፡ መልስ ፡ ሰጭ ፡ በቀለች ፡ ካሣ ፡ በሚለው ፡ መዝገብ ፡ ውስጥ ፡ የሚከተለው ፡ ተተንትኗል ።

«...በኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፮፻፴፪ ፡ እንደተጻ ፈው ፡ ስለ ፡ አእምሮ ፡ ሥራ ፡ ውሎችና ፡ ስለ ፡ ጥብቅና ፡ አገልግሎቶች ፡ እንደሚከተለው ፡ ይደነግጋል ። በዕውቀታቸው ፡ ለማገልገል ፡ ውል ፡ የሚገቡ ፡ ሁሉ ፡ እንደጠበቆችና ፡ ሌሎችም ፡ ውል ፡ የገቡበትን ፡ ግዴታ ፡ ለመፈጸም ፡ በግል ፡ ኃላፊዎችና ፡ ተጠያቂዎች ፡ ናቸው ፡ በማለት ፡ ሕጉ ፡ ግዴታ ፡ ጥሎባቸዋል ። አንቀጽ ፡ ፪ሺ፮፻፴፫ ፡ እንደሚያመለክተው ፡ ግን ፡ ውል ፡ የገቡበት ፡ ግዴታ ፡ መሠረት ፡ የሚፈጸመው ፡ ሥራ ፡ የበረከተና ፡ መጠኑ ፡ የበዛ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ጠበቃው ፡ በራሱ ፡ መሪነትና ፡ ተቆጣጣሪነት፡ የሚሠሩትን ፡ የቅርብ ፡ ረዳቶቹን ፡ እያዘዘ ፡ ግዴታውን ፡ ሊፈጽም ፡ እንደ ሚችል ፡ በሕጉ ፡ ተደንግጓል ።»

«እንዲሁም ፡ ጠበቃውና ፡ ደንበኛው ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ የተሳሰረ ፡ እም ነትና ፡ የተጠበቀ ፡ ምሥጢር ፡ በመካከላቸው ፡ እንዲኖር ፡ ተገቢ ፡ ነው» ።

ሲል ፡ የጠበቃውን ፡ ሥራ ፡ ይገልጻል ። እንግዲህ ፡ የጠበቃውና ፡ የደንበኛው ፡ ግንኙ ነት ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ሲሆን ፡ ጠበቃ ፡ በፈቃዱ ፡ ከጀመረው ፡ ጉዳይ ፡ ሊወጣ ፡ ፈልጎ ፡ ውለ ታውን ፡ ቢሰርዝ ፡ የሚገደድበት ፡ ነገር ፡ የለም ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፮፻፴፰ ፡ ይህንኑ ፡ ይደነግጋል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ለአደረገውም ፡ አገልግሎት ፡ ተመጣጣኝ ፡ ገንዘብ ፡ ብቻ ፡ ለመውሰድ ፡ መብት ፡ እንዳለውና ፡ እንዲሁም ፡ የበለጠ ፡ አበል ፡ አስቀድሞ ፡ የወሰደ ፡ ከሆነ ፡ ደንበኛው ፡ የከፈለው ፡ እንዲመለስ ፡ መጠየቅ ፡ ይችላል ።

እንግዲህ ፡ በዚህ ፡ አነጋገር ፡ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ አንድ ፡ ጉዳይ ፡ ተቀብሎ ፡ ሊነጋ ገር ፡ የሚገባው ፡ ውል ፡ የሚያሳድርበት ፡ ግዴታ ፡ እስከዚህም ፡ ድረስ ፡ ከሌላው ፡ ውል ፡ የተለየ ፡ አይደለም ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ጠበቃው ፡ ከነገሩ ፡ ውስጥ ፡ እስካለ ፡ ድረስ ፡ ብዙ ፡ ግዴታዎች ፡ አሉበት ። ይህ ፡ በሌላውም ፡ የስምምነት ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ የተለ መደና ፡ ያለ ፡ ነው ። ይሁንና ፡ የጥብቅና ፡ ሞያ ፡ ስለ ፡ እውነት ፡ ፍለጋ ፡ የሚደረገውን ፡ ጥረት ፡ ለማውጣት ፡ የሚያስችል ፡ ታላቅ ፡ ሥራ ፡ ስለሆነ ፡ የጥብቅና ፡ ሞያቸውን ፡ ለማበርከት ፡ ስምምነት ፡ የሚያደርጉ ፡ ጠበቆች ፡ የገቡበትን ፡ ግዴታ ፡ አክብረው ፡ እንዲገኙ ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ምግባር ፡ ያስገድዳቸዋል ። ጥብቅና ፡ እንደንግድ ፡ የሚታይ ፡ ሥራ ፡ ስላልሆነ ፡ የገንዘብን ፡ ትርፍ ፡ ብቻ ፡ በማየት ፡ አለበቂ ፡ ምክንያት ፡ የጀመሩ ትን ፡ ነገር ፡ ግብ ፡ ሳያደርሱ ፡ መካከል ፡ ላይ ፡ ጥሎ ፡ መሄድ ፡ ተገቢ ፡ አይደለም ። ጥብቅናን ፡ እንደ ፡ ንግድ ፡ ሥራ ፡ ይዘው ፡ ደንበኞቻቸውን ፡ ከውላቸው ፡ ውጪ ፡ ገን ዘብ ፡ በማስጨመር ፤ ገንዘብ ፡ የተቀበሉበትን ፡ ጉዳይ ፡ ችላ ፡ በማለትና ፡ ትኩስ ፡ ትኩሱን ፡ ብቻ ፡ በማባረር ፡ ደንበኞቻቸውን ፡ የሚያበሳጩ ፡ሞልተዋል ። እንዲሁም፡ ብዙዎችም ፡ ጠበቆች ፡ አጀንዳቸው ፡ ሙሉ ፡ መሆኑን ፡ እያወቁ ፡ ሰባትና ፡ ስምንት ፡ ፋይል ፡ በተለያዩ ፡ ችሎቶች ፡ በአንድ ፡ ቀን ፡ በማስቀጠር ፡ ሁሉንም ፡ ለማዳረስ ፡ ባለመቻላቸው ፡ በደንበኞቻቸው ፡ ላይ ፡ ኪሣራ ፡ የሚያስቀርጡ ፡ አያሌ ፡ ጠበቆች ፡ እንዳሉ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ደንበኞቻቸው ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የማይመጣ ፡ ከሆነም ፡ ባለመቅረባቸው ፡ መዝገቡን ፡ የሚያዘጉበትና ፡ ወይንም ፡ በሌለበት ፡ የሚያስፈርዱ

በት ፡ እንዲሁ ፡ ይገኛሉ ። ደንበኞቸውን ፡ ጉዳት ፡ ላይ ፡ ከመጣላቸውም ፡ በላይ ፡ የነገር ፡ መጐተት ፡ ምክንያት ፡ ሊሆኑ ፡ ከሚችሉት ፡ ምክንያቶች ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ የእነርሱ በቀጠሮ ፡ አለመገኘት ፡ ነው ። በቀጠሮው ፡ ቢገኙም ፡ እንኳን ፡ ለክርክሩ ፡ በቂ ፡ ዝግጅት ፡ አድርገው ፡ ስለማይመጡ ፡ መልስ ፡ ወይም ፡ የመልስ ፡ መልስ ፡ መስጠት ፡ ሲኖርባቸው ፡ ለጊዜው ፡ እዚያው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ በዋዜማው ፡ ለይ ድረስ ፡ የተጫጫረ ፡ መልስ ፡ ስለሚያቀርቡ ፡ ደንበኞቸውን ፡ ጉዳት ፡ ላይ ፡ ከመጣላቸውም ፡ ሌላ ፡ የዳኝነትን ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ይረዳሉ ፡ ተብሎ ፡ የተጣለባቸውን ፡ ኃላፊነት ፡ ከንቱ ፡ ያደርጉታል ።

በወንጀል ፡ ነገር ፡ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ ፡ የቆመ ፡ እንደሆነ ፡ በቀላሉ ፡ ሊወጣ ፡ አይችልም ። በቂ ፡ ምክንያት ፡ ካለው ፡ ግን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አመልክቶ ፡ ሲቀበለው ፡ ሊወጣ ፡ ይችላል ። አንዳንድ ፡ ጠበቆች ፡ እውነቱን ፡ ደብቀው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክርክሩ ፡ በሚቀጥልበት ፡ ጊዜ ፡ በክርክሩ ፡ ውስጥ ፡ ለመቀጠል ፡ ስለሚቸገሩ ፡ ከጉዳዩ ፡ እንውጣ ፡ በማለት ፡ የሚያመለክቱ ፡ አሉ ። ምናልባትም ፡ አንድ ፡ ተከሳሽ ፡ ወንጀል ፡ መፈጸሙ ፡ የማያጠራጥር ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ጠበቃው ፡ ይህን ፡ ዓይነቱን ፡ ሰው ፡ ለመርዳት ፡ መሞከሩ ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ ጋር ፡ የሚጋጭ ፡ ይመስለው ፡ ይሆናል ። እርግጥ ፡ አንድ ፡ ወንጀል ፡ የሠራ ፡ ሰው ፡ ተገቢውን ፡ ቅጣት ፡ ሳይቀበል ፡ ሲቀር ፡ ለኅሊናም ፡ ሆነ ፡ ለሕጋዊ ፡ አስተሳሰብ ፡ ትክክለኛ ፡ አይደለም ። አንድ ፡ ጠበቃ ፡ ደንበኛው ፡ ወንጀል ፡ የሠራ ፡ ቢመስለውም ፡ እንኳን ፡ የራሱን ፡ ስሜት ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ በመተው ፡ ለተከሰሰው ፡ ሰው ፡ የሚገባውን ፡ ሕጋዊ ፡ መከላከያ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ የተከሳሹን ፡ ጥፋተኛነት ፡ ጠበቃው ፡ ቢገነዘብም ፡ ማየት ፡ ያለበት ፡ ተከሳሹ ፡ ይህን ፡ ጥፋት ፡ ሊፈጽም ፡ የቻለው ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ እንደሆነ ፤ ራሱን ፡ ለማዘዝ ፡ የሚችል ፡ ወይም ፡ የማይችል ፡ መሆኑን ፡ አእምሮው ፡ ትክክለኛ ፡ መሆን ፡ አለመሆኑን ፡ ሳያስብና ፡ ሳያውቀው ፡ ድርጊቱን ፡ የፈጸመ ፡ መሆን ፡ አለመሆኑን ፡ ይህንንና ፡ ይህንን ፡ የመሳሰሉ ፡ ምክንያቶች ፡ በማፍለቅ ፡ ሊደገፍ ፡ የሚችልበትን ፡ መከላከያ ፡ ማዘጋጀት ፡ አለበት ። ተከሣሹ ፡ ወንጀሉን ፡ የፈጸመ ፡ መሆኑን ፡ ጠበቃው ፡ ቢያምንም ፡ የወንጀሉን ፡ አፈጻጸም ፡ ማስረዳት ፡ ያለበት ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ በመሆኑ ፡ የጠበቃው ፡ ጥረት ፡ ያለ ፡ አገባብና ፡ ያለ ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ በተከሳሹ ፡ ላይ ፡ እንዳይፈረድበት ፡ መሞከር ፡ መሆን ፡ አለበት ። መጨረሻም ፡ በተከሳሹ ፡ ላይ ፡ የተመሰከረበት ፡ ቢሆንም ፡ እንኳን ፡ የጠበቃው ፡ ግዳጅ ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ አይቆምም ። የተከሳሹ ፡ ጥፋት ፡ የመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ጥፋቱ ፡ ሊሆን ፡ ስለሚችል ፡ ጠባዩ ፡ ወንጀሉን ፡ ከፈጸመበት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ መሻሻል ፡ ያሳየና ፡ የተጸጸተ ፡ መሆኑን ፡ የሚመለከት ፡ መሆኑንና ፡ ወደፊትም ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ እስር ፡ ቤት ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ ማቆየት ፡ ኅብረተ ፡ ሰቡን ፡ የማይጠቅምና ፡ በተከሳሹም ፡ ላይ ፡ የቅጣቱ ፡ መብዛት ፡ ምንም ፡ የማይጨምርለት ፡ መሆኑን ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ማመልከት ፡ ቅጣቱ ፡ እንዲቃለልለት ፡ ወይም ፡ በአመክሮ ፡ እንዲታለፍና ፡ ይህንንና ፡ ይህንን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ማሳሰብና ፡ ማመልከት ፡ ተገቢ ፡ ተግባሩ ፡ ነው ።

ጠበቃ ፡ ለአንዱ ፡ ደንበኛው ፡ እስከመጨረሻው ፡ ድረስ ፡ መታገል ፡ ቢኖርበትም ፡ ደንበኛው ፡ ለምሳሌ ፡ በሐሰት ፡ የመሐላ ፡ ቃል ፡ ለመስጠት ፡ ሙከራ ፡ ማድረጉን ፡ ቢያውቅ ፡ ሊያስጠነቅቀውና ፡ እንደዚህ ፡ ዓይነቱን ፡ ነገር ፡ እንዲያቆም ፡ ነግሮ ፡ ምክሩ ፡ ተቀባይነት ፡ ሲያጣ ፡ ሁኔታው ፡ ከዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ጋር ፡ የሚጋጭ ፡ በመሆኑ ፡ ከነገሩ ፡ መውጣት ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ተገቢ ፡ እርምጃ ፡ መውሰድ ፡ ይችላል ። ይህም ፡ ከደንበኛው ፡ እንደሚያጣላው ፡ አያጠራጥርም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ጠበቃ ፡

እውነትን ፡ ፍለጋ ፡ ለሚደረገው ፡ ጥረት ፡ ረዳት ፡ ስለሆነ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ጥቅም ፡ መጠበቅና ፡ ሞያውን ፡ ማስከበር ፡ አለበት ።

ጠበቃው ፡ ለደንበኛው ፡ ያለበትን ፡ ግዴታ ፡ ከመደምደማችን ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ልናብራራው ፡ የሚገባ ፡ ነጥብ ፡ አለ ። ይኸውም ፡ ጠበቃ ፡ ለአንድ ፡ ደንበኛ ፡ ቆሞ ፡ ሲከራከር ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፡ ነገሩን ፡ አስወስኖ ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፡ ይህ ፡ የቀድሞ ፡ ደን በኛው ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ ሙግት ፡ ቢኖረው ፡ ለዚሁ ፡ ለሌላው ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ ቆሞ ፡ ይህንኑ ፡ የቀድሞ ፡ ደንበኛውን ፡ ይሞግተዋልን ፡ የሚል ፡ ጥያቄ ፡ ነው ። ለም ሳሌ ፡ በካናዳ ፡ ጠበቃ ፡ የድሮ ፡ ደንበኛውን ፡ አይፈልገው ፡ እንደሆነ ፡ ማስፈቀድ ፡ አለበት ፡ የሚል ፡ አስተያየትና ፡ ልማድ ፡ አለ ። ይሁንና ፡ የእኛ ፡ ጠበቆች ፡ የሚመለ ከቱት ፡ ጥቅማቸውን ፡ ስለሆነ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ደንበኛዬ ፡ ነበር ፡ ብለው ፡ ፈጽሞ ፡ እንቢ ፡ አይሉም ። ይህ ፡ ደንበኛ ፡ ተባራሪ ፡ ከሆነ ፡ ምንም ፡ ሳያቅማማ ፡ ለሌላው ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ ቆሞ ፡ ይሞግተዋል ። ይህም ፡ የውክልና ፡ ሥልጣንን ፡ ይመለከ ታል ። ውክልናው ፡ ለአንድ ፡ ጉዳይ ፡ ብቻ ፡ ከነበረ ፡ የቀድሞ ፡ ደንበኛን ፡ መሞገት ፡ የተለመደ ፡ ሆኗል ። ጠቅላላ ፡ የውክልና ፡ ሥልጣን ፡ ቢኖረውም ፡ እንኳ ፡ ጥቅሙን ፡ ተመልክቶ ፡ ውክልናውን ፡ አውርዶ ፡ ወደ ፡ አዲሱ ፡ ደንበኛ ፡ የሚሄድ ፡ ሞልቷል ። የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ አሠራር ፡ ከሕግ ፡ ሥነ ፡ ምግባር ፡ ወጪ ፡ ነው ። ጠበቃው ፡ ከድሮ ፡ ደንበኛው ፡ አስቀድሞ ፡ በነበራቸው ፡ ግንኙነት ፡ ምክንያት ፡ ብዙ ፡ ምስጢር ፡ ማወቅ ፡ ስለሚችል ፡ እንደገና ፡ ሲሞግተው ፡ ሊጎዳው ፡ ይችላል ። ስለዚህ ፡ ማስፈቀዱ ፡ ተገቢ ነው ።

## አንድ ፡ ጠበቃ ፡ ለሌላው ፡ ጠበቃ ፡ ያለበት ፡ ግዴታ ፤

አንድ ፡ ጠበቃ ፡ ለሌላው ፡ ጠበቃ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ግዴታና ፡ ኃላፊነት ፡ አለበት ፤ ምንስ ፡ ያህል ፡ ግዴታውን ፡ ያከብራል ፡ የሚለውን ፡ ጥያቄ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ እንመ ረምራለን ። ከጥቂት ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ የሙግት ፡ መክፈቻ ፡ ስድብ ፡ ነበር ፡ ይባ ላል ። አንዱ ፡ ጠበቃ ፡ ሌላውን ፡ ተከራካሪ ፡ ጠበቃና ፡ ባላጋራውን ፡ ካልሰደበና ፡ ካላ ዋረደ ፡ ደንበኛው ፡ ፈጽሞ ፡ አይደሰትበትም ። አሁን ፡ ግን ፡ ጠበቆች ፡ ለደንበኞቻ ቸው ፡ ጉዳይ ፡ ሁሉ ፡ ሲሰዳደቡና ፡ ሲጣሉ ፡ መዋሉ ፡ ፍሬ ፡ የሌለው ፡ መሆኑን ፡ በመ ረዳትና ፡ በትምህርትም ፡ ኃይል ፡ የሚያጣላቸው ፡ ነገር ፡ አለመኖሩን ፡ በማወቅ ፡ ወደ ፡ መግባባት ፡ ገደማ ፡ ናቸው ። ይሁንና ፡ በጠበቆች ፡ መካከል ፡ ትኅትና ፡ ቅን ፡ ልቦና ፤ የወዳጅነት ፡ መንፈስ ፡ መኖር ፡ ይገባዋል ። ይህ ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ መጠኑ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነው ፡ የሚለውን ፡ ጥያቄ ፡ መመለስ ፡ ተገቢ ፡ ነው ። ትኅትና ፡ ይታያል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከልብ ፡ የመነጨ ፡ አይደለም ፤ እንደምናየው ፡ አንዱ ፡ ጠበቃ ፡ የሌላውን ፡ ችሎታና ፡ እውቀት ፡ ሲንቅና ፡ ሲያንኳስስ ፡ ይሰማል ። ይህ ፡ አድራጐት ፡ ከጠበቆች ፡ ሥነ ፡ ምግባር ፡ ደንብ ፡ ውጭ ፡ ነው ። በጠበቆች ፡ መካከል ፡ ትኅትናና ፡ የወንድማማ ችነት ፡ መንፈስ ፡ መኖር ፡ ይገባዋል ። ለምሳሌ ፡ በአሜሪካን ፡ አገር ፡ በየጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ የሚገኙት ፡ ጥቂት ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበሮች ፡ በውስጥ ፡ ደንባቸው ፡ ውስጥ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በሞት ፡ ለተለየ ፡ ጠበቃ ፡ ቤተሰቦች ፡ ወይም ፡ ለሚቹ ፡ ቤት ፡ ዘመዶች፡ ዋጋ ፡ ሳይጠይቁ ፡ በነፃ ፡ ምክር ፡ መስጠትና ፡ የጥብቅና ፡ አገልግሎት ፡ ማበርከት ፡ የተደነገገ ፡ ነው ። በጠበቆች ፡ መካከል ፡ ቅን ፡ ልቦና ፡ መኖር ፡ ይገባዋል ። ይኸውም ፡ በብዙዎች ፡ አገሮች ፡ የጠበቆች ፡ ሥነ ፡ ምግባር ፡ ደንብ ፡ በግልጽ ፡ የተደነገገ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ የካናዳ ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ የሥነ ፡ ምግባር ፡ ደንብ ፡ ቁጥር ፡ ፬ (፪) እን ዲህ ፡ ይላል ። «ጠበቃ ፡ የደንበኛውን ፡ ጥቅምና ፡ ትክክለኛ ፡ ፍትሕ ፡ የማያጓድል ፡ ከሆነ ፡ ለሌላው ፡ ተከራካሪ ፡ ጠበቃ ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ቀናና ፡ ምቹ ፡ እንዲሆን ለት ፡ መጣር ፡ ይገባዋል ።» ሆኖም ፡ በሀገራችን ፡ እንደምናየው ፡ በጠበቆች ፡ መካከል

ቅን ፡ ልቦና ፡ የለም ፤ ለምሳሌ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጉዳዩን ፡ የሚቀጥርበት ፡ ቀን ፡ ለአንደ ኛው ፡ ጠበቃ ፡ ምቹ ፡ በማይሆንበት ፡ ጊዜ ፡ ለሌላው ፡ ተከራካሪ ፡ ጠበቃ ፡ ቀኑ ፡ ቢለ ወጥ ፡ ምንም ፡ የሚጐዳው ፡ ነገር ፡ ሳይኖር ፡ እንዲሁ ፡ እንቅፋት ፡ ለመሆን ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ የቀጠሮውን ፡ ቀን ፡ በመቃወም ፡ ሌላው ፡ ጠበቃ ፡ ችግር ፡ ላይ ፡ እንዲወድቅ ፡ ይጥራል ። ይኸውም ፡ ፋይሉን ፡ ለማዘጋት ፤ ኪሣራ ፡ ለማስቀረጥ ፤ በጠቅላላው ፡ ሌላው ፡ ጠበቃ ፡ በሌለበት ፡ ለመጠቀም ፡ ነው ። አንዳንዴም ፡ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ በቀ ጠሮው ፡ ቀን ፡ ባለመቅረቡ ፡ የሚቀጥለውን ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ ያልሰማ ፡ ሆኖ ፡ ሌላውን ፡ ተከራካሪ ፡ ጠበቃ ፡ ለመቼ ፡ እንደተቀጠረ ፡ ሲጠይቀው ፡ በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ይመስለኛል፡ የሚል ፡ አጠራጣሪ ፡ መልስ ፡ በመስጠት ፡ ሊጐዳው ፡ ይሞክራል ። ይህ ፡ አለመተባ በር ፡ የጠበቆችን ፡ ሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ያጓድላል ፡ እንጂ ፡ ለቆሙበት ፡ ጉዳይ ፡ በምንም ፡ አይረዳም ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ጠበቆች ፡ በችሎት ፡ ፊት ፡ ለመከራከር ፡ ሲቀርቡ ፡ መደ ማመጥና ፡ ተራ ፡ መጠበቅ ፡ አለባቸው ። እንደሚታየው ፡ ግን ፡ ለመናገር ፡ በመሽቀ ቀዳደም ፡ ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ ትተው ፡ እርስ ፡ በእርሳቸው ፡ ሲነታረኩ ፡ ከመቀያየም ፡ ሌላ የፍርድ ፡ ቤቱንና ፡ የራሳቸውን ፡ ጊዜ ፡ በከንቱ ፡ ያጠፋሉ ። በተጨማሪም ፡ ሁለቱ ፡ ባለጉዳዮች ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ቢቀያየሙ ፡ ጠበቆቹ ፡ ለቆሙበት ፡ ክርክር ፡ እንጂ ፡ ባለጉዳዮቹን ፡ መስለው ፡ ቂም ፡ ለመበቀል ፡ በመካከላቸው ፡ የጥላቻ ፡ መንፈስ ፡ መፍ ጠር ፡ የለባቸውም ። ጠበቆች ፡ ለአንድ ፡ ዓይነት ፡ ዓላማ ፡ የቆሙ ፡ ሰዎች ፡ በመሆና ቸው ፡ በመካከላቸው ፡ የመተባበርና ፡ የወንድማማችነት ፡ መንፈስ ፡ መኖር ፡ ይገባዋል ። ቀደም ፡ ብለን ፡ እንዳየነው ፡ ጥብቅና ፡ ንግድ ፡ አይደለም ። የንግድ ፡ ሥራ ፡ ዓላ ማው ፡ ትርፍ ፡ ስለሆነ ፡ ነጋዴዎች ፡ ብዙ ፡ ዓይነት ፡ ዘዴ ፡ በመጠቀም ፡ አንዱ ፡ የአን ደኛውን ፡ ደንበኛ ፡ ቢወስድበት ፡ ፈጽሞ ፡ ነውር ፡ አይደለም ። ጥብቅና ፡ ሞያ ፡ በመ ሆኑ ፡ የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ አድራጐት ፡ በሕግ ፡ ሥነ ፡ ምግባር ፡ በጣም ፡ የተከለከለ ፡ ነው ። አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ እንደምናየው ፡ አንዱ ፡ ጠበቃ ፡ የሌላውን ፡ ጠበቃ ፡ ችሎታ ፡ በማንኳሰስ ፡ ከባላጋራ ፡ ጋር ፡ ይስማማል ፤ ከሁለት ፡ ፊት ፡ ይበላል ፡ እያለ ፡ በማዋረ ድና ፡ ስሙን ፡ በማጥፋት ፡ ደንበኞቹን ፡ በማሸሽና ፡ ወደርሱ ፡ እንዲመጡ ፡ በማድ ረግ ፡ ሊጠቀም ፡ ይሞክራል ።

በችሎት ፡ ውስጥ ፡ ጠበቃው ፡ በሚከራከርበት ፡ ጊዜ ፡ ባለማስተዋልም ፡ ሆን ፡ በችኰላ ፡ አግባብ ፡ የሌለውን ፡ አንቀጽ ፡ ቢጠቅስ ፡ ወይም ፡ ስህተት ፡ ቢያደርግ ፡ ሌላው ፡ ተከራካሪ ፡ ጠበቃ ፡ ወዲያውኑ ፡ ሊያገንን ፤ ሊተቸውና ፡ ሊያስቅበት ፡ ይሞክ ራል ። ይኸውም ፡ ቂም ፡ ለመውጣት ፤ የሚፈልገውን ፡ ደንበኛውን ፡ ለማስደሰትና ፤ የተሻለ ፡ ጠበቃ ፡ መስሎ ፡ ለመታየት ፡ በማሰብ ፡ የሚያደርገው ፡ ነው ፡ ከማለት ፡ በስ ተቀር ፡ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ የሚኖረው ፡ አይመስልም ። ይህም ፡ በሕግ ፡ ሥነ ፡ ምግባር ፡ የተከለከለ ፡ አድራጐት ፡ ነው ። የበላይነትና ፡ የበታችነት ፡ ስሜት ፡ በጠበቆች ፡ መካ ከል ፡ መፈጠር ፡ የለበትም ። ስለዚህ ፡ በጠቅላላው ፡ ሌላው ፡ ተከራካሪ ፡ ወገን ፡ ባለ ማስተዋልና ፡ በችኰላ ፡ ምክንያት ፡ በሚያደርገው ፡ አነስተኛ ፡ ስህተት ፡ ወዲያው ፡ ከአፉ ፡ ቀልቦ ፡ ማሳጣት ፡ ፈጽሞ ፡ ተገቢ ፡ ድርጊት ፡ አይደለም ።

ጠበቃ ፡ ለሌላው ፡ ጠበቃ፡ ካለበት ፡ ግዴታ ፡ አንዱ ፡ ደግሞ፡ በሚከራከሩበት፡ ጉዳይ፡ የተከራካሪውን ፡ ጠበቃ ፡ ፈቃድ ፡ ሳይጠይቅ ፡ በቀጥታ ፡ ባለጉዳዩን ፡ ማለት ፡ የደንበ ኛውን ፡ ባላጋራ ፡ ማነጋገር ፡ ነው ። አንዳንድ ፡ ጠበቆች ፡ ግን ፡ ሌላውን ፡ ተከራካሪ ፡ ጠበቃ ፡ አልፈውና ፡ ዘለው ፡ ደንበኛውን ፡ ይህን ፡ ጉዳይ ፡ በዕርቅ ፡ ብንጨርሰው ፡ አይ ሻልም ፡ ወይ ፡ እያሉ ፡ የሚያነጋግሩና ፡ የሚያግባቡ ፡ ይገኛሉ ። ይኸውም ፡ ጠበቃው ፡ የገባበት ፡ እንደሆነ ፡ ነገሩን ፡ ያከብደዋል ፤ ወይም ፡ አይስማማበትም ፡ ብለው ፡ በማ መን ፡ ነው ። አንዳንዶቹም ፡ ባለጉዳዩን ፡ ለጠበቃህ ፡ አትንገረው ፡ እርሱ ፡ የገባበት ፡ እንደሆነ ፡ እሺ ፡ አይልም ፡ ያስቸግራል ፤ እያሉ ፡ ባለጉዳዮቹን ፡ ይመክሯቸዋል ። ጉዳ

ዩን ፡ እንደተመከረው ፡ ለጠበቃው ፡ ሳይነግር ፡ በዕርቅ ፡ ለመጨረስ ፡ ከተስማሙ ፡ በኋላ ፡ ባለጉዳዩ ፡ ከጠበቃው ፡ ጋር ፡ ስለአገልግሎት ፡ ዋጋ ፡ ባላቸው ፡ ስምምነት ፡ ስለ ፡ አከፋፈሉ ፡ ችግር ፡ ስለሚገጥመው ፡ በሙሉ ፡ እንዳይጠይቀው ፡ ወደ ፡ ጠበቃው ፡ አማላጅ ፡ ይልክበታል ። እንግዲህ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ችግር ፡ የሚያስከትለው ፡ ሌላው ፡ ጠበቃ ፡ የሕጉን ፡ ሥነ ፡ ምግባር ፡ በመተላለፍ ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ መንገድ ፡ በመከተሉ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ በጠቅላላው ፡ አነጋገር ፡ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ የዳኝነትን ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ይረዳል ፡ ተብሎ ፡ ከተሾመና ፡ ጥብቅናን ፡ የሚያኮራ ፡ ሞያ ፡ አድርጎ ፡ ከያዘ ፡ ቀደም ፡ ብለን ፡ እንደገለጽነው ፡ ለመንግሥትና ፡ ለሕዝብ ፤ ለፍርድ ፡ ቤት ፤ ለደንበኛውና ፡ ለሌላው ፡ ጠበቃ ፡ ያሉበትን ፡ ግዴታዎችና ፡ ኃላፊነቶች ፡ በሚገባ ፡ ማክበርና ፡ መፈጸም ፡ ስላለበት ፡ ከላይ ፡ የተገለጸውን ፡ ጉድለት ፡ ካላስወገደ ፡ በመንግሥት ፡ የተጣለበትን ፡ አደራ ፡ ከግብ ፡ አደረሰ ፡ ለማለት ፡ አያስደፍርም ።

ስለዚህ ፡ ወደ ፡ ጥብቅና ፡ ሥራ ፡ የሚሠማሩት ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ለጥቅም ፡ ፍለጋ ፡ ሳይሆን ፡ ሕጉ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፤ ኅብረተ ፡ ሰቡ ፡ እንዲረዳ ፡ ከፍተኛ ፡ ኃላፊነት ፡ እንደተጣለባቸው ፡ ማወቅና ፡ ሞያው ፡ እንዲከበር ፡ መጣር ፡ አለባቸው ።

በአሁኑ ፡ ዓይነት ፡ አቋም ፡ በጠበቆች ፡ መካከል ፡ የመተባበርና ፡ የመፈቃቀድ ፡ እንዲሁም ፡ የመከባበር ፡ መንፈስ ፡ ሊኖር ፡ አይችልም ። ለምሳሌ ፡ የእንግሊዝ ፡ አገር ፡ ጠበቆች ፡ የጠነከረ ፡ የአንድነት ፡ መንፈስ ፡ በጣም ፡ የሚደነቅ ፡ ነው ። ይህንኑም ፡ የትብብር ፡ መንፈስ ፡ ከሚያጠነክሩት ፡ ምክንያቶች ፡ መካከል ፡ ጥቂቶች ፡ በየቀኑ ፡ ያላቸው ፡ ግንኙነትና ፡ እንዲሁም ፡ በየጊዜው ፡ የሚደረገው ፡ የመገናኛ ፡ የምሳ ፡ ወይም ፡ የራት ፡ ግብዣ ፡ ነው ። ከሀገራችን ፡ ምሳሌ ፡ ብንጠቅስ ፤ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ በነጋዴዎች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ የራት ፡ ግብዣ ፡ በማድረግ ፡ አዋቂዎች ፡ እየተጠሩ ፡ ጠቃሚ ፡ ንግግርና ፡ ውይይት ፡ ይደረጋል ። ጠበቆችም ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆነ ፡ ዝግጅት ፡ ቢያደርጉ ፡ ሞያቸውን ፡ ለማስከበር ፡ በመካከላቸውም ፡ የአንድነት ፡ መንፈስ ፡ ለመፍጠር ፡ ይቻላል ።

ጠበቆች ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ አካላት ፡ ያላቸውን ፡ ግዴታ ፡ ከመደምደማችን ፡ በፊት ፡ ለሞያው ፡ የአለባቸውን ፡ ግዴታ ፡ መመልከት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ቀደም ፡ ብለን ፡ እንደገለጽነው ፡ ሁሉ ፡ ጥብቅና ፡ ክብር ፡ ያለው ፡ ሞያ ፡ ነው ፤ ከንግድ ፡ ሥራም ፡ እንዴት ፡ እንደሚለይ ፡ አይተናል ። አንድ ፡ ጠበቃ ፡ የተወሰኑትን ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ምግባር ፡ ማክበርና ፡ ሌሎችም ፡ ጠበቆች ፡ ማክበራቸውን ፡ መከታተል ፡ አለበት ። የካናዳ ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ምግባር ፡ ደንብ ፡ ቁጥር ፡ ፫/፩ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ።

> «የሞያውን ፡ ክብርና ፡ ከፍተኛነት ፡ መጠበቅ ፡ ግዴታ ፡ ነው ፤ እንዲሁም ፡ አለ ፡ ፍርሃትና ፡ አለአድልዎ ፡ ደንበኛ ፡ የዳኝነት ፡ መልክ ፡ ባለው ፡ ድርጅት ፡ ፊት ፡ ከሞያ ፡ ውጭ ፡ ወይም ፡ የማታለል ፡ ተግባር ፡ አንድ ፡ የሞያው ፡ አባል ፡ ሲፈጽም ፤ ማጋለጥ ፡ አለበት ፤ እንዲሁም ፡ የሞያው ፡ አባል ፡ ደንበኛውን ፡ በድኋል ፡ በሚባልበት ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ ሳያመነታ ፡ ጉዳዩን ፡ ተቀብሎ ፡ መቆም ፡ አለበት» ።

በሌሎችም ፡ አገሮች ፡ ተመሳሳይ ፡ ደንቦች ፡ እንዳሉ ፡ አይጠረጠርም ። የእኛ ፡ አገር ፡ ጠበቆች ፡ ሞያውን ፡ እንደ ፡ ንግድ ፡ ስለሚቆጥሩት ፡ የሚገባውን ፡ ክብር ፡ ሊያገኝ ፡ አልቻለም ። ሆኖም ፡ አሁን ፡ በመቋቋም ፡ ላይ ፡ የሚገኘው ፡ የአዲስ ፡ አበባ ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ በሞያው ፡ ሥራ ፡ ከተሰማሩት ፡ ጠበቆች ፡ በሙሉ ፡ እንኳ ፡ ባይሆን ፡ የአብዛኞቹን ፡ ድጋፍ ፡ ቢያገኝ ፡ እና ፡ ጠበቆች ፡ አንድ ፡ አቋም ፡ ይዘው ፡ በአንድ ፡ ድምፅ ፡ ቢናገሩ ፡ አዳማጭ ፡ የግድ ፡ ማግኘት ፡ ይችላሉ ። የተበላሹትን ፡ ነገሮች ፡

ሁሉ ፡ ለማረምና ፡ ሞያውን ፡ ፈጽሞ ፡ ንጹህ ፡ በማድረግ ፡ ሕዝቡ ፡ በማኅበሩ ፡ ላይ ፡ እምነት ፡ እንዲጥልበት ፡ ለማድረግ ፡ ያስችላል ። በአሁኑ ፡ ይዞታ ፡ ግን ፡ ጠበቆች ፡ የሚገባቸውን ፡ ክብር ፡ ያላገኙና ፡ ምንም ፡ እምነት ፡ ያልተጣለባቸው ፡ ናቸው ። በሌላ ፡ አገር ፡ ጠበቃ ፡ አንደ ፡ አንድ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣን ፡ ይቆጠራል ። በሀገራችን እንኳ ፡ በአሥመራ ፡ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ የፈለገውን ፡ መዝገብ ፡ ከሬጅስትራሩ ፡ ቢሮ ፡ ገብቶ ፡ ለማገላበጥ ፡ አስፈላጊ ፡ ከሆነም ፡ ከችሎት ፡ ወደ ፡ ችሎት ፡ በራሱ ፡ ኃላፊነት ፡ ሊወስድ ፡ ይችላል ። ይህ ፡ መብት ፡ ደንበኛው ፡ የለውም ፤ ምክንያቱም ፡ የሚጠቅመውን ፡ ማስረጃ ፡ ያጠፋል ፤ ይወስዳል ፡ ተብሎ ፡ ስለሚገመት ፡ ነው ። ጠበቃው ፡ ግን ፡ ትልቅ ፡ ኃላፊነት ፡ የተጣለበት ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ስለሚታመን ፡ የፈለገውን ፡ መዝገብ ፡ መመልከት ፡ ይችላል ። በሌሎች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ግዛቶች ፡ ግን ፡ መዝገብ ፡ የሚሄደው ፡ በተላላኪ ፡ እጅ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ጠበቃ ፡ የተላላኪን ፡ ያህል ፡ እንኳን ፡ እምነት ፡ የተጣለበት ፡ አይደለም ፡ ማለት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ የጥብቅና ፡ ሞያ ፡ አስቀድሞ ፡ ንጹሕ ፡ ሲሆንና ፡ ጠበቃው ፡ ክብር ፡ የሚገባው ፡ መሆኑን ፡ እራሱ ፡ ጠበቃው ፡ ሲያሳይና ፡ ሞያውን ፡ ሲያስከብር ፡ ሌሎችም ፡ ለጥብቅና ፡ ሙያ ፡ ከፍተኛ ፡ ሥፍራ ፡ እንደሚሰጡት ፡ አይጠረጠርም ። ስለዚህ ፡ አሁን ፡ ካለንበት ፡ ችግር ፡ ለመውጣት ፡ መፍትሔዎቹ ፡ ብዙ ፡ ሊሆኑ ፡ ሲችሉ ፡ ለዘለቄታው ፡ መሠረታዊ ፡ መፍትሔው ፡ ግን ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ ብቻ ፡ ነው ።

## የቅጣት ፡ እርምጃዎች ፤

በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ጥብቅና ፡ አቋም ፡ ስንመረምር ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ የጥብቅና ፡ ፈቃድ ፡ ሲጠይቅ ፡ አስቀድሞ ፡ ጠባዩ ፡ መልካም ፡ መሆኑ ፡ መረጋገጥ ፡ እንዳለበት ፡ ገልጸናል ።

ወደ ፡ ጥብቅና ፡ ሥራ ፡ ከተሰማራም ፡ በኋላ ፡ ይህንኑ ፡ መልካም ፡ ጠባዩን ፡ መልቀቅ ፡ የለበትም ። ጠበቆች ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በሙያቸው ፡ ምክንያት ፡ ከተራው ፡ ሰው፣ የተለዩ ፡ ግዴታዎች፡ እንዳሉባቸው ፡ ብናውቅም ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜም ፡ ይህንኑ ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ምግባር ፡ ፈጽሞ ፡ እንደማያከብሩ ፡ ተገልጿል ። በጥብቅና ፡ ሙያ ፡ ከተሰማሩ ፡ በኋላ ፡ የሕግን ፡ ምግባር ፡ የሚተላለፉና ፡ ለዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ጠባያቸው ፡ ተስማሚ ፡ ያልሆኑት ፡ ጠበቆች ፡ ከጥብቅናቸው ፡ ሊወገዱ ፡ ይችላሉ ። ይህም፡ ሥልጣን ፡ በ፲፱፻፴፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በወጣው ፡ የዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ አዋጅ ፡ በ፳ኛው ፡ አንቀጽ ፡ መሠረት ፡ ለፍርድ ፡ ሚኒስትሩ ፡ የተሰጠ ፡ ስለሆነ ፡ ደንቡ ፡ በሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፷፯/፲፱፻፵፮ ፡ ወጥቷል ። በዚህም ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ እንደተመለከተው ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴሩ ፡ ወይም ፡ ሚኒስትሩ ፡ ሥልጣን ፡ የሰጠው ፡ ሰው ፡ አምስት ፡ አባሎች ፡ ያሉበት ፡ የጠበቆች ፡ ያስተዳደር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ (ዲስፕሊን) ፡ ኮሚቴ ፡ ያቆማል ፡ ስለሚል ፡ ሚኒስትሩ ፡ አምስት ፡ ሰዎች ፡ በየጊዜው ፡ እየመረጡ ፡ በጠበቆች ፡ ላይ ፡ የሚቀርበውን ፡ አቤቱታ ፡ እየመረመሩ ፡ ሐሳባቸውን ፡ ያቀርባሉ ። የፍርድ ፡ ሚኒስትሩ ፡ የፈለጉትን ፡ ሰው ፡ ለመምረጥ ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው። ይሁንና ፡ በልማድ ፡ የሚሰሙት ፡ ከፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሁለት ፡ አባሎች ፡ ሲሆኑ ፡ እነርሱም ፡ ጠቅላይ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉና ፡ የጠበቆች ፡ ዲሬክሲዮን ፡ ዲሬክተር ፡ ናቸው ። አንዳንዴም ፡ ከዳኞች ፡ ወይም ፡ ከፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ባልደረባ ፡ አንድ ፡ አባል ፡ ሊመረጥ ፡ ይቻላል ። የቀሩት ፡ ሁለቱ ፡ ግን ፡ ከጠበቆች ፡ መካከል ፡ ችሎታና ፡ እምነት ፡ ያላቸው ፡ በአባልነት ፡ ይሾማሉ ። ይህ ፡ ለሸዋ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፡ በኤርትራ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ እንዲሁ ፡ ተመሳሳይ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ የጠበቆች ፡ ያስተዳደር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ (ዲስፕሊን) ፡ ኮሚቴ ፡ አለ ። እንዲሁም ፡ በቀሩት ፡ ጠቅላይ ፡

ግዛቶች ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሰብሳቢ ፡ ዳኛ ፡ የኮሚቴው ፡ ሰብሳቢ ፤ ሲሆን ፡ የዚሁ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኛ ፤ የአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ም/ፕሬዚዳንት ፤ ሬጅስትራሩ ፤ እና ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡ ሹም ፡ በአባልነት ፡ በጠበቆች ፡ ላይ ፡ የሚቀርበውን ፡ ቅሬታ ፡ ይምረምራሉ ፤ አዲስ ፡ አበባ ፡ የሚመጡት ፡ በይግባኝ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

የዚህ ፡ የጠበቆች ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ (ዲሲፕሊን) ፡ ኮሚቴ ፡ ሥራ ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁ. ፩፻፷፯/፲፱፻፵፬ ፡ አንቀጽ ፡ ፳ (፪) ሲገልጽ ፤

«የኮሚቴው ፡ ተግባር ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ በጥብቅና ፡ መዝገብ ፡ የገባ ፡ ሰው ፡ በመዝገብ ፡ ገብቶ ፡ ሳለ ፡ ወይም ፡ በመዝገብ ፡ ለመግባት ፡ ማመልከቻ ፡ አቅርቦ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ የማይገባ ፡ ሥራ ፡ ሠርቷል ፡ ሲባል ፤ የሠራው ፡ ሥራ ፡ ሰውየውን ፡ ለዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሔድ ፡ ይህ ፡ ጠባዩ ፡ የማይስማማ ፡ ያደረገው ፡ እንደሆነ ፡ ማናቸውንም ፡ ሥራውንና ፡ ጠባዩን ፡ ለመመርመር ፡ በምርመራ ፡ ያገኘውን ፡ ነገር ፡ በጽሑፍ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ሥልጣን ፡ ለሰጠው ፡ ሰው ፡ በፍጥነት ፡ ማቅረብ ፡ ነው» ።

የኮሚቴው ፡ ሥራ ፡ ለጥብቅና ፡ ሥራ ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ ድርጊት ፡ የፈጸመውን ፡ ጠበቃ ፡ እንደ ፡ አስፈላጊነቱ ፡ ከጥብቅና ፡ በመሰረዝም ፡ ሆነ ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ በማሳገድ ፡ እርምጃ ፡ እንዲወሰድበት ፡ ለሚኒስትሩ ፡ ሐሳብ ፡ መስጠት ፡ ነው ። ይሁንና ፡ ይግባኝ ፡ ካልተባለ ፡ በስተቀር ፡ የኮሚቴው ፡ ውሳኔ ፡ መጽደቅ ፡ እንደማያስፈልገውና ፡ የጸና ፡ እንደሆነ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ለኮሚቴው ፡ በደብዳቤ ፡ ሥልጣን ፡ ሰጥተዋል ።

ይህ ፡ ኮሚቴ ፡ በጠበቆች ፡ ላይ ፡ የሚቀርበውን ፡ ቅሬታ ፡ ለመመርመር ፡ በሳምንት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይሰበሰባል ። አቤቱታ ፡ የቀረበበት ፡ ጠበቃ ፡ ለክሱ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ መልስ ፡ ይዞ ፡ መቅረብ ፡ እንዲችል ፡ መጥሪያ ፡ እንዲደርሰው ፡ ይደረጋል ። ራሱ ፡ ቀርቦ ፡ ወይም ፡ ጠበቃ ፡ ይዞ ፡ ሊከላከል ፡ ይችላል ። ራሳቸው ፡ ጠበቃ ፡ ሆነው ፡ ጠበቃ ፡ ይዞ ፡ ለመቅረብ ፡ ግን ፡ ብዙዎች ፡ እንደ ፡ ዕፍረት ፡ ስለሚቆጥሩት ፡ ብቻቸውን ፡ ይቀርባሉ ። ይኸውም ፡ ጠበቃ ፡ ይዞ ፡ የመጣ ፡ እንደሆነ ፡ ጠበቃ ፡ ሆኖ ፡ እንዴት ፡ መከራከር ፡ ያቅተዋል ፡ ለራሱ ፡ ያልሆነ ፡ እንዴት ፡ ለሰው ፡ ጉዳይ ፡ መቆም ፡ ይችላል ፡ የሚል ፡ አስተያየት ፡ ይጥሉብኛል ፡ ሲል ፡ የጠበቃ ፡ ዕርዳታ ፡ አይፈልግም ። በ፲፱፻፶፱ ዓ ፡ ም ፡ ከወለጋ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የተከሰሰ ፡ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ የሚረዳው ፡ ጠበቃ ፡ ይዞ ፡ መቅረቡ ፡ ይታወሳል ፤ እንዲሁም ፡ ከላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ አንቀጽ ፡ ፳/፩/ መሠረት ፡ የተከሰሰው ፡ ጠበቃ ፡ ይጠቅመኛል ፡ የሚለውን ፡ መከላከያ ፡ ለኮሚቴው ፡ ለማሰማትና ፡ ማስረጃ ፡ ለማቅረብ ፡ መብት ፡ አለው ። በኮሚቴው ፡ ውሳኔ ፡ ቅሬታ ፡ የተሰማው ፡ ጠበቃ ፡ ለሚኒስትሩ ፡ በስምንት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ይግባኝ ፡ ለማለት ፡ መብት ፡ አለው ።

በጠበቆች ፡ ላይ ፡ የሚቀርበው ፡ አቤቱታ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በግል ፡ አቤት ፡ ባዮች ፡ ሲሆን ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ግን ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ በኩልም ፡ በዲሲፕሊን ፡ እርምጃ ፡ እንዲወሰድባቸው ፡ ለፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ በቀጥታ ፡ የሚጻፍ ፡ ጭምር ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ በተጠቀሰው ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁ.፱ ፡ መሠረት ፡ «ማናቸውም ፡ ክርክር ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜ ፡ ጠበቃው ፡ በጠባዩ ፡ ፍርድ ፡ ቤትን ፡ ያቃለለ ፡ ወይም ፡ ለዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ ያልተስማማ ፡ መሆኑን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተመለከተ ፡ እንደሆነ ፡ ወዲያውኑ ፡ ከጥብቅና ፡ ሥራው ፡ ከአንድ ፡ ወር ፡ ለማይበልጥ ፡ ጊዜ ፡ እንዲታገድ ፡ ወይም ፡ ከሁለት ፡ መቶ ፡ ሃምሳ ፡ ብር ፡ በማይበልጥ ፡ መቀጫ ፡ እንዲቀጣ ፡ ለማዘዝ ፡ ይቻላል» ፡ ስለሚል ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሥልጣን ፡ ጠባብ ፡

ነው ። ስለዚህ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከጥብቅና ፡ የማገድ ፡ ውሳኔው ፡ ለአጭር ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡
ስለሆነ ፡ ጥፋተኛውን ፡ ጠበቃ ፡ በገንዘብ ፡ ብቻ ፡ ይቀጣና ፡ ከጥብቅናው ፡ ስለማገዱ ፡
ጉዳይ ፡ እርምጃ ፡ እንዲወሰድበት ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ይጽፋል ። አንዳንድ ፡
ጊዜም ፡ ምንም ፡ ሳይቀጣ ፡ በቀጥታ ፡ ለፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ የሚጽፍበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ።
ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ በ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ ሀብት ፡ እያለው ፡ በድሃ ፡ ደንብ ፡
ዳኝነት ፡ ሳይከፍልበት ፡ በነፃ ፡ ፋይል ፡ እንዲከፍትለት ፡ የሐሰት ፡ የመሐላ ፡ ቃል ፡
በመስጠቱ ፡ ባላጋራዎቹ ፡ ተቃውመው ፡ ንብረት ፡ እንዳለው ፡ አስመሰከሩበት ።
ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ የዳኝነት ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፍል ፡ ከወሰነ ፡ በኋላ ፡ ጠበቃው ፡ ለዳኝ
ነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ የማይስማማ ፡ መሆኑን ፡ በመግለጽ ፡ የዲሲፕሊን ፡ እርምጃ ፡
እንዲወሰድበት ፡ ለፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ደብዳቤ ፡ ጻፈ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የጠበቆች ፡
ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ (ዲስፕሊን) ፡ ኮሚቴ ፡ ጉዳዩን ፡ ከመረመረ ፡ በኋላ ፡ ጠበቃውን ፡ ከጥ
ብቅና ፡ ሥራው ፡ አግዶ ፡ አድራጎቱ ፡ ወንጀል ፡ ስለነበረ ፡ ጠቅላይ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕግ ፡
የወንጀል ፡ ክስ ፡ እንዲመሠረትበት ፡ አድርጎ ፡ አሁን ፡ ጉዳዩ ፡ ወንጀል ፡ ችሎት ፡
ውስጥ ፡ በቀጠሮ ፡ ላይ ፡ ይገኛል ።

ከላይ ፡ የተገለጸው ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ አማካይነት ፡ ጠበቆች ፡ ሙያቸውን ፡ የሚ
ጻረር ፡ ድርጊት ፡ ሲፈጽሙ ፡ የሚታገዱበት ፡ ሁኔታ ፡ ነው ።

ነገር ፡ ግን ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ጠበቆች ፡ ላይ ፡ እርምጃ ፡ የሚወሰደው ፡ የግል ፡
ተበዳይ ፡ ወይም ፡ አቤት ፡ ባይ ፡ ለጠበቆች ፡ ክፍል ፡ የደረሰበትን ፡ ጉዳይ ፡ ሲያመለ
ክት ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ለምሳሌ ፡ አቤት ፡ ባዩ ፡ ለጠበቆች ፡ አስተዳደር ፡ ክፍል ፡
እገሌ ፡ የተባለው ፡ ጠበቃ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ የኔ ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ ሆኖ ፡ ወይም ፡ ጉዳዩን ፡
በሽምግልና ፡ አይቶት ፡ ሳለ ፡ አሁን ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ለሌላው ፡ ባላጋራዬ ፡ ጠበቃ ፡
ሆኖ ፡ ይሞግተኛል ፡ ሲል ፡ በጽሑፍ ፡ ያመለክታል ። ከዚህ ፡ ሌላ ፡ የአቤቱታው ፡
ምክንያት ፡ በጣም ፡ የተለያየ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የሚቀርቡት ፡
አቤቱታዎች ፡ ግን ፡ አቶ ፡ እገሌ ፡ የተባለው ፡ ጠበቃ ፡ ገንዘብ ፡ በልቶ ፡ አልተከራከረ
ልንም ፤ መዝገብ ፡ አዘጋብኝ ፤ በየቀጠሮው ፡ አይቀርብልኝም ፤ የአካፈልኩትን ፡ ሚስ
ጢር ፡ ወይም ፡ ማስረጃ ፡ ለባላጋራዬ ፡ ሰጠብኝ ፤ ወይም ፡ ለዳኝነት ፡ የሰጠሁትን ፡ ገን
ዘብ ፡ ፋይሉን ፡ ሳይከፍትልኝ ፡ ለራሱ ፡ ጥቅም ፡ አዋለው ፡ የሚልና ፡ ይህን ፡ የመሳሰ
ሉት ፡ ናቸው ። ኮሚቴው ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ መምሪያ ፡ ስለሌለው ፡ ማለትም ፡ ጠበቆች ፡ ከጥ
ብቅናቸው ፡ የሚወገዱባቸው ፡ ሁኔታዎች ፡ (ምክንያቶች) ፡ ተዘርዝረው ፡ ስለአልወጡና ፡
የሕግ ፡ ሥነ ፡ ምግባር ፡ ደንብ ፡ ስለሌለ ፡ እንዲሁም ፡ ጠበቆች ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ የጥብ
ቅናን ፡ ሙያ ፡ ደንብ ፡ እንደሚተላለፉ ፡ ማወቅ ፡ ስለማይቻል ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡
ያዳግተዋል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ጠበቃው ፡ ግልጽ ፡ የሆኑ ፡ ጥፋቶች ፡ መፈጸሙን ፡ እያ
ወቁ ፡ ማለትም ፡ ለምሳሌ ፤ አቤት ፡ ባዩ ፡ ጠበቃዬ ፡ በቀጠሮ ፡ ባለመቅረቡ ፡ መዝ
ገብ ፡ አዘጋብኝ ፡ የሚል ፡ አቤቱታ ፡ እያቀረቡ ፡ በኮሚቴው ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡
አባል ፡ ጠበቆች ፡ አቤቱታውን ፡ በመናቅ ፡ የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ አድራጎት ፡ የተለመደና ፡
ማንም ፡ ጠበቃ ፡ በየቀኑ ፡ የሚፈጽመው ፡ ድርጊት ፡ ነው ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ጠበ
ቃው ፡ መታገድ ፡ ወይም ፡ የቅጣት ፡ እርምጃ ፡ እንዲሠነዘርበት ፡ አያስፈልግም ፡
በማለት ፡ ለክሱ ፡ ብዙ ፡ ዋጋ ፡ አይሰጡትም ።

ስለዚህ ፡ ጠበቃው ፡ የሚቀጣበት ፡ ሁኔታ ፡ አነስተኛ ፡ ስለሆነ ፡ ሞያውን ፡ ንጹሀ ፡
ለማድረግ ፡ አይችልም ። የቅጣቱ ፡ ሁኔታ ፡ ደግሞ ፡ በጣም ፡ ያነሠ ፡ የሚሆነው ፡
ጥፋቱ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ በግልጽ ፡ ካልተፈጸመ ፡ ወይም ፡ በጥፋተኛው ፡ ጠበቃ ፡ ላይ ፡
ተበዳዩ ፡ ባለጉዳይ ፡ ተከታትሎ ፡ አቤቱታ ፡ ካላቀረበ ፡ ኮሚቴው ፡ ጉዳዩን ፡ ተከታትሎ
ስለማይደርስበት ፡ አጥፊው ፡ ጠበቃ ፡ ሳይቀጣ ፡ ይታለፋል ። አንድ ፡ ጠበቃ ፡ ግዴ

ታው ፣ ለመንግሥት ፤ ለፍርድ ፡ ቤት ፤ ለደንበኛው ፤ ለሌላው ፡ ጠበቃና ፡ ለሞያው ፡ መሆኑ ፡ ተገልጿል ። ከዚህ ፡ ውስጥ ፡ ግዴታውን ፡ ተላልፏል ፡ ብለው ፡ አቤቱታ ፡ የሚያቀርቡት ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ባለጉዳዮቹ ፡ ብቻ ፡ ስለሆኑ ፡ ለመንግሥት ፡ ወይም፡ ለሌላው ፡ ጠበቃ ፡ ወይም ፡ ለሞያው ፡ ያለበትን ፡ ግዴታ ፡ ጥሷል ፡ በማለት ፡ ተከታትሎ ፡ አቤቱታ ፡ የሚያቀርብ ፡ የለም ። ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ በ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ለኮሚቴው ፡ (አዲስ ፡ አበባ) ፡ የቀረቡት ፡ ጉዳዮች ፡ አሥር ፡ ብቻ ፡ ነበሩ ። ቀጥሎም ፡ በ፲፱፻፶፱፡ አሥራ ፡ ሰባት ፡ ጉዳዮች ፡ ቀርበዋል ፤ ከእነዚሁም ፡ አሥሩ ፡ እስከ ፡ አውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ድረስ ፡ ብቻ ፡ ለመከራከር ፡ ሥልጣን ፡ ባላቸው ፡ ጠበቆች ፡ ላይ ፡ የቀረበ ፡ ነበር ። በ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እስከ ፡ መጋቢት ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ ለኮሚቴው ፡ አሥራ ፡ አንድ ፡ ጉዳዮች ፡ ቀርበው ፡ ሁለቱ ፡ ውሳኔ ፡ አግኝተዋል ። በአገሪቷ ፡ ፪ሺ፫፻፫ ፡ ያህል ፡ ጠበቆች ፡ መኖራቸው ፡ ሲታወቅ ፡ አቤቱታ ፡ የሚቀርብባቸው ፡ ግን ፡ በጣም ፡ ጥቂት መሆናቸውን ፡ ቁጥሩ ፡ ያስረዳል ። አቤቱታ ፡ የቀረበባቸው ፡ ጠበቆች ፡ ቁጥር ፡ ሊያንስ ፡ የቻለው ፡ ጠበቆች ፡ የሕግን ፡ ሥነ ፡ ምግባር ፡ አክባሪዎች ፡ ሆነው ፡ ሳይሆን ፡ በቅርብ ፡ የሚከታተላቸው ፡ ባለመኖሩ ፡ ነው ። አቤቱታ ፡ በሚቀርብባቸውም ፤ ላይ ፡ እጅግ ፡ ከባድ ፡ ቅጣት ፡ አይወሰንባቸውም ፤ ለምሳሌ ፡ በ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ. ም. አንድ ፡ ጠበቃ ፡ የሐሰት ፡ ቃለ ፡ መሐላ ፡ በመስጠቱ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ብቻ ፡ ከጥብቅና ፡ እንዲወገድ ፡ ተወስኖበታል ። ይሁንና ፡ የቅጣቱ ፡ ዓይነት ፡ በሶስት ፡ ሊከፈል ፡ ይችላል ። ይኸውም ፡ በወቀሳ ፡ ማለፍ ፤ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ማገድ ፤ ከጥብቅና ፡ ሥራ ፡ ፈጽሞ ፡ ማገድ ፡ ናቸው ።

የቅጣቱ ፡ ማነስና ፡ መብዛት ፡ ብዙ ፡ አከራካሪ ፡ መሆን ፡ አይገባውም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የሚያሳዝነው ፡ አጥፊው ፡ ጠበቃ ፡ ጥፋቱ ፡ ሳይገለጥበት ፡ ሞያውን ፡ እያጐደፈ ፡ መኖሩ ፡ ነው ። አንድ ፡ ጠበቃ ፡ ሌላው ፡ ጠበቃ ፡ የሕግን ፡ ሥነ ፡ ምግባር ፡ የሚጻረር ፡ ድርጊት ፡ ሲፈጽም ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ማሳለፍ ፡ የለበትም ፤ ከግዴታዎቹ ፡ አንዱ ፡ ይህንን ፡ ጥፋት ፡ ለተገቢው ፡ ድርጅት ፡ ማመልከት ፡ ነው ። ከላይ ፡ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ የተጠቀሰው ፡ ማለት ፡ የሐሰት ፡ ቃለ ፡ መሐላ ፡ በመስጠት ፡ የተከሰሰው ፡ ጠበቃ ፡ ጉዳዩ ፡ ለኮሚቴው ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ ጉዳዩን ፡ እኛ ፡ መርምረንና ፡ አጣርተን ፡ እስክንልክ ፡ ድረስ ፡ ኮሚቴው ፡ ጉዳዩን ፡ እንዳያይ ፡ ሲሉ ፡ ለፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፈው ፡ ነበር ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ጥያቄያቸው ፡ ተቀባይነት ፡ አላገኘም ። ይኸውም ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ ሙከራ ፡ ጠበቃው ፡ የማህበሩ ፡ አባል ፡ ስለነበረ ፡ እርሱን ፡ ለመርዳት ፡ እንጂ ፡ የኮሚቴውን ፡ የሥራ ፡ አመራር ፡ ለማቃናት ፡ የታሰበ ፡ ባለመሆኑ ፡ ነበር ። የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ ምግባር ፡ የዚህን ፡ ዓይነት ፡ መልክ ፡ የያዘ ፡ ከሆነ ፡ ለሙያ ፡ ተስማሚ ፡ ያልሆኑት ፡ ጠበቆች ፡ የሚወገዱበት ፡ ዕድል ፡ በጣም ፡ የመነመነ ፡ ይሆናል ። የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ ግዴታው ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ በሚከተለው ፡ ክፍል ፡ ስለሚተነተን ፡ በዚህ ፡ አርዕስት ፡ ውስጥ ፡ ማውሳት ፡ አያሻም ።

## የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ አቋምና ፡ ግዴታው ።

ጠበቃው ፡ ለሕብረተ ፡ ሰቡና ፡ ለመንግሥቱ ፡ ያለበት ፡ ግዴታ ፡ ተብሎ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ውስጥ ፡ ስለጠበቃው ፡ ተግባሮች ፡ ሲተነተን ፤ እያንዳንዱ ፡ ጠበቃ ፡ ተግባሩን ፡ በትክክል ፡ ለማከናወን ፡ እንዲችል ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ ቢቋቋም ፡ እንዴት ፡ እንደሚረዳው ፡ መግለጻችን ፡ የሚታወስ ፡ ነው ።

አሁን ፡ በዚህ ፡ አርዕስት ፡ ልናወሳ ፡ የምንፈልገው ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ በሌላው ፡ አገር ፡ በተለይም ፡ በአሜሪካን ፡ ውስጥ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ሥልጣንና ፡ ተግባር ፡ እንዳለው ፡ ሲሆን ፤ ይህ ፡ የምንዘረዝረውም ፡ ሥልጣንና ፡ ተግባር ፡ በመጠኑ ፡ በኢትዮ

ጵያም ፡ ውስጥ ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ ሥልጣንና ፡ ተግባር ፡ ሊሆን ፡ ይገባዋል ፡ በማለት ፡ ነው ።

የውጪን ፡ አገር ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ ሥልጣንና ፡ ተግባር ፡ ከመዘርዘራችን ፡ በፊት ፡ ግን ፡ በኢትዮጵያም ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ አቋም ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ባጭሩ ፡ ልንገልጽ ፡ እንፈልጋለን ።

አሁን ፡ በቅርቡ ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ እየተባለ ፡ የሚጠራ ፡ ድርጅት ፡ መቋቋሙ ታውቋል ። ማኅበሩ ፡ የመተዳደሪያ ፡ የውስጥ ፡ ደንብ ፡ አለው ። ድርጅቱ ፡ በአባልነት፡ ጠበቆች ፡ ብቻ ፡ የሚገኙበት ፡ በመሆኑ ፡ እንጂ ፡ በልማድ ፡ በየቀበሌው ፡ ከሚሠራበት ፡ የመረዳጃ ፡ ማኅበር ፡ የማይለይ ፡ መሆኑን ፡ ለማወቅ ፡ ችለናል ። ይኸውም ፡ ማለት ፡ የማኅበሩ ፡ ዓላማ ፡ የሞተውን ፡ መቅበር ፤ የታመመውን ፡ ማስታመም ፡ የተቸገረውን ፡ መርዳት ፡ እንጂ ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ ተብሎ ፡ በሌሎች ፡ አገር ፡ እንደሚታወቀው ፡ የጥብቅና ፡ ሞያን ፡ የሚመለከት ፡ ድርጅት ፡ አይደለም ።

ማኅበሩ ፡ አሁን ፡ ካለበት ፡ የመረዳጃነት ፡ አቋም ፡ ተለውጦ ፡ የጥብቅና ፡ ሞያን ፡ የሚመለከት ፡ አቋም ፡ እንዲኖረው ፡ ለምን ፡ አልተደረገም ፡ ለሚለው ፡ ጥያቄ ፡ የሚገኘው ፡ መልስ ፡ እንኳንስ ፡ እንዲህ ፡ ዓይነቱን ፡ ትልቅ ፡ ነገር ፡ ተስማምቶ ፡ ለመሥራትና ፡ ለግል ፡ ጥቅም ፡ እንኳን ፡ በሽርክና ፡ ማኅበር ፡ ለመሥራት ፡ ጠበቆች ፡ የማይስማሙ ፡ መሆናቸውን ፡ ነው ። አሁንም ፡ በተያዘው ፡ የመረዳጃ ፡ አቋም ፡ እንኳ ፡ አንዱ ፡ ሌላውን ፡ በመንቀፍና ፡ በመውቀስ ፡ እንዲሁም ፡ በመናቅ ፡ ለስብሰባው ፡ ተካፋይ ፡ የሚሆኑት ፡ ጠበቆች ፡ ቁጥር ፡ በጣም ፡ አነስተኛ ፡ መሆኑ ፡ ታውቋል ።

ባጭሩ ፡ በሌሎች ፡ አገሮች ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ እየተባለ ፡ የሚጠራው ፡ ድርጅት ፡ አሁን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የለም ። የማኅበሩ ፡ መኖር ፡ አስፈላጊነት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሲሆን ፡ አሁን ፡ ባለው ፡ አያያዝ ፡ ግን ፡ ለመቋቋም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ እንደሚያጋጥም ፡ አይጠረጠርም ። ቢሆንም ፡ ችግር ፡ ያጋጥመናል ፡ ብሎ ፡ መሸሽ ፡ ሳይሆን ፡ ለሚያጋጥመው ፡ ችግር ፡ መድኀን ፡ በመፈለግ ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ እንዲቋቋም ፡ ማድረግ ፡ የያንዳንዱ ፡ የሕግ ፡ ሰው ፡ (ጠበቃ) ፡ ተግባር ፡ ነው ።

በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ አሁን ፡ ያለውን ፡ አቋም ፡ ባጭሩ ፡ ካወሳን ፡ ዘንድ ፤ አሁን ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ እየተባለ ፡ የሚጠራው ፡ ድርጅት ፡ አቋም ፡ እንዴት ፡ እንደሆነና ፡ ምን ፡ ግዳጀችም ፡ እንዳሉበት ፡ እንመልከት ። እያንዳንዱንም ፡ ግዳጅ ፡ ከተመለከትን ፡ በኋላ ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ ሲታይ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ይህ ፡ ዓይነቱ ፡ ግዳጅ ፡ ሊፈጸም ፡ መቻል ፡ አለመቻሉንም ፡ ሃሳብ ፡ ልንሰጥበት ፡ እንሞክራለን ።

ሲ.ኤል. አናንድ ፡ የተባሉት ፡ ጸሐፊ ፡ «ጄኔራል ፡ ፕሪንስፕልስ ፡ ኦፍ ፡ ሊጋል ፡ ኤቲክስ» ፡ በተባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ የጠበቆችን ፡ ማኅበር ፡ አቋምና ፡ ግዴታዎች፡ እንደሚከተለው ፡ ዘርዝረውታል ።

የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ የመጀመሪያው ፡ እርምጃ ፡ የራሱን ፡ አቋም ፡ በትክክል ፡ ማደርጀት ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ለማድረግ ፡ የአባሎቹን ፡ ቁጥር ፡ ማበርከትና ፡ ለመቋቋሚያና ፡ ለእንዳንድ ፡ ዕቅዶች ፡ ማካሄጃ ፡ የሚረዳውን ፡ በቂ ፡ ገንዘብ ፡ ከአባሎቹ ፡ ማግኘት ፡ ይኖርበታል ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ የአባሎቹ ፡ መምረጫ ፡ መለኪያ ፡ የገንዘብ ፡ መክፈል ፡ ችሎታ ፡ መሆን ፡ የለበትም ። የአባልነት ፡ መለኪያው ፤ ከጊዜው ፡ ጋር ፡ በመራመድ ፡ የሚወጡትን ፡ ሕጐች ፡ ተረድቶ ፡ አገልግሎቱን ፡ ለማበርከት ፡ የሚያስችል ፡ ዕውቀት ፡ እያንዳንዱ ፡

አባል ፡ እንዲኖረው ፡ ሲሆን ፡ ለዚህም ፡ ችሎታ ፡ የሚያበቃው ፡ የቀለም ፡ ዕውቀት ፡ የሁለት ፡ ዓመት ፡ ጠቅላላ ፡ የኮሌጅ ፡ ትምህርት ፡ ጥናትና ፡ በተጨማሪም ፡ የሦስት ፤ ዓመት ፡ ልዩ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ጥናት ፡ ነው ።

ከዚህም ፡ ሌላ ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ በራሱ ፡ ሕግ ፡ እራሱን ፡ ችሎ ፡ የሚተዳደር ፡ እንዲሆንና ፡ የአባሎቹን ፡ እርምጃ ፡ የትምህርት ፡ ችሎታ ፤ የጥብቅና ፡ ፈቃድ ፡ አሰጣጥና ፡ አከላከል ፡ የሚወሰንበት ፡ ሥልጣን ፡ በሕግ ፡ አውጭዎች ፡ ታውጆ፡ እንዲሰጠው ፡ ያስፈልጋል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ የፈቃድ ፡ አሰጣጥና ፡ አከላከል ፡ ሥልጣኑ ፡ አስፈላጊ ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ቁጥጥር ፡ ስር ፡ ሊሆን ፡ ይገባዋል ።

ይህ ፡ ዓይነቱ ፡ እራሱን ፡ የቻለ ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ መቋቋም ፡ ለሕግ ፡ ሞያ ፡ አንድነትን ፡ ኩራትንና ፡ የኃላፊነትን ፡ ግዴታ ፡ ይፈጥራል ።

እዚህ ፡ ነጥብ ፡ ላይ ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ ሁኔታ ፡ ልንገልጽ ፡ የምንፈልገው ፡ ስለ አባልነት ፡ መለኪያውና ፡ የጥብቅና ፡ ፈቃድ ፡ መስጠቱ ፡ ሥልጣን ፡ ነው ። ከላይ ፡ በተገለጸው ፡ ሀሳብ ፡ ላይ ፡ የቀረበው ፡ የአባልነት ፡ መለኪያ ፡ ለጊዜው ፡ ከኢትዮጵያ፡ ጠበቆች ፡ ችሎታ ፡ ጋር ፡ የማይመጣጠን ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መለኪያ ፡ ነው ። ይህን ፡ የተጠቀሰውን ፡ የትምህርት ፡ መለኪያ ፡ የሚያገኙ ፡ በጣም ፡ ጥቂቶቹ ፡ በመሆናቸው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሊቋቋም ፡ የሚገባው ፡ ማኅበር ፡ መለኪያውን ፡ በመጠኑ ፡ ዝቅ ፡ ማድረግ ፡ ይኖርበታል ። በጥብቅና ፡ አሰጣጥም ፡ በኩል ፡ ለጊዜው ፡ ፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ያለውን ፡ ሥልጣን ፡ ለማስለቀቅ ፡ ችግርን ፡ ሳይፈጥር ፡ አይቀርም ። ችግሩ ፡ ሥልጣን ፡ የማስለቀቁ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ሥልጣኑን ፡ የሚረከቡ ፡ ሰዎች ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ማግኘቱ ፡ ነው ።

ከላይ ፡ በተጠቀሱት ፡ ጸሐፊ ፡ አስተያየት ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ ሁለተኛው ፡ እርምጃ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚቀመጡት ፡ ዳኞች ፡ እንዲሻሻሉ ፡ ማድረግ ፡ ነው ።

ሰዎች ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ የሚያገኙበት ፡ መንገድ ፡ በየሀገሩ ፡ የተለያየ ፡ ነው ። በአንዳንድ ፡ አገሮች ፡ ዳኞች ፡ በሕዝብ ፡ ይመረጣሉ ፤ በአንዳንዶች ፡ አገሮች ፡ በልዩ ፡ ኮሚቴ ፡ ይመረጣሉ ፤ እንዲሁም ፡ በሌሎች ፡ አገሮች ፡ በባለሥልጣኖች ፡ ይሾማሉ ። ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ በዳኝነት ፡ ሊቀመጡ ፡ የሚገባቸውን ፡ ሰዎች ፡ በበለጠ፡ ሊያውቁ ፡ የሚችሉት ፡ እራሳቸው ፡ ጠበቆች ፡ ስለሆኑ ፤ በዳኞች ፡ ምርጫ ፡ ወይም ፡ ሹመት ፡ ላይ ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ ተካፋይ ፡ እንዲሆን ፡ ቢደረግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥቅም፡ የሚሰጥ ፡ መሆኑ ፡ ተረጋግጧል ። ስለዚህ ፡ ሁለተኛው ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ ተግባር፡ አዋቂ ፡ ዳኞችን ፡ መርጦ ፡ ማዘጋጀት ፡ ሊሆን ፡ ይገባዋል ።

የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ ሶስተኛው ፡ ተግባር ፡ ግልጽ ፡ ያልሆኑ ፡ ሕጎች ፡ በግልጽ ፡ በሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡ እንዲታወቁ ፡ ማድረግ ፡ ነው ። በዚህም ፡ ረገድ ፡ በእያንዳንዱ ፡ የሕግ ፡ አንቀጽና ፡ ቃላት ፡ ላይ ፡ ሰፋ ፡ ያሉ ፡ ማብራሪያዎችን ፤ መግለጫዎችን ፡ መስጠት ፡ ተገቢያቸው ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ጉዳዩ ፡ እስከአሁን ፡ ድረስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ምን ፡ እርምጃ ፡ እንደተወሰደና ፡ የዚህ ፡ ዓይነቱም ፡ እርምጃ ፡ እንዲስፋፋ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ቀደም ፡ ብለን ፡ የጠበቃውን ፡ ግዴታ ፡ በገለጽንበት ፡ ጊዜ ፡ ያቀረብነውን ፡ ሃሳብ ፡ መመልከት ፡ በቂ ፡ ነው ።

አራተኛው ፡ ተግባር ፡ በሕግ ፡ አውጭዎች ፡ የሚወጡት ፡ ሕጎች ፡ ሁሉ ፡ ያለአንዳች ፡ ልዩነት ፡ በሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡ በእኩልነት ፡ እንዲሠሩ ፡ ማድረግ ፡ ነው ።

አምስተኛው ፡ ተግባር ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ኮሚቴዎችን ፡ በማቋቋም ፡ ሕጐች ፡ እንዲ ሻሻሉና ፡ የፍትሐብሔር ፡ ሥራ ፡ ያለእንከን ፡ የሚገሠግሥበትን ፡ ዘዴዎች ፡ መፈለግ ነው ። ይህንንም ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጥናቶችና ፡ ምርምሮች ፡ በየፍርድ ፡ ቤቶችና ፡ በየአስፈላጊው ፡ ቦታ ፡ መደረግ ፡ አለባቸው ፡ ማለት ፡ ነው ።

ይህ ፡ አምስተኛው ፡ ተግባር ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ የጠበቃው ፡ ግዴታ ፡ ተብሎ ፡ በተጠቀሰው ፡ አርዕስት ፡ ውስጥ ፡ በሰፊው ፡ የታተተ ፡ በመሆኑ ፡ ተግባሩን ፡ በይበልጥ ለመረዳት ፡ ያኛውን ፡ ክፍል ፡ መመልከት ፡ ይጠቅማል ፡ ብለን ፡ እናምናለን ።

«ሴሌክትድ ፡ ሪዲንግስ ፡ ኦን ፡ ዘ ፡ ሊጋል ፡ ፕሮፌሽን» ፡ በተባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ከላይ ፡ የተዘረዘሩትንና ፡ ሌሎችንም ፡ የጠበቆችን ፡ ማኅበር ፡ ተግባሮች ፡ በማጠቃለል ፡ እንደሚከተለው ፡ ባጭሩ ፡ ተዘርዝሮ ፡ ይገኛል ።

የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ ተግባሮች ፦

፩/ አባሎቻቸው ፡ በኮሚቴ ፡ እንዲመረጡ ፡ ማድረግና ፡ የአባሎቻቸውም ፡ የሕግ ፡ ዕውቀት ፡ ችሎታ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ እንዲሆን ፡ ማድረግ ።

፪/ የጥብቅና ፡ ፈቃድ ፡ ያልተሰጣቸው ፡ ሰዎች ፡ በጥብቅና ፡ እንዳይቆሙ ፡ መከላከል ።

፫/ የሕግን ፡ ድጋፍ ፡ ለሚፈልጉ ፡ ድሆች ፡ ሰዎች ፡ በወንጀልም ፡ ሆነ ፡ በፍት ሐብሔር ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ጠበቃ ፡ እንዲኖራቸው ፡ ማድረግ ።

፬/ ክብራቸውና ፡ መብታቸው ፡ በጊዜው ፡ ፖለቲካ ፡ አቋም ፡ ሳይነካ ፡ ተጠብ ቀው ፡ ትክክለኛውን ፡ ፍትሕ ፡ የሚሰጡ ፡ ዳኞች ፡ እንዲኖሩ ፡ ማድረግ ።

፭/ ሕዝቡ ፡ የሕግን ፤ የጠበቆችንና ፡ የፍ/ቤቶችን ፡ ጥቅም ፡ እንዲያውቅ ፡ ማስ ተማር ።

፮/ እያንዳንዱ ፡ ጠበቃ ፡ ለሕዝቡ ፤ ለደንበኛው ፤ ለሌሎች ፡ ጠበቆችና ፡ ለፍርድ፡ ቤቶች ፡ ያለበትን ፡ ግዴታ ፡ እንዲያውቅና ፡ ግዴታውን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲያውለው ፡ ማድረግ ።

፯/ የሕግ ፡ አስተዳደር ፡ እንዲሻሻልና ፡ ያልተዛባ ፡ ፍትሕ ፡ ባጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ እንዲሰጥ ፡ ማድረግ ።

፰/ ጠበቆች ፡ የሚያደርጉትን ፡ ጥፋት ፡ በፍጥነት ፡ ተከታትሎ ፡ ተገቢውን ፡ ቅጣት ፡ መስጠትና ፡ በጠበቃውም ፡ ጥፋት ፡ የተጐዱት ፡ ሰዎች ፡ ካሣ ፡ የሚ ያገኙበትን ፡ ዘዴ ፡ መፈለግ ፡ ናቸው ።

ቀደም ፡ ብለን ፡ እንደገለጽነው ፡ እነኚህ ፡ የዘረዘርናቸው ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ ተግባሮች ፡ በአሜሪካን ፡ አገር ፡ የሚሠራባቸው ፡ ቢሆንም ፡ በእንግሊዝና ፡ በሕ ንድ ፡ አገሮችም ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የዋሉ ፡ ናቸው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ማስታወስ ፡ ያለብን ፡ የነኚህ ፡ አገሮች ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ ከእንደዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ሥልጣንና ፡ ግዳጅ ፡ ላይ ፡ የደረሱት ፡ ከተቋቋሙ ፡ ከብዙ ፡ ዓመታት ፡ በኋላ ፡ መሆኑን ፡ ነው ።

በዚህ ፡ አርዕስት ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ እንደገለጽነው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ እንኳንስ ፡ ለማኅበሩ ፡ ከላይ ፡ የተዘረዘሩትን ፡ ሥልጣንና ፡ ግዳጆች ፡ በሙሉ ፡ ለማስገኘት ፡ ይቅርና ፡ በመሠረቱም ፡ ማኅበሩን ፡ ማቋቋም ፡ አስቸጋሪ ፡ እን ደሚሆን ፡ የማይጠረጠር ፡ ነው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ አዝመራ ፡ ፍሬ ፡ ከመስጠቱ ፡ በፊት ፡ መሬቱ ፡ መታረስ ፤ መጐልጐል ፤ ዘሩ ፡ መዘራትና ፡ አትክልቱም ፡ መታረም ፡

እንዳለበት ፡ ሁሉ ፤ ማኅበሩም ፡ ከሚያስፈልገው ፡ ደረጃ ፡ ደርሶ ፡ የተፈለገውን ፡ ፍሬ ፡ ለማስገኘት ፡ እንዲችል ፡ መሠረቱ ፡ ካሁኑ ፡ መጣል ፡ አለበት ። ማኅበሩም ፡ ገና ፡ ከመ ጀመሩ ፡ የኃላፊነት ፡ ሸክም ፡ በዝቶበት ፡ በአረም ፡ እንደተዋጠ ፡ አትክልት ፡ ፍሬ ፡ ሳይሰጥ ፡ እንዳይቀር ፡ ሥልጣኑንና ፡ ግዳጁን ፡ በመጠኑ ፡ አድርጎ ፡ ሥራውን ፡ እንዲ ጀምር ፡ ቢደረግ ፡ ላሁኑም ፡ ሆነ ፡ ለወደፊቱ ፡ ትውልድ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥቅም ፡ ይሰ ጣል ።

ከላይ ፡ ከተዘረዘሩት ፡ ተግባሮች ፡ ውስጥ ፡ ለሚቋቋመው ፡ የጠበቆች ፡ ማኅበር ፡ ሸክም ፡ ይሆናል ፡ ብለን ፡ የምናስበው ፤ የጥብቅና ፡ ፈቃድ ፡ አሰጣጡ ፡ ሥልጣን ፤ የአ ባሎች ፡ የዕውቀት ፡ መለኪያ ፡ ሚዛንና ፡ ነፃ ፡ የጥብቅና ፡ አገልግሎትን ፡ ለድሆች ፡ ማበርከት ፡ ነው ። የጥብቅና ፡ ፈቃድ ፡ አሰጣጡ ፡ ሥልጣን ፡ ለማኅበሩ ፡ ይሰጠውና ፡ ሥልጣኑንም ፡ ሌሎች ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ማኅበሮች ፡ እንደሚሠሩበት ፡ ይሥራ ፡ ያልን ፡ እንደሆነ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ ያጋጥመናል ። ምክንያቱም ፡ በአገሪቷ ፡ ውስጥ ፡ አሁን፡ በጥብቅና ፡ ሥራ ፡ ተሠማርተው ፡ የሚገኙት ፡ አብዛኞቹ ሰዎች ፡ ጥብቅናን ፡ እንደገ ንዘብ ፡ ማግኛ ፡ ንግድ ፡ እንጂ ፡ እንደሞያ ፡ (ፕሮፌሽን) አድርገው ፡ ያልያዙት ፡ በመ ሆናቸውና ፡ ማኅበሩ ፡ ሥልጣኑን ፡ በትክክል ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ እርምጃ ፡ በሚወስድበት ፡ ጊዜ ፡ ብዙዎቹን ፡ ከጉዳት ፡ ላይ ፡ ያደርሳቸዋል ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ፈቃድ ፡ የመስጠቱና ፡ የመከልከሉ ፡ ሥልጣን ፡ ከባድ ፡ ኃላፊነት ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ በመሆኑ ፡ ይህን ፡ ኃላፊነት ፡ በጥሞና ፡ የሚከታተሉ ፡ ሰዎች ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ማግ ኘቱ ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ አሁን ፡ የፈቃድ ፡ መስጠቱን ፡ ሥልጣን ፡ የያዘው ፡ የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ በቅርቡ ፡ በወሰደው ፡ ጥብቅ ፡ የፈቃድ ፡ አሰጣጥ ፡ ቁጥጥር ፡ መሠረት ፡ ከቀጠለ ፡ ለጊዜው ፡ ይህ ፡ ሥልጣን ፡ በፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ እጅ ፡ ቢቆይ ፡ የተሻለ ፡ ነው ። ቢሆንም ፡ ማኅበሩ ፡ ከተቋቋመ ፡ ከፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ የጠበ ቆች ፡ አስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ጋር ፡ ፈተና ፡ የማዘጋጀትም ፡ ሆነ ፡ ሁኔታውን ፡ የመመር መር ፡ መብት ፡ እንዲኖረው ፡ ማድረግ ፡ ተገቢ ፡ ነው ።

በአባሎች ፡ የዕውቀት ፡ መለኪያ ፡ በኩል ፡ በሌላው ፡ አገር ፡ ከፍተኛ ፡ ችሎታ ፡ የሚፈለግ ፡ ቢሆንም ፡ በአገራችንም ፡ ተመሳሳይ ፡ መለኪያ ፡ ይደረግ ፡ ማለት ፡ አስቸ፡ ጋሪ ፡ ስለሆነ ፡ ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ ከሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ የሕግ ፡ ዲፕሎማ ፡ ያለው ፡ ወይም ፡ ተመጣጣኝ ፡ የሆነ ፡ ፈተና ፡ ያለፈ ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ። በተጨማሪም ፡ አባሎች ፡ ጥሩ ፡ ስምና ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው ፡ መሆናቸው ፡ በሚገባ ፡ መረጋገጥ ፡ አለበት ። ስለ ፡ ነፃ ፡ የጥብቅና ፡ አገልግሎት ፡ በመጀመሪያ ፡ ክፍል ፡ ጠበቃ ፡ ለሕዝቡ ፡ ያለበት ፡ አገልግሎት ፡ የተጠቀሰ ፡ ስለሆነ ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ መድገም ፡ አያሻም ።

## <u>መደምደሚያ ።</u>

አንድ ፡ የሕግ ፡ ጠበቃ ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ አባሎች ፡ ያለበት ፡ ግዴታና ፡ አሁን ፡ በአገራችን ፡ እንዴት ፡ እንደሚሠራበት ፡ የሚቻለውን ፡ ያህል ፡ ተገልጿል ፤ እንዲሁም በየክፍሉ ፡ መጨረሻ ፡ አስተያየት ፡ የተሰጠበት ፡ ስለሆነ ፡ እንደገና ፡ እዚህ ፡ ውስጥ ፡ ልንደግመው ፡ አያሻም ።

ይሁንና ፡ ጠበቃ ፡ ከፍተኛ ፡ ኃላፊነት ፡ ያለበት ፡ መሆኑን ፡ ወደዚህም ፡ ሥራ ፡ የሚሠማሩት ፡ ሰዎች ፡ ከፍተኛ ፡ ቁጥጥር ፡ እንዲደረግባቸውና ፡ እንዲሁም ፡ ወደ ፡ ጥብቅና ፡ ከተሠማሩ ፡ በኋላ ፡ የሕግን ፡ ሥነ ፡ ምግባር ፡ የሚተላለፉት ፡ ጠበቆች ፡ ከፍተኛ ፡ ቅጣት ፡ እንዲወሰድባቸው ፡ ያስፈልጋል ፡ ብለናል ። ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ኅዳር ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ

የሕግ ፡ ፋክልቲ ፡ ከኤክስቴንሽን ፡ ክፍል ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ተመርቀው ፡ ለወጡት ፡ ተማሪዎች ፡ ንግግር ፡ ሲያደርጉ ፡—

«በዳኝነት ፡ እውነትን ፡ መፈለግ ፡ ለሥራም ፡ ምርጥ ፡ ሰው ፡ መፈለግ ፡ ግዴታ ፡ ነው ። የሚመረጠውም ፡ ሕግን ፡ ከተማሩና ፡ ከራሳቸው ፡ ሥራቸውን ፡ ከሚያበልጡ ፡ መካከል ፡ ነው ። ጠበቃም ፡ በዕውነት ፡ ከሠራ ፡ ዳኛ ፡ ነው» ፡ ብለዋል ።

ስለዚህ ፡ የጥብቅና ፡ ሥራ ፡ በዚህ ፡ መልክ ፡ ቢያዝ ፡ ፍትሕ ፡ በደንብ ፡ ሊሠምር፡ ይችላል ። ሕዝቡ ፡ ትክክለኛ ፡ ፍርድ ፡ ስለሚፈልግ ፡ ሕግና ፡ ዳኞች ፡ ብቻ ፡ ቢኖሩ ፡ ጠበቃ ፡ ከሌለ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ችግር ፡ እንደሚኖር ፡ በሃሳባችን ፡ መገመት ፡ እንችላለን ። ለምሳሌ ፡ አንድ ፡ ንጹሕ ፡ ሰው ፡ ባልሠራው ፡ ወንጀል ፡ ታስሮ ፡ ሲጉላላ ፡ ንጽሕናውን ፡ ለማረጋገጥ ፡ ዞር ፡ ብሎ ፡ የሚመለከተው ፡ ወደ ፡ ጠበቃ ፡ ነው ። ጠበቃ ፡ ከሌለ ፡ ንጽሕናውን ፡ ለማረጋገጥ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ችግር ፡ እንደሚገጥመው ፡ መገመት ፡ እንችላለን ። ጥሩ ፡ ጠበቃ ፡ ካለው ፡ ግን ፡ ትክክለኛ ፡ ፍርድ ፡ አገኛለሁ ፡ ብሎ ፡ ስለሚያምን ፡ በነፃነቱ ፡ ኩራት ፡ ይሰማዋል ።

ስለዚህ ፡ የጥብቅናን ፡ ሞያ ፡ ንጹሕ ፡ ለማድረግ ፡ ስሙንና ፡ ክብሩን ፡ የማይጠብቁ ፡ ጠበቆች ፡ ከሥራቸው ፡ የሚወገዱበት ፡ ሁኔታዎች ፡ ተዘርዝረው ፡ በደንብ ፡ መውጣት ፡ አለባቸው ። ፍርድ ፡ ቤትም ፡ ሆነ ፡ የጠበቆች ፡ የዲሲፕሊን ፡ ኮሚቴ ፡ በሚገባ ፡ እየተቆጣጠረ ፡ የአንድ ፡ ጠበቃ ፡ አድራጎት ፡ የጥብቅናን ፡ ሞያ ፡ የተላለፈ ፡ ሲመስለው ፡ ጠበቃውን ፡ ከሞያው ፡ ማስወገድ ፡ አለበት ። የፍርድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ሠራተኞች ፡ ዳኞችና ፡ ጠበቆች ፡ በዲሲፕሊን ፡ የሚቀጡበትን ፡ ዝርዝር፡ ሁኔታ ፡ አዘጋጅቶ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ይጠና ፡ ተብሎ ፡ እስከዛሬ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ አልዋለም ። ይሁንና ፡ ደንቡ ፡ ተጠናቆ ፡ ከተዘጋጀ ፡ በኋላ ፡ እያንዳንዱ ፡ ጠበቃ ፡ እንዲከተለው ፡ መውጣት ፡ አለበት ። በተጨማሪም ፡ በሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ኮርስ ፡ ውስጥ ወይም ፡ የጠበቆች ፡ ውይይት ፡ በማድረግ ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ምግባር ፡ ፕሮግራም ፡ ውስጥ ፡ መግባት ፡ ይገባዋል ።

ጠበቆች ፡ ለራሳቸው ፡ ጥቅም ፡ ብቻ ፡ በማሰብ ፡ ሕግን ፡ ቢማሩ ፡ አይበቃም ፤ ሕዝቡም ፡ የተሻለ ፡ መንገድ ፡ በቅን ፡ ልቦና ፡ እንዲረዳና ፡ ሞያው ፡ እንዲከበር ፤ ፍትሕ፡ እንዲሰምር ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ምግባርንም ፡ መማር ፡ ይገባቸዋል ። ይህንኑ ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ምግባር ፡ አክብረው ፡ በእውነት ፡ ከሠሩ ፡ አገራቸውን ፡ በደንብ ፡ ረድተዋል ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ።

## LEGAL ETHICS

(Englih Summary)

*by Teferi Berhane*

The author deplores that by there are no recognized rules for the professional behaviour of lawyers in Ethiopia. He also regrets the non-existence of bar associations like those existing in other countries. Being a practitioner himself he discusses the problems of lawyers and the legal profession in Ethiopia.

He strongly advocates the promulgation of rules for professional behaviour and makes suggestions as to their content. He also urges the formation of bar associations which, in his opinion, should be modelled with regard to foreign experiences.